# ለሙስሊሞች ጥያቄዎች

# የክርስቲያኖች መልሶች

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተክርስቲያን
**Ethiopian Evangelical Baptist Church**
2822 S. Jupiter Rd.
Garland, TX 75041
Tel: (214) 703-0100 Fax: (214) 703-0161
WWW.EEBC-DALLAS.ORG

በጌርሃርድ ኔልስ

መግቢያ ........................................ 1
መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተለወጠ፥ እንደ ተበላሸ፥ በሚቃረኑ እሳቦች እና ጣልቃ ገብ ጽሑፎች እንደ ተሞላ የሚቀርቡ ቅዋሜዎች ...... 5
የመገለጥ ትርጉም ................................ 14
እስላማዊ ቅዋሜዎችና በመረጃ የተደገፉ መልሶቻችን .......... 17
የተፈጸሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች .................... 63
እስልምና ከመሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ራእይ ጋር አይስማማም፤ አይቀበለውምም ..................... 102
በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ መሐመድ እንደ ተተነበዩ ሆነው የቀረቡ ትንቢቶች ........................ 165
መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደ መጣልን .................... 175
የበርናባስ ወንጌል ................................ 177
የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ለምን በዙ? ................. 193
ማጠቃለያ ........................................ 201
እንግዲህ ወንጌል ምንድን ነው? ........................ 204

# ለሙስሊሞች ጥያቄዎች የክርስቲያኖች መልሶች

## መግቢያ

ገና ከጅምሩ ለአንባቢው ለማስተላለፍ የምንፈልገው መልእክት ቢኖር ይህን መጽሐፍ ባልተከፈለ ልብ ማጤንና በቀረቡትም እውነታዎች መሠረት ከስሜታዊነት የራቀ ብስል ማጠቃለያ ማበጀት አስፈላጊ እንደ ሆነ ነው። ሃይማኖታዊ መረዳቶችህን በተመለከተ አስቀድመህ በአእምሮህ ከመወሰን አላመለጥህም ይሆናል። ይህ በአመዛኙ ተጽዕኖ የሚደርስበት፡- አንድ ሰው ከሚኖርበት አካባቢ፥ ከተቀበላቸው ሃይማኖታዊ መመሪያዎች፥ ከሚያከብራቸው ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችና በዓላት፥ ከወላጆች፥ ከዘመዶችና ከጓደኞች ሃይማኖታዊ ልምምድና በአጠቃላይም ከሁለንተናዊ የሕይወት ዘይቤ ነው። ይህንንም ሁኔታ የሃይማኖት ቡድኖችና የማኅበረሰቦች ቀናተኛ ዝንባሌና የወግ ቁራኛነት እያርገበገበ ያቀጣጥለዋል። ዓላማችን ግን እነርሱን ለማሳጣት አይደለም።

«ክርስቲያን» የሚል ስያሜ ከተሰጣቸው ምናልባትም 99 በመቶ የሚሆኑት እንደዚያው እንደ ሆኑ ራሳቸውን የሚቆጥሩትና «ሙስሊሞች» ተብለው የተለዩትም ወደ እስልምናው የሚወግኑት በዚህ ምክንያት እንደ ሆነ ግልጽ ነው። የሃይማኖታቸውን ግንብ ጥሰው ወደ ሌላው የሚዘልቁ እናላ ሲሆኑ፥ እነርሱም ቢሆኑ በአመዛኙ የጋብቻ ዝንባሌ ያላቸው ናቸው። ጥናትና ምርምር ካደረጉና ቀድሞ ከለመዱት ሃይማኖት ጋር ያለውን የእውነት ይዘት ካወዳደሩ በኋላ ይህን እርምጃ የሚወስዱ ሰዎች የሉም ለማለት ያስደፍራል።

ይህ ልቅ ዐረፍተ ነገር ተከታዩን ጥያቄ በማንሣት በቀላሉ ሊብራራ ይችላል፡- ከአንድ ከተወሰነ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ስለ ሌሎች ሃይማኖቶች ያልተዛባ ሚዛናዊ አስተያየት ለመስጠት የሚያስችላቸውን ያህል እውቀት ያላቸው ምን ያህሉ ናቸው? እውቀታቸውን ስሕተት ለመፈላለግ ተግባር ሳያውሉ፥ እንደዚህ ባሉት ሃይማኖቶች ዘንድ ያለውን እውነት ለማረጋገጥ የሚያስችል እውቀትስ ያላቸው ስንቶች ናቸው?

እውነት ለድርድር ልትቀርብ ወይም ልትከፋፈል እንደማትችል እናምናለን፤ እውነት ፍጹም ናት። እውነት «እውነቶችን» ታገልላለች። የኋለኞቹ ከመጀመሪያዋ ጋር የማይስማሙ ከሆነ፥ አንድም ውሸቶች ናቸው፤ ከዚህም ቢሻል ስሕተቶች ናቸው። እኛ የምንጠቅሰው ከእግዚአብሔርና ስለ እግዚአብሔር የሆነውን መለኮታዊ እውነት፥ እንዲሁም ስለ እርሱ ዕቅዶችና ስለ ሰውም የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ ነው። ሁለት የሚቃረኑ ዐረፍተ ነገሮች ሁለቱም እውነት እንደማይሆኑና ተመሳሳይ ምንጭም እንደማይኖራቸው ግልጽ ነው። በውጤቱም በእውነተኛ ነገር የሚያምን ሰው እውነትነት ለራቀው ጉዳይ ምንም ትዕግሥት ሊኖረው አይችልም። ምናልባትም ብቸኛው አጠያያቂ ገጽታ የእውነትን መሠረት ለመጣል የሚጠቀሙበት ዘዴ ይሆናል።

ሃይማኖታዊ ትዕግሥት ለእውነት እና የእውነት ባለቤት ለሆነው አካል ፍቅር ማጣት ነው። እንዲሁም በጨለማ ውስጥ እየተደናበረ በሞት አፋፍ ላይ ላለ ሰው ፍቅር፥ ምሕረትና ርኅራኄ ማጣት ነው። ሃይማኖታዊ ትዕግሥት ራስን የማታለል አስጸያፊ ገጽታ ነው። እንደዚሁም በ«ሌላው እውነት» ላይ በተደረገ ሐቀኛ ጥናት ሳቢያ የራስን እምነቶች ላለማጋለጥ ከመፈለግ የሚመነጨው ፍርሃት የዚሁ ራስን የማታለል ክፍል ነው። እውነት ግልጽ ሊሆን ይገባል! እንዲሁም እውነት መረጃ ሊኖረው ይገባል! ወደ እውነትም የሚደርሰው የሃይማኖት «ተጠቃሚ» ሳይሆን ቅን ፈላጊ ነው።

ዳሩ ግን ቅንነት ብቻውን በቂ አይደለም። ቁም ነገሩ ከተጨባጩ ነገር ላይ ሲሆን፥ ይኸውም እግዚአብሔርና መገለጡ ወይም ራእዩ ነው።

እግዚአብሔርን በእውነት የሚፈልግ ሰው ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍለው ቢሆን እንኳ ስሕተት ሆኖ የተመሠረተውን ነገር ለመተው ገና ከጅምሩ መፍቀድና መዘጋጀት አለበት። ያም ብርታትና ጥንካሬን ይሻል። ለግብዝነት ቢዳርግም እንኳን ሳይታወክ በራስ የሃይማኖት ጎራ ተቀምጦ ሁሉ የሚያምነውን ማመን፥ ሁሉ የሚያደርገውን ማድረግ፥ ሁሉ ወደሚሄድበት መሄድ በጣም ይቀላል።

እነዚህን ማስታወሻዎች ያጠናቀርኋቸው የእውነትን ዳርቻ ለማግኘት 12 ዓመታት ስለ ፈጀብኝ ነው። ከዚያም እውነተኛ ክርስቲያኖች ለመሆን



በቅተናል። ይህ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ በከፍተኛ ደረጃ መጽሐፍ ቅዱስንና በዚህች የእኛዪቱ ዓለም የቅዱስ ጉዞ ተጓዥ ወገኖቼን እምነቶች ላጠና 20 ዓመታት አልፈዋል።

ከባለቤቴ ጋር ወደ ኬፐታውን ከተዛወርን በኋላ በርካታ ሙስሊሞችን አግኝተናል፤ ከእነርሱም ጥቂቶቹ በኋላ ተወዳጅተውናል። በዚህም ጊዜ ከእስልምና ጋር ዳግም ተጋፈጥን። ራሳችንንም ሙስሊሞች ስለ ክርስትና እምነትና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ለሚሰነዝሩት ትችት አጋልጠናል። ደግሞ ሙስሊሞች ስለ እስልምና ስለሚሉትም ነገር ራሳችንን አጋልጠናል። ስለዚህ ጉዳይ ለመገንዘብ በመወሰናችን ስለ እስልምና የሚወራውን በመስማት ብቻ አልረካንም። ይልቁንም በገዛ ራሳችንም መርምረን ለማግኘት ቆረጥን። ምንም የተቀየጠ ነገር ሳይታከልበት ስለ እስልምና ከመሠረቱና በርካታ የ«ቅዱስ ቁርዓን» ትርጉሞችን፥ የሃዲስ ስብስቦችን፥ በእስልምና ሊቃውንት በእስልምና ርዕስ-ጉዳይ ላይ የተጻፉ መጻሕፍትንና በክርስትና እምነት ላይ የተጻፉ እስላማዊ መጻሕፍትን አሰባስበናል።

ሰው የራሱ ጽኑ መረዳት እያለው ሊያደርገው የሚችለውን ያህል ከአጉል አስተያየት ነጻ በሆነ መልክ ለእነዚህ ጥናቶች አስፈላጊ ጊዜ ከሰዋን በኋላ፥ ከተወሰነ ማጠቃለያ ላይ ደርሰናል። የእግዚአብሔርን እውነት ለማግኘት ራሳቸውን የሰጡትን ሌሎች ሰዎች ለመርዳት በመንገዳችን ላይ የደረስንባቸው ግኝቶች እዚህ ላይ ተመዝግበዋል። እነርሱም እውነትን ፈላጊው እሳቡ ሳይበታተን መልሱን በፍጥነት እንዲያገኝ ሊረዱት ይችላሉ። እግዚአብሔርን የሚፈልገው ሰው ማጠቃለያዎቻችንን እንዲሁ መቀበል የለበትም። ይልቁንም ማጠቃለያዎቻችንን የሚደግፈውን መረጃ እስተውሎ በመመልከት፥ በሕያው አምላክ ፊት ከራሱ ማጠቃለያ ላይ እንዲደርስ ይጠየቃል። በዚህ ትምህርት ላይ የሚሰነዘሩ ስሜታዊ ዘለፋዎች ፋይዳ የላቸውም። እነዚህ የቱን ያህል የተሳሳቱ ቢሆኑም እንኳ፥ ሰውዬውን መልሰው ወደ ነበረበት እምነት እንጂ ወደ የትም አያደርሱም።

አንድ ሙስሊም ወዳጃችን «ሐቆቹ ትክክል ሲሆኑ፥ አተረጓጎሙ ግን ስሕተት ነው» በማለት ስለ አንድ መጽሐፍ እሳብ ሰንዝሮ ነበር። እኛ ሐቆች ከባሕላችን ጋር በሚስማማና ለእኛ በሚመቸን መንገድ መተርጎም አለባቸው ብለን እንስማማም። ይኸው ወዳጃችን ራሱ የእግዚአብሔርን እውነት በመመሥረቱ ረገድ አገዛ ለማድረግ የገዛ መረዳታችንን በጽሑፍ

እንድናጠናቅረውና ሃይማኖታዊ ስሕተትን ወይም ቅጥፈትን እንድናጋልጥ ገፋፍቶናል። ዴንማርካዊው የፍልስፍና ጠቢብ የሆኑት ኤስ. ክርክጋርድ እንዲህ በማለት ተቃውሞ አቅርበዋል:- «መረጃ መረዳትን መወሰኑ አከትሟል፤ ይልቁንም መረዳት የራሱን መረጃዎች ይመርጣል እንጂ።» በእግርጥ ሰዎች የሃይማኖት መረዳቶቻቸውን ተስማሚና የተመረጡ የመከራከሪያ ነጥቦች ለማቅረብ ያጠናክሩ እንጂ በዚህ መንገድ ከሐቀኛ ድምዳሜ ላይ ሊደርሱ አይችሉም።

ውድ አንባቢ፥ እነሆ በፊትህ ከማንም ወይም ከምንም በላይ እግዚአብሔርንና እውነትን የሚወድ ሰው ግኝቶች በአጭሩ ቀርበውልሃል። የዚህም ሰው ፍቅር ከዕውርነት የራቀ ነው።

መረጃው ሁሉ እስኪታወቅና እውነትነቱ ወይም ደግሞ ውሸት መሆኑ እስኪረጋገጥ ድረስ ይህንን መጽሐፍ ወደ ጎን እንዳይተው አንባቢውን ልናበረታታ እንወዳለን። ምናልባት ለሙስሊም አንባቢ አስደንጋጭ የሚመስሉ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ዳሩ ግን የእነዚህን ነገሮች እውነት ለመረዳት በታማኝነት፥ ስሜታዊነት ባላየለበትና መረጋጋት በሰፈነበት መንገድ መወሰኑ ይመረጣል። ለዚሁም እንዲረዳው በለመዳቸው አስተሳሰቦቹ ጠባብ ባሕር ላይ እየተንሳፈፈ እንዲኖር ከሚያደርጉት ሙጃዎች ላይ ዓይኑን መንቀል ይጠበቅበታል።

ጌርሃርድ ኔልስ



# መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተለወጠ፥ እንደ ተበላሸ፥ በሚቃረኑ አሳቦች እና ጣልቃ ገብ ጽሑፎች እንደ ተሞላ የሚቀርቡ ቅዋሜዎች

## ቁርዓን መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተለወጠ ይናገራልን?

ቁርዓን የመጽሐፍ ቅዱስን ተቀባይነት በመግለጽ፥ ማጥናትና መታዘዝ እንደሚገባ ያወሳል።

> «እኛ ተውራትን በውስጥዋ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትኾን አወረድን፤ ... በፈለጎቻቸውም (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲኾን አስከተልን፤ ኢንጂልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት፥ በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ፥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሣጭ ሲኾን ሰጠነው... ወደ አንተም (መሐመድ) መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን በውነት አወረድን» (ሱረቱ 5፡44-48)።

> «እላንተ የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! ተውራትንና ኢንጂልን፥ ከጌታችሁም ወደናንተ የተወረደውን እስከምታቆሙ (እስከምትሠሩባቸው) ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም በላቸው፤ ከጌታህም ወደ አንተ የተወረደው ቁርዓን ከነሱ ብዙዎቹን ትዕቢትንና ክሕደትን በእርግጥ ይጨምርባቸዋል ... እነዚያ ያመኑና (በቁርዓን) እነዚያም ይሁዳውያን (ብሉይ ኪዳን) የሆኑ ሳቢያኖችም፥ ክርስቲያኖችም፥ (ከነርሱ) በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነና መልካምን ሥራ የሠራ ሰው፥ በነርሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነርሱም አያዝኑም» (ሱረቱ 5፡68-69)። «እነርሱም ተውራትንና ኢንጂልን ከጌታቸውም ወደ እነርሱ የተወረደውን መጽሐፍ ባቋቋሙ (በሠሩበት) ኖሮ ከበላያቸውና ከእግሮቻቸው ሥር በተመገቡ ነበር» (ሱረቱ 5፡6፤ 5፡15)።

> «የመጽሐፉን ባለቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በኾነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ! ከእነሱ እነዚያን የበደሉትን ሲቀር፤ በሉም፡- በዚያ ወደኛ በተወረደው፥ ወደናንተም በተወረደው አመንን፤

አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው፤ እኛም ለርሱ ታዛዦች ነን» (ሱረቱ 29:46)።

«ይህም ቁርዓን፥ ከአላህ ሌላ (ከኾነ ፍጡር) የተቀጠፈ፥ ሊኾን አይገባውም፤ ግን ያንን ከርሱ በፊት ያለውን (መጽሐፍ)፥ የሚያረጋግጥና በመጽሐፉ ውስጥ ያለውን የሚዘረዝር ... ነው» (ሱረቱ 10:37)።

«ከበፊቱም የሙሳ መጽሐፍ መሪና ጸጋ ሲኾን አለ፤ ይህም እነዚያን የበደሉትን ሊያስፈራራ በዐረብኛ ቋንቋ ሲኾን (የፊቶቹን መጻሕፍት) አረጋጋጭ መጽሐፍ ነው፤ ለበጎ አድራጊዎችም ብስራት ነው» (ሱረቱ 46:12)።

«ያንን ብርሃንና ለሰዎች መሪ ኾኖ ሙሳ ያመጣውን መጽሐፍ፥ ክፍልፍሎች የምታደርጉት ስትኾኑ ማን አወረደው? (የወደዳችኋትን) ትገልጿታላችሁ ብዙውንም ትደብቃላችሁ፤ እናንተም አባቶቻችሁም ያላወቃችሁትን ተስተማራችሁ» (ሱረቱ 6:91)።

«ያም ከመጽሐፉ ወደአንተ ያወረድንልህ፥ ከበፊቱ ላለው አረጋጋጭ ሲኾን፥ እርሱ እውነት ነው» (ሱረቱ 35:31)።

«የእሥራኤል ልጆች ሆይ! ያችን በእናንተ ላይ የለገስኳትን ጸጋዬን አስታውሱ ... ከእናንተ ጋር ያለውን (መጽሐፍ) የሚያረጋግጥ ኾኖ ባወረድኩትም (ቁርዓን) እመኑ፤ በርሱም የመጀመሪያ ከሐዲ አትኹኑ ... እውነቱንም በውሸት አትቀላቅሉ፤ እናንተም የምታውቁ ስትኾኑ እውነትን አትደብቁ» (ሱረቱ 2:40-42)።

ከላይ የቀረቡት ምንባቦች ማጠናከሪያ የቀረበለት ነገር ስለ መኖሩ መታወቁን ያስገነዝባሉ። ቶራ በመሐመድ ዘመን ባልተቀየጠ መልኩ እንደ ነበር ያመለክታሉ።

«ሙሳንም መጽሐፉን በእርግጥ ሰጠነው፤ ከበኋላውም መልእክተኞችን አስከታተልን፤ የመርየምን ልጅ ዒሳንም ግልጽ ታምራቶችን ሰጠነው፤ በቅዱሱ መንፈስም አበረታነው» (ሱረቱ 2:87)።



«ከነሱም ጋር ያለውን (መጽሐፍ) አረጋጋጭ የኾነ መጽሐፍ፥ ከአላህ ዘንድ በመጣላቸው ጊዜ (ለአይሁዶች) ...በርሱ ካዱ» (ሱረቱ 2:89)።

«ከርሱ በፊት ያሉትን መጻሕፍት የሚያረጋግጥ ሲኾን፥ መጽሐፉን (ቁርዓንን) በእንተ ላይ ከፋፍሎ በእውነት አወረደ። ተውራትንና ኢንጂልንም (2) አውርዷል» (ሱረቱ 3:3)።

ከመሐመድ ዘመን በፊት ቢያንስ እስከ 350 ዓ.ም. ድረስ መጽሐፍ ቅዱስ በመሠረታዊ ወጥነቱ እንደ ነበር ጥርጥር የለውም። ከዚያ ወዲህ ምንም ለውጥ ያልተደረገበት፥ ያልተቀየጠ፥ ያልተበላሸ ወይም ጣልቃ ያልተገባበት ነው።

«ከእንተም በፊት (ከመሐመድ) ወደነሱ የምናወርድላቸው የኾኑ ሰዎችን እንጂ ሌላን አልላክንም፤ የማታውቁም ብትኾኑ፥ የመጽሐፉን ባለቤቶች ጠይቁ» (ሱረቱ 21:7)።

«እላንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና በመልእክተኛው፥ በዚያም በመልእክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ፥ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ፥ እመኑ፤ በአላህና በመላእክቱም፥ በመጽሐፎቹም፥ በመልእክተኞቹም፥ በመጨረሻውም ቀን የካደ ሰው (ከውነት) የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ» (ሱረቱ 4:136)። «ሁሉም በአላህ በመላእክቱም፥ በመጻሕፍቱም፥ በመልእክተኞቹም፥ ከመልእክተኞቹም በአንድም መካከል አንለይም፥ (የሚሉ ሲኾኑ) አመኑ» (ሱረቱ 2:285)።

«እውነተኞችም እንደኾናችሁ ተውራትን አምጡ፥ አንብቡዋትም በላቸው» (እዚህም ላይ የቶራ መኖር ተወስቷል) (ሱረቱ 3:93)።

«እላንተ መጽሐፉን የተሰጣችሁ ሆይ! ... ከእናንተ ጋር ያለውን የሚያረጋግጥ ኾኖ ባወረድነው (ቁርዓን) እመኑ» (ሱረቱ 4:47)።

አንደኛው ከጠፋ እንዴት እድርገው ሁለቱን ያወዳድሯቸዋል? (በተጨማሪም ሱረቱ 5:43፥ 46፥ 48፥ 65-68፤ 66:12፤ 2:44፥

53፤ 3፡70፥ 78፤ 5፡13፥ 15፤ 4፡44-46 እና 2፡78-79 አንብብ።)

በአይሁዶችና በክርስቲያኖች ላይ የቀረበው ወቀሳ መጽሐፉን አላግባብ ተርጉመዋል፤ እውነቱን ሸሽገዋል፤ ወይም የመጽሐፉን ቃል አልታዘዙትም የሚል እንጂ አበላሽተውታል የሚል እንዳልሆነ በጣም ግልጽ በሆነ ሁኔታ እንመለከታለን።

«የአላህንም ንግግሮች ለዋጭ የለም፤ ከመልእክተኞቹም ወሬ (የምትረጋጋበት) በእርግጥ መጣልህ» (ሱረቱ 6፡34)።

«የአላህ ቃላት መልለወጥ የላትም» (ሱረቱ 10፡64)።

## ክርስቲያን ሊቃውንት «መጽሐፍ ቅዱስ ተለውጧል» ይላሉን?

ጥቂቶች ይላሉ። ይህን ለመግለጽ ማብራሪያ መጠቀም ያስፈልጋል። አንድ ሙስሊም በእስልምና እምነት ተከታዮች መካከል ስለ ተወለደ ሙስሊም ነው። ይህ አመለካከት በአጠቃላይ ተቀባይነት ያለው ነው። በዚህ መንገድ ክርስቲያን ሊሆን የሚችል ሰው ግን የለም። መጽሐፍ ቅዱስ በጥብቅ ይህን ይቃረናል፡-

ክርስቶስ የተወሰኑ ተከታዮችን፡- «ስለ ምን፡- ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ ትሉኛላችሁ፥ የምለውንም አታደርጉም?» (ሉቃስ 6፡46) በማለት ጠይቆአቸዋል።

«ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል» (ማርቆስ 16፡16)።

ያለ እምነት ማንም ሰው ክርስቲያን ሊሆን አይችልም። እምነት በማን? በመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር!

ይህ እንዲያው በእግዚአብሔር መኖር ማመን ብቻ አለመሆኑ ግልጽ ነው፡-

«አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል» የተባለውን በመጽሐፍ ቅዱስ እናነባለን (ያዕቆብ 2፡19)።



የሚፈለገው ግን በታዛዥነት ራስን በእጆቹና በፈቃዱ ውስጥ ማስቀመጡ ነው። ስለ እግዚአብሔር፥ ለእኛ ስላለው ፈቃዱ፥ እንዲሁም ከፊቱ ስላለን አቋም መቆማችን ያለን እውቀት ሁሉ ከቃሉ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኝ ነው። በማስተዋል ወደ እግዚአብሔር መመለስና እርሱን ለመታዘዝ መወሰን፥ እንዲሁም ትእዛዙን፥ ምሪቱንና በተስፋ ቃሎቹ ላይ የተመሠረተውን ሕይወት መቀበል እያንዳንዱ ግለሰብ በፈቃደኝነት የሚፈጽመው ተግባር ነው።

በአንድ ሰው መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ክርስቲያን ለመሆን የሚደረግ ውሳኔ አስፈላጊነቱ፥ ልክ ልደት ለአንድ ሕፃን ሥጋዊ ሕይወት የሚያስፈልገውን ያህል ነው። ኢየሱስም እንዲህ ብሏል፡-

«እውነት እውነት እልሃለሁ፤ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም ... ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» (ዮሐንስ 3፡3፥5)።

ከቆንስጣንጢኖስ ዘመን ጀምሮ (274-337 ዓ.ም.) ቤተ ክርስቲያን እንደ ተቋም ሆና ስትመሠረት፥ መንፈሳዊ ዝቅጠት ሥር መስደድ ጀመረ። ሰው «ክርስቲያን» የሚሆነው በመወለድና ቁርባንንና ጥምቀትን በመቀበል እንደ ሆነ (ከአዲስ ኪዳን ወይም ከኢንጂል ትምህርት በተቃራኒ) ሰዎች ተቀበሉ። በዚያን ጊዜ «ተራ» ክርስቲያኖች ይቅሩና ቄሶችም እንኳን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ እውቀት አልነበራቸውም። ባህልና ሥነ ሥርዓትም የእግዚአብሔርን ቃል ተካ። ይህም ወደ ኋላ «አውሮፓዊ ክርስትና» ወይም «የምዕራቡ ዓለም ክርስትና» ተብሎ የተጠራውን ክርስቲያናዊ ዓለም አስገኝቷል። እርሱም በእርግጥ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ላይ ያልተመሠረተ በመሆኑ «ክርስትና» አልነበረም።

እምነቱን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለሚመሠርት ግለሰብ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው አሳብ ፍጹም ሐሰተኛ ትምህርት ነው። «ክርስቲያን» የሆነ ምዕራብ እንዲያውም «ክርስቲያን» የሚባል አገርም በፍጹም አልነበረም። ምናልባት አንድ ሕዝብ የክርስትናን ሃይማኖት ተቀብሎ ይሆናል፤ ምናልባት አዲስ ዓይነት እምነቶችን በመምሪያ መልክ በጅምላ በመቀበል

የክርስቲያን በዓላትን አክብሮ ይሆናል። ይሁን እንጂ በመሠረቱ እምነት ሁልጊዜም በግለሰቡ ውሳኔ ላይ የሚያርፍ የሕይወት አቋም ነው።

የጅምላ ክርስትና በበረከተበት ሁኔታ ውስጥ እምነታቸው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ የተመራና ከጅምላ ክርስትና የጠራ ምሳሌ ለመሆን ባለማቋረጥ የጣሩ አማኞች ነበሩ። በዚህ ሁኔታ ዛሬም ሳይለወጥ ቀጥሏል።

የ«ውጪው» ሰው ስለ «ክርስትና» የሚረዳው ነገር ቢኖር የሃይማኖታዊ አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን እንደ ያዘ ምዕራባዊ ባህል አድርጎ ነው። ይህም ባህል የመስቀል ጦርነትን ከማወጅ፥ ጦርነቶችን ከመቀደስና በአስከሬ መጠጦች ከመታጠብ፥ ግብረ ገብነት ተብሎ ሊጠራ የማይችለውን ድርጊት ከመቀበልና ከማስፋፋት ወደ ኋላ ያላለ ነው። በአጭሩ፥ እንዲህ ዓይነቱ ክርስትና የእግዚአብሔርን ቃል ከማወቅና ከመታዘዝ የተለየና የራቀ ነው።

ዳሩ ግን ከላይ እንዳየነው ውዳቂ ሞራል ባለው የጅምላ ክርሰትና ውስጥም እንኳ አሁንም እግዚአብሔርን የሚወዱ፥ ሰፈቃዱ የሚታዘዙ፥ የተሰየና የተሰጠ ሕይወት የሚኖሩ ብዙዎች ናቸው። እነዚህኞቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የሚመሩ ናቸው። ስለ ሆነም ሁለት ዋና ዋና የክርስትና የሥነ-መለኮት ዐቢይ መስመሮች መከሰታቸው የሚያስገርመን አይሆንም። አንደኛው በሰው የሚመራ ነው (ሰብዓዊ፥ ለዘብተኛ፥ ስሜታዊ፥ ሌላም ሌላም ሰማለት ይቻላል)። በዚህ መሥመር የቤተ ክርስቲያን አባልነት ሰመጽሐፍ ቅዱስ እምነትና መመዘኛዎች ቅድመ-ሁኔታ ሆኖ አይቀርብም፤ ሆኖም አንድ ሰው ለጥምቀትና ለመሳሰሉት «ሥርዓቶች» ራሱን አሳልፎ ከሰጠ ክርስትና እንዲሁ የሚከሰት ተደርጎ ይወሰዳል።

ኢየሱስ በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ውስጥ የሚናገረው ስሰዚህ ዓይነቱ ክርስትና ነው፡-

> «በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን አውቃለሁ። በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር። እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው። ሀብታም ነኝና ባለ ጠጋ ሆኜአለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም የምትል ስለ ሆንህ፥ ጐስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ . . .» (ራእይ 3፡ 15-17)።



ክርስትናን እንደዚህ አድርገህ ተመልክተህ ከሆነ፥ ለአንተ የሚሆን የምሥራች አለኝ፡- ክርስትና እንደዚህ አይደለም! እንደዚህ ሆኖም አያውቅም። ለዘብተኛ ሥነ-መለኮት የእግዚአብሔርን መገለጥ በመካድ ለራሱ፥ ለሕይወት ዘይቤውና ለዓላማው በሚመች መልኩ «ተርጉሞታል።» ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች በታላቅ ጉጉት መጽሐፍ ቅዱስን የመጻረሪያ ነጥቦች አድርገው የተቀበሏቸውን «ቅራኔዎች» እና «ብረዛዎች» ያገኟቸው እነዚሁ «የሥነ-መለኮት ምሁራን» ወይም «የክርስትና ሊቃውንት» የተባሉት ናቸው።

ይህም ሆኖ እምነታቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የመሠረቱ ሌሎች በርካታ ክርስቲያን ሊቃውንት መኖራቸውን ስጠቅስ ደስ እያለኝ ነው። ያ እምነታቸው ዓይናቸውን አይጨፍንባቸውም። በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱሰ በእጅ በተገለበጠባቸው በ3000 ዓመታት የጊዜ ገደብ ውስጥ ሠርገው የገቡትን ማናቸውንም የመገልበጥ ስሕተቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለማጥራት ሳለፉት 100 ዓመታት እጅግ ተግተው ሠርተዋል። ምንም ያህል ጥንቃቄ ቢደረግና ተደጋግሞ የማረጋገጫ ምንባብ ቢደረግም እንኳ ታትመው የሚወጡ መጻሕፍት ሁልጊዜም ስሕተት እንደሚኖርባቸው መጽሐፉን የደረሰ ሰው ሁሉ ይረዳል።

ባለፉት 100 ዓመታት ብቻ በክርስ-ምድር ተመራማሪዎች አማካኝነት ከተገኙት በጣም ጥሩና ጥንታዊ የሆኑ መዛግብት ሳቢያ የመጨረሻ ትርጉሞቻችን ከትችት ነፃ ለመሆን የተቃረቡ ናቸው። በ1948 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) ከሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የነበሩ በደንብ የተጠበቁ ብራናዎች በሙት ባሕር አካባቢ ተገኝተዋል። የነቢዩ ኢሳይያስ ሙሉ ቅጂም ተገኝቷል። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ካለው ቅጂ ጋር በሁሉም ዝርዝር ይስማማል።

ከዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ የተነሣውን ጥያቄ ለመመለስ ለዘብተኛ፥ «ዘመናዊ» የሥነ- መለኮት አዋቂዎች ብቻ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብረዛ ሊያገኙ የሚጥሩ ይመስላሉ። ብሂላቸውም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ወደ በኋላ ይገመገማል።

## ሙስሊም የሥነ-መለኮት ጠበብት መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተለወጠ ይናገራሉን?

ከላይ እንደ ወረደ ራእይ እንደሚቀበሉት ከሚናገሩበት ከቁርዓን ትምህርት በማፈንገጥ፥ ሙስሊም የሥነ-መለኮት ጠበብት የዘመናዊ «ክርስቲያን» ሃያሲያንን አሳቦችና ገለጻዎች ተቀብለዋል። ይህ ብዙም የሚያስደንቅ ነገር አይደለም፤ ምክንያቱም ቁርዓን በጥራቱና በተአማኒነቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ እንደ ሆነ ለማሳየት፡ከፍተኛ ፍላጎት ስላላቸው ነው። ሚዛናዊ ብያኔ ለመስጠት ግን በቁርዓን ላይ የቀረቡ የሙስሊም ጽሑፍ ሃያሲያን የት እንዳሉና ግኝታቸውም ምን እንደ ሆነ መጠየቅ ይኖርብናል። በቁርዓን ላይ ሂስ ማቅረብ በሙስሊሞች ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ አያውቅም።

ሙስሊሞች መጽሐፋቸውን ናዚል (ከሰማይ የመጣ) አድርገው ስለሚመለከቱ፥ ከሰብአዊ ትችት በላይ እንደ ሆነ ይቈጥራሉ። የመጽሐፍ ቅዱስን መገለጦች ባሕርይ ሊገመግሙ ግን እጥፍ ድርብ መመዘኛዎች ማንጋጋታቸውን እኛ እንደ ደካማነት እናየዋለን። ስለዚህ እንድም ቅዱሳት መጻሕፍትን ሁሉ ለትችት ሳናቀርብ እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት እንቀበላቸዋለን፤ አሊያም ተአማኒነታቸውን ለመለካት ቅዱሳት መጻሕፍትን ሁሉ እንፈትናቸዋለን።

ይህ በርካታ ሙስሊሞች ያለ ምንም ማረጋገጫ የሚሰነዝሩት የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባቦች ሆን ተብለው የመለወጣቸው የከረረ ክስ «ታረፍ-ዒ-ላፍዚ» ተብሎ ይጠራል። ይህን ጉዳይ ያጠኑ ሙስሊም ጸሐፍት ክሱ በአይሁዶች ወይም በክርስቲያኖች ላይ ሊረጋገጥ እንደማይችል በግልጽ ማስታወቃቸውን ታውቃለህ? የአሊጋር ኮሌጅ መሥራች የሆኑት ሰር ሰይድ አሕመድ ካን፥ «በእኛ በመሐመዳውያን አመለካከት ብረዛው (ታሪፍ-ዒ-ላፍዚ) መፈጸሙ አልተረጋገጠም» በማለት ጽፏል። ሰር ሰይድ ኢማም ቡክሃሪንና ፊክሩዲን ራዚን በመጥቀስ በአሳባቸው እንደሚስማሙ ይናገራሉ። ፊክሩዲን ራዚ በመሐመድ ወንድም ልጅ በአብን አባስ ሥልጣን የሚከተለውን ያስቀምጣል፡- «አይሁዶችና የቀድሞ ክርስቲያኖች የተውራትንና የኢንጂልን መጻሕፍት በመለወጡ ጉዳይ ተጠርጥረዋል። ዳሩ ግን በታወቁት ዶክተሮችና የሥነ-መለኮት ጠቢባን አመለካከት መጽሐፉን መለወጥ ሊሆን የሚችል ነገር አይደለም፤ ምክንያቱም እነዚያ ቅዱሳት መጻሕፍት በሰፋት



የተሰራጩ፥ በአጠቃላይም የታወቁና ከትውልድ ወደ ትውልድ የተሳለፉ ስለ ነበሩ ነው።» ይህ ምስክርነት እውነት በመሆኑም፥ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አሳማኝ የሆኑትን እውነቶች ሁሉ እናቀርባለን። የምንጠይቀው ነገር ቢኖር፥ እነዚህን እውነቶች አስተውሎ ለመመርመር እንባቢው በቂ ጊዜ እንዲወስድ ብቻ ነው። እንቁላሎችዋን በጥድፊያ ጥላ የምትነሣ ዶሮ ምንም ጫጩቶች ለመፈልፈል እንደማትችል ሁሉ፥ እውነቶችን በጽሞና ለመመርመር የማይፈልግ አእምሮም እውነትን ለማግኘት አይችልም።

ለእውነት እውነተኛ ጥማት ማግኘት ለእኛ ምንኛ አስፈላጊ ነው! ይሁንና መነጽር አንድን ዓይነ-ሥውር እንዲያይ እንደማይረዳው ሁሉ፥ በእውነት የተሞሉ ዐረፍተ-ነገሮችም እድልዎ ያለበትን አእምሮ መንፈሳዊ እውነትን እንዲያስተውል ሊረዱት አይችሉም።

ስለ ሆነም ከእውነቶች በተጨማሪ ሰው ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር፥ ማለትም ለእግዚአብሔርና ለመንገዶቹ ሁሉና ለመገለጡ የተከፈተ አእምሮ፥ እንዲሁም በማንኛውም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እርሱን ለመታዘዝ ፈቃደኛነት ያስፈልጋል። ይህም ፈቃደኝነት የእምነታችን ማጠቃለያ ነው።

# የመገለጥ ትርጉም

ወደ ቀጣዩ ትምህርታችን ከመመልከታችን በፊት፥ በአንድ በኩል በክርስቲያኖች፥ በሌላ በኩል ደግሞ በሙስሊሞች በተለያዩ አተረጓጐሞች የተላበሰውን «መገለጥ» የሚለውን ቃል መተርጐም አለብን።

እስልምና እንዲህ ይላል፡- መጽሐፍ (ቁርዓን) ከእግዚአብሔር (ናዚል = የወረደ) ከእግዚአብሔር የመጣ መገለጥ ነው።

ክርስትናም በበኩሉ፡- ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው ይላል።

እንግዲህ ወሳኙ ጥያቄ፡-

ክርስቶስ የእግዚአብሔር ቃል (ሎጎስ) ነው = መገለጥስ ነውን? (ሱረቱ 3፡45፤ 4፡171፤ ዮሐንስ 1፡1፥14)

ወይስ

ቁርዓን የእግዚአብሔር ቃል ነው = መገለጥስ ነውን? ምናልባትስ ሁለቱንም?

ይሁንና እግዚአብሔር ራሱን በቃላት ብቻ ለመግለጽ እንደማይችል መገንዘብ አለብን! ስለ ራሱ፥ ስለ ባሕርዩና ስለ ፈቃዱ መረጃዎችን ይሰጣል። ስለ ራሱ የሚያቀርበው መገለጥ የእርሱ «በግልጽ መታየት» እና «መግለጫ» ነው። ይህም የሆነው ለእርሱ ሥጋ በተዘጋጀለት ጊዜ ነው (ዕብራውያን 10፡5)። ስለዚህም ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡-

> «እኔን ያየ አብን አይቶአል» (ዮሐንስ 14፡9)።

በተጨማሪም ሐዋርያው ዮሐንስ የሚከተለውን ዘግቦልናል፡-

> «ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን» (ዮሐንስ 1፡14)።



በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስለ ተገለጸው የእግዚአብሔር ስም ያህዌና ስለ ኢየሱስ የምናውቀውን ነገር የምናገኘው ከመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ላይ ነው። ይህ ከእግዚአብሔር ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ የተጻፈ መገለጥ ነው። እያንዳንዱ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ ሥልጣን አምኖ ይቀበላል።

መጽሐፍ ቅዱስም እንደዚሁ ደረጃ በደረጃ ወደ መገለጡ ፍጻሜ ይኸውም እግዚአብሔር ራሱን ወደ መገለጥ ያመራል። ይህ መገለጥ ዛሬ የእስልምና ሥነ-መለኮት እንደሚረዳው «ናዚል» አይደለም። በተመሳሳይ ጽንሰ-አሳብ ከተለካ ቁርዓንም ሊሆን አይችልም («ክርስቲያኖች ሙስሊሞችን ይጠይቃሉ» የሚለውን መጽሐፍ ተመልከት)። መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን የእጅ አሻራ (የግለሰቦችን የቋንቋ አጠቃቀም፥ የተለያየ ደረጃ ያለውን የእውቀትና የባሕርይ ብቃት፥ ያለ እርሱ በጊዜው መጽሐፍ ቅዱስ ከአእምሮ በላይ ሊሆን ይችል የነበረውን ዘመናዊ የሳይንስ እውቀት ጽንሰ-አሳቦች አንጻራዊ መላምትና የአጻጻፍ ስልት) በደንብ ያሳያል።

ሙስሊም አንባቢ ይህ የመገለጥ ጽንሰ-አሳብ እርሱ ከሚያውቀው ስለሚለይበት ለመቀበል አስቸጋሪ ሊሆንበት ይችላል። ዳሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስን ከ«ናዚል» ጽንሰ-አሳብ ማመዛዘኑ የሙስሊሞች ስሕተት እንደ ሆነ ለመጠቆም እንወዳለን። ትንሽ ዘግየት ብለን እንደምንመለከተው፥ መጽሐፍ ቅዱስ በከፍተኛ ደረጃ የሚያቀርባቸው የመገለጥ መረጃዎች በቁርዓን ውስጥ አልተገኙም። እነዚህም የተፈጸመ ትንቢት፥ ታሪካዊ መረጃዎች፥ ተባባሪ ምልክቶችና ድንቆችን ያካተቱ ተቀባይነት ያላቸው የዓይን ምስክሮች ዘገባ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ተመሳሳይ ሰብአዊ የእጅ አሻራ በቁርዓን ውስጥ እናገኛለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እስትንፋስ-እግዚአብሔር በተለያዩ መልኮች ቀርቦ እናያለን።

> «እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት» (ኢሳይያስ 6፡1)።
>
> «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ...» (በኤርምያስ 13፡9 እና በሌሎች በርካታ ስፍራዎች)።
>
> «የእግዚአብሔር ቃል ... ወደ እኔ መጣ...» (በኤርምያስ 13፡8 እና በሌሎች በርካታ ስፍራዎች)።

«በሚልክያስ እጅ ለእስራኤል የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ሸክም ይህ ነው» (ሚልክያስ 1፡1)።

«በእሳትም የተቀላቀለውን የብርጭቆ ባሕር የሚመስለውን አየሁ» (ራእይ 15፡2)።

«ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ። ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ አትፍራ!» (ራእይ 1፡17)። ወይም ደግሞ፡-

«የተጋቡትን አዛቸዋለሁ፥ እኔ ግን አላዝም፥ ጌታ እንጂ... እኔ (ጳውሎስ) እላለሁ፥ ጌታም አይደለም፤ ... ዳሩ ግን ይህን እንደ ፈቃድ እላለሁ እንጂ እንደ ትእዛዝ አይደለም ... እንዲሁም በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አደነግጋለሁ... የጌታ ትእዛዝ የለኝም፥ ነገር ግን ... ምክር እመክራለሁ» (1ኛ ቆሮንቶስ 7፡10፥ 6፥17፥25)።

ከእነዚህ መልኮች መካከል ግንዛቤ ማግኘትን መማር አለብን። ሙስሊሙም ደግሞ «ቁርዓን» እና «ሃዲስ» «ታፍሲር»ም ብሎ የሚጠራቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቃልሎ እንደምናገኛቸው መረዳትን መማር አለበት።

ምንም እንኳ የተለያዩ ሰዎች «ቢመዘግቡት»ና በመካከላቸውም ረዥም የጊዜ ገደብ ቢኖር፥ አስፈላጊው የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ግን አንድ ዓይነት ነው። እግዚአብሔር ከሰው ጋር ለማድረግ ለሚፈልጋቸው ግንኙነቶቹ መልእክቱን ከማስተላለፍ ወደ ኋላ አይልም። እነዚህም ፍቅሩ፥ አሳቢነቱና ኀዘኑ፥ ርኅራኄው፥ ምሕረቱና ቁጣው፥ እንዲሁም ዕርቅ የማድረግ ዕቅዱ ናቸው። ክርስቶስ ከመጀመሪያው የብሉይ ኪዳን ጥቅስ ጀምሮ በእርሱ በሆነው የእግዚአብሔር መገለጥ ሁሉ ውስጥ ከዳር እስከ ዳር ይታያል (ከገጽ 63 ጀምሮና ከገጽ 137 ጀምሮ)። ይሁን እንጂ እንደ ሰው የመረዳት ብቃት፥ ሁሉም ነገር ደረጃ በደረጃ ተገልጿል።

በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በተመዘገበው ቃል ውስጥ እግዚአብሔርን በኢየሱስ ውስጥ እናገኘዋለን። ዛሬም እንኳ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት የሚገኘውን እምነታችንን በእርሱ ላይ ካደረግን፥ በመጽሐፍ



ቅዱስ እንደ ተዘገበው፥ አዲስ ልደትን መለማመድ እንችላለን። እሁንም ቢሆን የሚለውጠንና በእኛ ውስጥ የሚኖረውን መንፈስ ቅዱስ ለመቀበል እንችላለን!

መጽሐፍ ቅዱስ «ናዚል» ነው የምንል ከሆነ፥ ቁርዓንንም በተመለከተ ከሙስሊሙ እንደምንጠብቀው ሁሉ፥ የሰውን የእጅ አሻራ ለማብራራት መሞከር አለብን ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ፥ ከመለኮታዊ ምንጭ ለመምጣቱ ግልጽ መረጃ ስላለ ተጨማሪ ማረጋገጫዎች አያስፈልጉትም (ከገጽ 63፥157፥201 ጀምሮ)። ምንም እንኳ ጥንታዊ በሆኑ መሣሪያዎችና አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች በእጅ የተጻፉትን መጻሕፍት ለህልቁ መሳፍርት ጊዜያት መቅዳቱ አንዳንድ «ስሕተቶችን» ቢያስከትልም፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት በእስትንፋስ-እግዚአብሔር የተገኘ ነው (ቲዎፕኖስቶስ = እግዚአብሔር የተነፈሰው)። ሊቃውንት በቅርብ የተገኙትን በርካታ መዛግብት በማጥናትና በማገላበጥ የተገኙትን ስሕተቶች በሙሉ ለይተው አውጥተዋቸዋል፤ አብራርተዋቸውማል።

## እስላማዊ ቅዋሜዎችና በመረጃ የተደገፉ መልሶቻችን

በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ በሚያተኩሩ በርካታ የእስልምና መጻሕፍት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ ለሙሉ ተአማኒነት እንደሌለው ተደርጎ ቀርቧል። ለዚህ አቀራረብ ግልጽ የሆኑ ምክንያቶችን ማብራራቱን እንፈልግም። ዳሩ ግን በርካታዎቹ መግለጫዎች እንድም በአለማወቅ የመጡ፥ አሊያም እውቀቱ እያለ ሆን ተብለው የተቀመጡ፥ ሻል ካለም በእሉታዊ አቋም በተመሠረቱ መረጃዎች ላይ የሚደገፉ ናቸው። ምንም እንኳ ይህን ጉዳይ በጥቅሉ ማየቱን ብንመርጥም፥ የምንለውን ነገር ለማጠናከር ሁለት ደራሲያንን መጥቀስ ግዴታችን ይሆናል።

«ብርሃኑ» የሚል ስያሜ በተሰጠው፥ በአል-ሃጅ ሱልጣን ሐፊዝ አብዱል በተዘጋጀውና በማውላና ሰይድ ዚያ-ኡድ-ዲን አህመድ ጊላኒ እንደገና ታርሞ በቀረበው መጽሐፍ ውስጥ፥ «ሲኖፕቲክ» ጸሐፊዎች (ማለትም በይበልጥ ታሪካዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ትኩረት የሰጡ ሦስቱ የወንጌል ዘጋቢዎች ከስተቶቹን ይበልጥ ከፍ ባለ ደረጃ ከሚመለከተው ከአራተኛው ዘጋቢ፥ ከዮሐንስ ይልቅ በበለጠ ይመሳሰላሉ) ጳውሎስ፥ ሉቃስ፥ ማቴዎስና ዮሐንስ እንደ ሆኑ ተነግሮናል። በእርግጥ «ሲኖፕቲክ»

ጸሐፊዎች ሦስት ብቻ ናቸው፤ የዮሐንስ የሆነው የወንጌል ክፍል የተለየ ነው፤ እንዲያውም ጳውሎስ የወንጌልን መልእክት ጭራሽ አልጻፈም! ማንኛውም ዝቅተኛ የሆነ ትምህርት ያለው ክርስቲያን እንኳ እንደሚያውቀው «ሲኖፐቲኮቹ» ማቴዎስ፥ ማርቆስና ሉቃስ ናቸው።

እንዲህ ዓይነቶቹን ምሁራን ክርስቲያኖች በጥርጣሬ ዓይን መመልከታቸው ትክክል ነው። ምክንያቱም ተቀባይነት ያለው አስተዋጽኦ ለማበርከት ስለማይችሉ ነው። እጅጉ አድርጎ የሚያሳዝነው ግን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊሞች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያገኙት ብቸኛ መረጃ ክርክራቸውን ሙሉ ለሙሉ ባለ አንድ አቅጣጫ በሆነ፥ በተለየና በተመረጠ እውቀት ላይ ከሚገነቡ፥ ወይም ደግሞ እያወቁ ከሚከራከሩ፥ ካልተረዱ አሊያም ከማይታመኑ ሰዎች መሆኑ ነው።

የሆነ ሆኖ ሁሉም ሙስሊሞች እንዲህ ባለ ርካሽ መንፈስ እንደማይከራከሩ መጥቀስ ይኖርብናል። በመጀመሪያ ደረጃ ትንታኔያችንን በጸረ-ክርስትና አቋሙ ዓይነተኛ እና ከእኛ ሁኔታ ጋር የተያያዘና ሁለገብም በሆነው መጽሐፍ ላይ እንወስናለን።

የሚከተሉት ነጥቦች፥ ጥያቄዎችና ጥቅሶች «መጽሐፍ ቅዱስ - የእግዚአብሔር ቃል ነው ወይስ የሰው ቃል?» በሚል ርዕስ በቀድሞው ፕሪቶሪያዊ በዛሬው ጆሀንስበርጋዊ በሼህ ኤ.ኤስ.ኬ ጁማል ከተዘጋጀው መጽሐፍ የተወሰዱ ናቸው።

ገና በመግቢያው ላይ ሚስተር ጁማል የሚተዋወቁት

> «እስልምናን ጎጂ ከሆኑ እንቋሻሽ ንግግሮች እንደሚከላከሉና ለእስልምና ትምህርቶች እንደ ቀንደኛ ደጋፊ»፥ እንዲሁም «ከደቡብ አፍሪካ በጣት ከሚቆጠሩ አስተዋይ ፈላስፎች እንደ አንዱ» ሆነው ነው።

በእስልምና ላይ የሚነሣው ጎጂ እንቋሻሽ ንግግር የተባለው እንግዲህ ከእስልምና አስቀድሞ የነበረውን መጽሐፍ፥ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ሆነ እንረዳለን!

በትችታቸውም «ዘመናዊ ሥነ-መለኮት» የተባለውን መሥመር ይከተላሉ። ይህም ተፈላጊ መረጃ እንዳበረከተላቸው ጥርጥር የለውም። በተጨማሪም የመጽሐፍ ቅዱስ ባሕርይ ሙስሊሞች በሚያምኑበት ዓይነት የመገለጥ



ጽንስ አሳብ («ናዚል») ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማሰቡ ስሕተት ነው። ይህም በሚከተለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ተመልክቷል፡-

> «እያንዳንዱ የጌታ (የኢየሱስ) ቃል፥ ትእዛዝ፥ ፈቃድ፥ እገዳ፥ ትችትና ሌሎችም ትምህርቶቹ መጀመሪያ በተናገረበት የአራማይክ ቋንቋ በጥንታዊ ጥራቱ ከተራባ የእግዚአብሔርን እውነተኛ ቃል ወይም መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚያካትት ጥርጥር የለውም። ትልቁ ጥያቄ፥ ይህኛው መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬ አለ ወይ? የሚለው ሲሆን፥ መልሱም እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቅ እንደሚያውቀው፥ የለም የሚል ነው።»

ይህ ከቀደምት እስላማዊ ጽንስ-አሳቦች የማይስማማ ነው፡-

> «የማርያም ልጅ ስለ ሆነው ኢየሱስ ወደ እኔ ከደረሱት ነገሮች መካከል ለወንጌል ተከታዮች ከእግዚአብሔር ዘንድ በተቀበለው ወንጌል ውስጥ ... ሐዋርያው ዮሐንስ ወንጌሉን ከኢየሱስ ኪዳን ለእነርሱ ከጻፈው የተውጣጣ ነው ...» (ሊራቱ አይ ራሱል ቁጥር 149)።

ይህን ጥቅስ በትክክል ብናየው የምሥራቹ (ወንጌሉ) ለኢየሱስ ነበር የተሰጠው። በጽሑፍ ተሰጠው አይልም። ቋንቋውንም ደግሞ አይጠቅስም። እነዚህንም በጽሑፍ «ያስፈራቸው» ሐዋርያው ዮሐንስ ነበር። ከዚህም ሰነድ ውስጥ ከፊሉ በወንጌል ውስጥ ስለ መሐመድ የተነገረ ትንቢት እንዳለ ለማሳየት አለ አግባብ ከግልጋሎት ላይ ውሏል። በየትኛውም ስፍራ የዮሐንስ ዘገባ እውነተኛነትና ንጽሕና በኢብን ይሻቅ አልተጠየቀም (ኤ.ኤች. 85-151)። ብቸኛውና እውነተኛው ችግር ጥቅሱ የተወሰደው ከመጀመሪያዎቹ መዛግብት ሳይሆን፥ በተርጓሚው የግርጌ ማስታወሻ ላይ እንደ ተገለጸው፥ «ፓለስቲንያን ሊርያክ ሌክሽነሪ» ከተሰኘው የተጭበረበረ መጽሐፍ ነው።

በሚስተር ጁማል ጥቅሶች ውስጥ ትኩረት የተደረገው በመጀመሪያው ቋንቋ ማለትም በእስልምና በኩል ዐረብኛ ላይ መሆኑ ነው። በእርግጥ ቁርዓን ለአንድ ሙስሊም አላህ ለመሐመድ የሰጠው የእያንዳንዱ ቃል ስብስብ፥ ትእዛዝ፥ ወዘተ... ነው። ሃዲስም እንዲሁ በብዙዎች ዘንድ በቃላቱና በግብሮቹ ከላይ እንደ ተላከ ሆኖ ይቆጠራል። ሃዲስ በቁርዓን

ላይ እውቀትን ይጨምራል፤ ይተረጉመዋልም። በዚህም ሙስሊሞች ስለ ነቢያቸው፥ ስለ ቃሎቹና ግብሮቹ ዝርዝር ነገሮችን ለማንበብና ለመከተል ያስችላቸዋል። ሆኖም የመሐመድ ቃሎች በሙሉ የመመዝገብ አለመመዝገባቸው ነገር ሌላ ጉዳይ ነው፤ ሙስሊሞች ቁርዓንን በሚመለከቱበት ሁኔታ ነው መጽሐፍ ቅዱስን የሚመለከቱት። ይህ አሳሳች የሆነ ነገር ነው። ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ ስልት ስለ ስላምታዎች ወይም በመጽሐፍ ቅዱሷ መልእክቶች ውስጥ ስለ ተጠቀሱት ሕይወትና እምነት ጉዳይ በተመለከተ ለሚነሡ ጥያቄዎች የተሰጠውን ምክር ስለማይቀበል ነው። በሙስሊሞች አመለካከት እንዲህ ያሉ ዐረፍተ ነገሮች የሃዲስ ብቻ ናቸው። ሙስሊም ጓደኞቻችን ስለዚህ ነገር እንዲያውቁ ማድረግ አለብን። እግዚአብሔር በቃሉ ለሰው ልጅ ለማስተላለፍ የፈለገው ሁሉ ተላልፎአል። ይህም ዛሬ በእያንዳንዱ ክርስቲያን እጅ ይገኛል። ተጨማሪዎች ወይም ማሻሻያዎች ቦታ የላቸውም። በቁርዓንም ውስጥ እንኳ ለመጽሐፍ ቅዱስ የሚሆን ምንም ማሻሻያ አናገኝም።

ቢሆንም የሚከተለው ሲነገረን ደግሞ እንመለከታለን:-

> «የበፊቱ የእግዚአብሔር ቃል፥ በሰው እጆች ስለ ተበረዘ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ከሰው ቃል ለመለየት አይቻልም። አሁንም በአንዳንድ ስፍራዎች ኢየሱስ ለሕዝቡ ጥቅም የተናገረውን እንደ ፋርጥ የሆነውን የመለኮታዊ ጥበብ ትምህርቱን የእውነት ብልጭታ እናገኛለን፤ እነዚህ ግን በጣም ጥቂቶች ሲሆኑ፥ መጽሐፍ ቅዱስን ካጣበቡት ጣልቃ ገብ ጽሑፎች እና ግጭት ከሚፈጥሩ የምንባቦች ጥሻ መካከል የሚገኙ ናቸው ... ሁላችንም እንደምናውቀው፥ ክርስትና የተመሠረተው በዕውር እምነት ላይ ነው። ትክክለኛ አስተሳሰብም በክርስትና ውስጥ ምንም ሚና አይጫወትም ... አሁን ያለው የእንግሊዝኛ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ቢያንስ 100000 ስሕተቶች (በግምት በእያንዳንዱ ጥቅስ ውስጥ ሦስት ስሕተቶች ይገኛሉ ማለት ነው ጂ.ኤን.) እንደሚገኙበት፥ ዕብራይስጥን የተማሩ በርካታ ምሁራን ይስማማሉ ... ማንኛውንም የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ማን እንደ ጻፈው በእርግጠኝነት አይታወቅም ... የትኞቹ መጻሕፍት በመንፈስ በመነዳት እንደ ተጻፉ ክርስቲያኖች ራሳቸውም ከስምምነት ላይ አልደረሱም።»



ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች በተግባር አንዱ ከሌላው ስለ ተለየ፥ የትኛው ትክክል እንደ ሆነ የሚያውቅ አለመኖሩም ተወስቷል።

ለምን በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች እንዳሏቸው ክርስቲያኖች በተደጋጋሚ ተጠይቀዋል። ሙስሊሞች እነዚህ እትሞች የመጀመሪያዎቹ መዛግብት የተለያዩ ትርጉሞች እንጂ ሌላ አለመሆናቸውን ሲሰሙ ይደነቃሉ። የ«ኪንግ ጀምስ ትርጉም» በ1611 ዓ.ም. የተዘጋጀ ነው። ከቋንቋ እድገት ለውጥ የተነሣ በድጋሚ ማዘጋጀቱ አስፈልጓል። ከዚህም ባሻገር ሌሎች ተጨማሪ መዛግብት ከዚያ ወዲህ ተገኝተዋል። አንዳንዶቹ ቁጥሮች በግማሾቹ መዛግብት ሲገኙ በሌሎቹ ውስጥ ግን አልነበሩም (ከገጽ 26 ጀምሮ ተመልከት)። እነዚህ ምንባቦች «ታርመው በተዘጋጁ እትሞች» ውስጥ ይገኛሉ። የእነዚህን ምንባቦች መጠን ከጠቅላላው መጽሐፍ ስፋት አኳያ ለመረዳት እያንዳንዳቸው 12 ቁጥሮች ካሉአቸው 2 ክፍሎች በተጨማሪ (ቁጥር 5 እና 6 ገጽ 28 እና 29)፥ በድግግሞሽ ምክንያት የተሠረዙት ሁለት ቁጥሮች ከምንባቡ መልእክት ወይም ትርጉም ጋር ምንም ዝምድና ስለሌላቸው አጠያያቂ የሆኑትን ስምንት ዐረፍተ ነገሮች ወይም ክፍሎች መጥቀስ ይገባል። ይህም ከ7959 የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች ውስጥ 0.1 በመቶ መሆኑ ነው!

አንዳንድ እትሞች በከፍተኛ ጥንቃቄ ለሊቃውንት የተዘጋጁ ሲሆኑ፥ ሌሎች ደግሞ ያልተለመዱ ቃላትን ወይም ሐረጎችን በመተው፥ ከሥነ-መለኮት ጽንሰ-አሳቦች ይልቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችና ትምህርታቸው ላይ ለሚያተኩሩ ወጣቶች ወይም መጠነኛ ትምህርት ላላቸው አንባቢያን በሚስማማ መልኩ የቀረቡ ናቸው። የሁሉም መልእክትና ይዘት ከተለያዩ የቁርዓን ትርጉሞች (ማለትም ዩሱፍ ዓሊ፥ ዳውድ፥ ማርማዱክ ፒክትሆል፥ ጆርጅ ሴል፥ሮድዌል፥ አርቤሪ፥ወዘተ.) የበለጠ ተመሳሳይነት ያለው ነው።

> «ምንም እንኳ በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበራትና በሌሎችም አክራሪዎች መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም በተነባቢነቱ ከፍተኛ ደረጃ የያዘ መጽሐፍ መሆኑ እየተጋነነ ቢነገርም፥ እውነቱ ግን ተቃራኒው ነው።»

እነዚህን ነገሮች በተመለከተ ሙስሊሞች አለን የሚሉት ጥልቅ እውቀት ግራ ያጋባናል። ቢሆንም ለእነዚህ አባባሎቻቸው ምንም ማስረጃ

እንደሌላቸው እንረዳለን። «የታወቁ» የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንትና ማብራሪያ አዘጋጆች ተብለው የተጠቀሱ ሰዎች ሙሉ ለሙሉ ድብቅ ባሕርይ ያላቸው ናቸው።

እስልምና በቁርዓን ላይ የቃል በቃል ሂስን አለመፍቀዱ፥ ከፍተኛ ወይም የውጫዊ ገጽታ ሂስን (ከቃል በቃል ሂስ ጋር መምታታት የለበትም)፥ የሚያካሄዱ የሥነ-መለኮት ምሁራን ሁሉ በእርግጥ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛ ይዘት እንደሚያቀርቡ እንዲገምቱ፥ ለሙስሊሞች መንገዱን ይጠርግላቸዋል። ይህ እንዳልሆነ ደግሞ ሁሉም የሚያውቀው ነው። ምክንያቱም «ከፍተኛው ትችት» የተመሠረተው ባመዛኙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት በሌላቸው የፍልስፍና መላምቶች ላይ ስለ ሆነና የተለያዩ ፍቺዎች ወዳሏቸው ዐረፍተ ነገሮች ስለሚመራ ነው። በአሥራ ዘጠነኛውና በሃያኛው ክፍለ ዘመን ግምታዊ ሥነ-መለኮት በርካታ አመለካከቶችንና መላምቶችን አስገኝቷል። እነዚህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካለመሆናቸው በተጨማሪ ማረጋገጫ የሌላቸውና በክርስቲያኖችም ዘንድ ስፍራ ያልተሰጣቸው ናቸው። እንደዚህ ካለው ሥነ-መለኮት ማጣቀሻ መውሰዱ መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ ለሙሉ ውሸት በሆነ ብርሃን ውስጥ ያስቀምጠዋል።

የሆነ ሆኖ ሙስሊሞች

> «መጽሐፍ ቅዱስ ዱሮ የእግዚአብሔር ቃል ነበር»

እንዲሁም፡-

> «አሁን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ በማንኛውም የአስተሳሰብ ደረጃ በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ የተሰጠ የእግዚአብሔር ቃል ተብሎ ሊጠራ አይችልም»

በተጨማሪም፡-

> «እምነት መጽሐፍ ቅዱስን ከነስሕተቶቹና ከነማይመስሉ ነገሮቹ እንዳለ መቀበልን ይጠይቃል። በሌላ በኩል አስተውሎት ሰብአዊ ማመዛዘንን የሚያጥሉ ነገሮችን ከመቀበል ወደ ኋላ ይላል» በማለት ደምድመዋል።



እንዲሁም ሙስሊሞች የኪንግ ጀምስን፥ ታርሞ የተዘጋጀውንና ሌሎችንም እትሞች በተመለከተ ጥያቄ ያነሣሉ፡-

> «የእግዚአብሔር ቃል በበርካታ እትሞች እንዲቀርብ ለምን ያስፈልጋል? የእኛ ግንዛቤ የሚነግረን እውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ሳይቀየር፥ ሳይበላሽ፥ ሳይከለስ፥ ልክ ለክርስቶስ እንደ ተገለጸው ሆኖ መኖር እንዳለበት ነው።»

እነዚህን ወቀሳዎች ለመመልከት ለአፍታ ቆም ማለት ያሻናል።

በመጀመሪያ ደረጃ የእግዚአብሔር ቃል ለኢየሱስ አልተገለጸም። እርሱ የእግዚአብሔር መገለጽ፥ የእግዚአብሔርም ቃል ነው። ይህ በቁርዓን እንኳ ድጋፍ ተሰጥቶታል (ሱረቱ 4፡171 እና 3፡45፥ 59)።

ከዚያም ቀጥተኛ የሆኑትን ጥያቄዎች መጠየቅ አለብን፡- መጽሐፍ ቅዱስ የተለወጠው መቼ፥ የትና በማነው? በመሐመድ ዘመን ቶራና ወንጌል በእርግጥ እንደ ነበሩ ቁርዓን እንኳ የምስክርነት ቃሉን ይሰጣል (ገጽ 6-8)። መጽሐፍ ቅዱስ ከዚያ በኋላ ተቀይሯል ማለት እውነታን የሚጻረር አባባል ነው።

ቁርዓን ቀድመው የተላኩትን መገለጦች ለመጠበቅ እንደ ወረደ ይናገራል (ሱረቱ 5፡46-51)። እንዲሁም ቶራና ወንጌል መገለጥ መሆናቸውን በግልጽ ያስቀምጣል። ይህ ማለት ከእግዚአብሔር የመጡና በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ቃል ናቸው ማለት ነው። በተጨማሪም ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ለመለወጥ እንደማይችል ቁርዓን አበክሮ ይናገራል (ሱረቱ 6፡34 እና 10፡64)።

የአዲስ ኪዳን ጽሑፎች የተጠናቀሩት ከቁርዓን ከ500 ዓመታት በላይ አስቀድመውና ከእነዚያ ክብሉይ ኪዳን ጽሑፎች እስከ 1500 ዓመታት ዘግይተው በተወሰነ የታሪክና የጊዜ ገደብ ውስጥ ነው። እንደ ዕብራይስጥ፥ አራማይክና ግሪክ ሳይሆን ዐረብኛ በቁርዓን ከፍተኛ ተጽዕኖ ሳቢያ እስከ አሁን ድረስ የንግግር ቋንቋ ሆኖ ቆይቷል። የዕብራይስጥ ቋንቋ በእስራኤላውያን መሰደድ ጊዜ ለ1500 ያህል ሕያው ቋንቋ ከመሆን ታቅቦ ቆይቶ ነበር፤ አራማይክ ግን ሕያው ቋንቋነቱ ካከተመ ቆይቷል። በተለይ በዚህ ክፍለ ዘመን የተደረገው ምርምር የዕብራይስጥ ቋንቋ

እውቀታችንን በደንብ በማሳደግ የቋንቋውን ችግር ለማቃለል ረድቷል። እንደ ማንኛውም የቋንቋ እርጅና ሁሉ (እስኪ ከ200 ዓመታት በፊት የተጻፈውን መጽሐፍ ለማንበብ ሞክር) ይህ ሁኔታና አይቀሬ የሆነው የማንኛውም ቋንቋ እርጅና፥ መጽሐፍ ቅዱስ በወቅቱ በሚነገረው ቋንቋ እውነተኛውን መልእክቱን ሳይዛባ እንዲያስተላልፍ በየጊዜው ተመጣጣኝ ትርጉሞችን ማዘጋጀት አስፈልጓል።

ለክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍትን ወይም ጸሎቶችን በተጻፉበት በመጀመሪያው ቋንቋ የማንበቡ ወይንም የመድገሙ አስፈላጊነት በሜት አይሰጠውም። በመሠረቱ እኛ የምናተኩረው በመልእክቱ ይዘት ላይ እንጂ በመጀመሪያ በተጻፈበት የቋንቋ አወቃቀር ላይ አይደለም። አንድ ዓይነተኛ ክርስቲያን ትርጉሞቻችንን ከሚያዘጋጁት ከእነዚያ ላቅ ያለ እውቀት ካላቸው የቋንቋ ሊቃውንት ቡድኖች እኩል በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ቋንቋ(ዎች) ላይ እውቀትን ለማካበት የሚችል አይመስልም። ከዚህም በተጨማሪ፥ በቋንቋችን ስናመልከው፥ ስናመሰግነው፥ ወይም በጸሎት ስንናገረው እግዚአብሔር የምንለውን እንደሚረዳ አጥብቀን እናምናለን።

እንዲሁም አንድ ሰው ምንጩን በትክክል መረዳት እስካልቻለ በመንፈስ በመነዳት የተገኘ ትንቢታዊ መልእክት አጣራጣሪ እንደ ሆነ በሙስሊሞች የሚቀርበውን አመለካከት አንቀበልም። በመሠረቱ ነቢዩ ወይም በመንፈስ በመነዳት የተሰጠውን መልእክት የሚጽፈው ሰው በእግዚአብሔር እጅ ያለ መሣሪያ ነው። የደብዳቤውን ተአማኒነት ለማረጋገጥ ብንፈልግ ብዕሩ በማንና የት እንደ ተሠራ በማወቅ አለማወቃችን ላይ አናስደግፍም። መልእክቱ እውነተኛ እንደ ሆነ እርግጠኞች እስከ ሆንን ድረስ ይህ ሁሉ አስፈላጊ አይደለም።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ 100000 ስሕተቶች አሉ የሚለው ወቀሳ ምላሽ እንኳ መስጠት የማያስፈልገው ትርጉም-አልባ ንግግር ነው። እንዲሁም የክርስትና እምነት የታወረ እምነት ነው የሚለውም አባባል ጸሐፊው ምን መረጃ እንዳገኘ በሚገባ የሚገልጥ አይደለም።

እንደዚህ ባለ የመጽሐፍ አቀራረብ ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚቀርቡትን ዘለፋዎች ሁሉ ማካተት እንደማይቻል ግልጽ ነው። ይሁንና ከሌሎች ጎልተው የሚታዩ ጥቂት ነገሮችን በመጀመሪያ እንመለከታለን።



በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሚገኙ የሚነገርላቸው ማታለያዎች፥ ብልሽቶች፥ የተጨመሩ ጽሑፎችና ግጭቶች

አሁንም በአል-ሐጅ ሱልጣን ሐፊዝ አብዱል ከተዘጋጀውና በማውላና ሰይድ ዚያ-ኡድ-ዲን አሕመድ ጊላኒ ታርሞ ከቀረበው «ብርሃኑ» ከተሰኘው መጽሐፍ አንዳንድ ምንባቦችን እጠቅሳለሁ። ከመቅድሙ ውስጥ (ገጽ 11) የሚከተለውን እናነባለን፡-

> «የኃጢአት ጅማሬን አስመልክቶ ስላለው ክርስቲያናዊ ንድፈ እሳብ፥ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለ መባሉ፥ ስለ መሢሑ የመስቀል ዝክረ-ሐተታ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሰው ልጅ ደኅንነት ስለማግኘቱ የመሠረተ እምነት ትምህርት በሌሎችም አያሌ አሳሳቢና አጠያያቂ ጉዳዮች ላይ ድጋፍና ነቀፋ ለመስጠት የሚረዱ እስላማዊ ያልሆኑ መረጃዎችን ለይቼ ለማሰባሰብ ተስፋ አደርጋለሁ። ከሁሉም በላይ ይህ መጽሐፍ በምሥራቁና በምዕራቡ፥ በመልካሙና በክፉው ኃይል መካከል እምባሳደር ይሆን ዘንድ በዚህ ዓይነት ትሕትና በተሞላበት መንገድ እጠይቃለሁ። በተጨማሪም የዓለም ቅዱሳት መጻሕፍትና የበርካታ ፍልስፍናዎቻቸው ጥልቅ ሃይማኖታዊ እውቀት፥ በማንኛውም ሕዝብ፥ አገር፥ ወይም የእምነት አቋም ላይ እውነተኛ የመልካምነት መንፈስ እንደሚያሳድር በጣም እርግጠኛ ነኝ።»

ከመጀመሪያው ክፍል ጋር ሙሉ ለሙሉ ከሚቃረነው ከዚህ አንቀጽ የመጨረሻ ዓረፍተ ነገር ጋር በደንብ እንስማማለን። በዚያ ስፍራ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርቶች አራት አእማድ በማጥላላት የመጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ለማናጋት ይታገላል። እነርሱም፡-

1. በጸጋ የሚገኝ ስርየት ወይም ደኅንነት፥

2. ስቅለት፥

3. የኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅነትና አምላክነት፥ እና

4. ሥላሴ ናቸው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚነሡ ሌሎች ተግዳሮቶች ሁሉ በእነዚህ ሥር ናቸው። እነርሱም ቢሆኑ መግለጫ የሚሹ ናቸው። ወጥነቱን ለመጠበቅ

ሲባል ተቃውሞዎቹ በሙሉ ቀደም ብሎ ከተገለጸው ከ ኤ.ኤስ.ኬ. ጄማል መጽሐፍ የተወሰዱ ናቸው። ግምገማችንን ግን አጠር ማድረግ ይኖርብናል።

## በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተደረጉ ለውጦችና ብረዛዎች

1. «ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ከጦም በቀር አይወጣም» የሚለው አሳብ በማቴዎስ 17፡21 ላይ የተጠቀሰ ሲሆን፥ ይህ ክፍል በኪንግ ጄምስ እትም እንጂ ታርሞ በተዘጋጀው «ሪቫይዝድ ቨርዥን» ውስጥ አይገኝም።

   አስቀድሞ እንደ ተገለጸው የ«ኪንግ ጄምስ ቨርዥን» መጽሐፍ ቅዱስ የ1611 ዓ.ም. ትርጉም ነው። ከዚያ በኋላ፥ በተለይም በዚህና በ19ኛው ክፍለ ዘመናት ውስጥ በ«ኪንግ ጄምስ ቨርዥን» ተርጓሚዎች ዘንድ ከነበሩት ይበልጥ አጠቃላይ የሆኑና ጥንታዊነት ያላቸው በርካታ መዛግብት መገኘት የቅጂ ስሕተቶችንና ጣልቃ-ገብ ጽሑፎችን ለይቶ ለማውጣት በተሻለ ስፍራ አስቀምጦናል።

   ጣልቃ-ገብ ጽሑፎች በመጽሐፉ ውስጥ የተጨመሩ ጽሑፎች ናቸው። ምናልባት አንድ ሲቅ የተወሰኑ ቃላትን ትርጉሞች በቅደም ተከተል፥ ማስታወሻ፥ ወይም ተመሳሳይ ምንባብ በመጽሐፉ ገጽ በጥግ በኩል ጽፎ ይሆናል። ተከታዩ ሰው መጽሐፉን በሚገለብጥበት ጊዜ ይህንኑ የጥግ ጽሑፍም ጨምሮ በመገልበጡ፥ በአዲሱ ሰነድ ውስጥ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ሆኖ ቀርቧል። በዚህ ዓይነት በተደጋጋሚ እየተገለበጠ ቆይቷል።

   በርካታ ጥንታዊ ስነዶች አንዳንዶቹ በተጨማሪ ጣልቃ የገቡትን ጽሑፎች ይዘውና ሌሎች ደግሞ ይህ ጽሑፍ ሳይኖራቸው ስለ ተገኙ፥ ሊቃውንቱ ጽሑፎቹ ጣልቃ-ገብ መሆናቸውን ወይንም በስሕተት መዘለላቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊ መምሪያ አላቸው። በመሆኑም በአዳዲሶቹ ትርጉሞች ውስጥ ተገቢ እርማቶች ተደርገዋል። ብሉይ ኪዳን ለ3000፥ አዲስ ኪዳንም ለ1400 ዓመታት ያህል በተለያዩ ማኅበረሰቦችና አገሮች፥ እንዲሁም ክፍለ ዓለማት ውስጥ በእጅ ሲገለበጡ መኖራቸውን ማወቅ ይኖርብናል።



   መሐመድ ከሞተ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ የቁርዓን የእርማት ሥራ ክርስቲያኖችና አይሁዶች የተጋፈጡአቸውን ችግሮች በተገነዘቡት በካሊፍ ኡስማን ተጠናቋል። በመጨረሻም የተለያዩት ምንባቦች ሁሉ ወድመው አንዱ የመጀመሪያ ቅጂ ብቻ ቀርቷል። ይህም የመጀመሪያ ቅጂ የስሕተቶችን ጣልቃ-ገብነት አደጋ ለማስወገድ ወዲያው ተገልብጦ ተባዝቷል («ክርስቲያኖች ሙስሊሞችን ይጠይቃሉ» የሚለውን መጽሐፍ ተመልከት)። ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ፥ ወደ ማንኛውም መጽሐፍ የሚገቡ ስሕተቶች ችግር አንድ ሰው በታሪክ ወደ ኋላ የሚሄድበት መጠን በጨመረ ቁጥር በጣሙን ይጨምራል።

   እዚህ ላይ እጠያያቂ ሆኖ የቀረበው ቁጥር የሚገኘው በ«ኮይኔ» ስነዶች «ሲ» እና «ዲ» ውስጥ ብቻ ነው፤ በሌሎች ውስጥ አይገኝም። ጣልቃ-ገብ እይደለም ለማለት ስለማይቻል፥ ይህ ቁጥር «ሪቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን» በተባለው የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ግርጌ ማስታወሻ ሆኖ ቀርቧል። ምናልባትም ከግል ልምምድ ጥቂት ቃል መጨመር ያስፈልገናል። የተጠቀሰው ምንባብ አጋንንትን ስለ ማስወጣት ይናገራል። የዚህ ምንባብ መለኮታዊ ሥልጣን ሲፈተን ይችላል፤ በራሴና በሌሎችም በርካታ ክርስቲያኖች «በሙሉ የሥራ ሂደት ውስጥ» እንደሚገኝ ሊታወቅ ችሏል። ዮሐንስ 7፡17ን እንጠቅሳለን፡-

   > «ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር፥ እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን . . . ያውቃል።»

2. በኢሳይያስ 7፡14 የ1954 ዓ.ም. የአማርኛ ትርጉም የሚከተለውን ይናገራል፡- «እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች» ይህ ልክ የ «ኪንግ ጄምስ ቨርዥን» መጽሐፍ ቀጥተኛ ትርጉም ነው።

የ «ሪቫይዝድ ቨርዥን» ትርጉም ደግሞ፡-

   «እነሆ፥ ልጃገረድ ትፀንሳለች» ይላል።

   ይህ የጣልቃ-ገብነት ወይም የመጀመሪያው መጽሐፍ እርማት ያስከተለው ልዩነት እይደለም። እዚህ ላይ ያገለገለው የዕብራይስጥ ቃል «አልማ» የሚል ሲሆን፥ ያላገባች ወጣት ሴት ማለት ነው።

በዘዳግም 22፡28 መሠረት ያላገባች ሴት ድንግል እንደ ሆነች ለመገመት እንችላለን።

3. ብዙ ጊዜ የ«ታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ» የሬቬሬንድ ዱሜለው አሳቦች ይጠቀሳሉ። በእርሱ አስተሳሰብ ምናልባት ዮሐንስ 21፡24-25 የተጨመረው ከጳውሎስ ሞት በኋላ ወንጌሉን ባስራጩትና ለእውነተኛነቱና ለተአማኒነቱ ለመመስከር በፈለጉት በኤፌሶን ሽማግሌዎች ነው። ዱሜለው በሙስሊም የመጽሐፍ ቅዱስ ሃያሲያን ዘንድ ብቻ የሚታወቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ አዘጋጅ ነው።

   ክርስቲያኖች ግምቱን ምንም ማረጋገጫ በሌላቸው መላምቶች ላይ የሚያደርግ ሰውን አስተያየት ስፍራ አይሰጡትም።

4. በሚስተር ጁማል ከቀረቡት ነጥቦች አንዳቸውም ትልቅ መዘዝ አያስከትሉም። «ወደ ሰማይም ዐረገ» (ሉቃስ 24፡51) የሚለው ሐረግ በዘመናዊ የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች ውስጥ የለም። ምክንያቱም ዛሬ ባሉት አንዳንድ መዛግብት ውስጥ (ኮዴክስ ስናይትኩስ እና ኮዴክስ ካምብሪጅ) ይህ ክፍል አልተጠቀሰም። ነገር ግን በኮዴክስ ቫትካኑስ እና በኮዴክስ አሌክሳንድሪኑስ ውስጥ ይገኛል።

   ክርስቶስ አላረገም ለሚለው ሬቬሬንድ ዱሜለው ይህ ሌላው የመቃወሚያ ነጥብ ነው። ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ባደረገው «ቃለ-ምልልስ» መጨረሻ ላይ ተአምራዊ በሆነ ሁኔታ ተሰወረ እንጂ አላረገም ባይ ነው። እውነቱ ግን ይኸው ጸሐፊ በሐዋርያት ሥራ 1፡9 ላይ አንድ ዓይነት ዓረፍተ ነገር ማስቀመጡ ነው። ስለ ሆነም የሐረጉ መዘለል በታሪክ ገጽታ፥ ወይም በመሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርት ላይ ያስከተለው ለውጥ እንደሌለ በማሳሰብ እናጠቃልላለን። በተጨማሪም፥ ይህን ክስተት ቁርዓን ራሱ ይደግፈዋል (ሱረቱ 4፡158)።

5. ከዮሐንስ 7፡53 እስከ ዮሐንስ 8፡11 ድረስ፥ በዝሙት ስለ ተያዘች ሴት የሚናገረው ታሪክ በኢታሊክስ የጽሑፍ አጣጣል ካልሆነ በቀር በዘመናዊ ትርጉሞች ውስጥ አይታይም።

   ውስጣዊና ውጫዊ መረጃዎች ምናልባት ይህ ምንባብ የዮሐንስ አንዳልሆነ ይጠቁማሉ። ይህ ምንባብ የወንጌላዊው ዮሐንስ ደቀ



መዝሙር የነበረው የሰምርኔሳዊው ፖሊካርፕ (በ69ዓ.ም. የተወለደ) ተባባሪ በሆነው የሄራፖሊስ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ በፖፒያስ የተጨመረ ይሆናል። ምንም ከጽሑፎች ማናቸውም ተጠብቀው ባይኖሩም፥ ከእርሱ የተገኙ ጥቅሶች በኡሴብዩስ ሥራዎች ውስጥ ይገኛሉ። ስለ ሆነም ይህ ምንባብ ጣልቃ-ገብ ሊሆን ከመቻሉ በተቃራኒ፥ በእውነተኛ ሐዋርያዊ የባህል ቅርስነቱ ምክንያት በክብር እንደ ተቀመጠ ብንገምት አንሳሳትም። ክርስቲያኖች በመጀመሪያዎቹ መዛግብት አቀራረብ ሐቀኞችና ታማኞች፥ እውነተኞችም ለመሆን መፈለጋቸው፥ የቅዱሳት መጻሕፍትን ሐቀኝነት ለማፈራረስ የመከራከሪያ ነጥብ ሆኖ መቅረብ እንደሌለበት ለማሳሰብ እንወዳለን። እንግዲህ ማድረግ የሚቻለው ሙስሊም ሊቃውንት በራሳቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ እንዲህ ዓይነቱን ምርምር ያድርጉ ማለት ብቻ ነው።

6. «ታላቁ ተልእኮ»ን ያካተቱት የመጨረሻዎቹ የማርቆስ ወንጌል ቃላት ከቁጥር 9-20 በእንግሊዝኛው «ሪቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን» ውስጥ የሰፈሩት በኢታሊክስ የጽሑፍ አጣጣል ነው፡-

   «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ። ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል። ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፤ የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጐዳቸውም፤ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ፤ እነርሱም ይድናሉ። «ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ። እነርሱም ወጥተው በየስፍራው ሁሉ ሰበኩ፥ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር፥ በሚከተሉትም ምልክቶች ቃሉን ያጸና ነበር።»

   አሁንም ይህን ምንባብ አንዳንድ ሰነዶች ሲመዘግቡት ሌሎች ግን ያላሰፈሩበት ሁኔታ አለ። የመጀመሪያዎቹ ቅጂ በመሆን በአጠቃላይ የተወሰዱት ኮዲስ ኤፍሬሚ ሬስክሪፕቱስ እና ቤዛ ካንታብርጅዩንሲስ ሁለቱም የማርቆስ ወንጌል የመጨረሻ ክፍልን ያካትታሉ። ይህ እስገራሚና እጅግ ጥንታዊ የሆኑት ሰነዶች መረጃ ነው። የከሪቶንያን ሰነድ አከራካሪ ከሆኑት ከአራቱ የመጨረሻ ቁጥሮች በቀር የማርቆስ ወንጌል በሙሉ የለውም። አከራካሪው ምንባብ በተጨማሪም

በሲሪያክና በፔሺቶ (ሁለተኛው ክፍል ዘመን) መጻሕፍት ውስጥ ተገኝቷል። እንዲሁም መምፍቲክ፥ ሳሂዲክ፥ ቴባይክ የሚባሉ የላይኛውና የታችኛው ግብፅ መጻሕፍትም ውስጥ ይገኛሉ። የሚያሳዝነው በቀደመው የክርስትና ዘመን፥ የመጀመሪያዎቹ መዛግብት የተጻፉት በእርጥበትና በትናንሽ ነፍሳት በቀላሉ ሊበላሽ በሚችለው በፓፒረስ መሆኑ ነው። ስለ ሆነም የተረፉልን ቁርጥራጮች ብቻ ናቸው። ነገር ግን እነዚህም ራሳቸው የኋለኞቹን መዛግብት ተአማኒነትና ተቀባይነት ይመሰክራሉ። ምክንያቱም እነዚህ ቁርጥራጮች በመቶ ከሚቆጠሩት ዓመታት በኋላ ከሚገኙት ጽሑፎች ጋር ሙሉ ለሙሉ ከተስማሙ፥ ሙሉው መጽሐፍ ተቀባይነት እንዳለው ለመገመት አያዳግትም። ጀሮምም የዚህን የወንጌል ትረካ መደምደሚያ በቨልጌት እትሙ ገልብጦታል (በ382-390 ዓ.ም. መካከል የተተረጎመ):-

«ጀሮም ይህንን ክፍል ባልተዛባ ይዞታ ባያገኘው ኖሮ፥ አለጥርጥር አያስገባውም ነበር» (በኤፍ.ሲ. ኩክ የቀረበ የአዲስ ኪዳን ትርጓሜ ቅጽ 1 ገጽ ከ302-303)።

አከራካሪ ክፍሎችን የሚያስወግዱ መዛግብት በአንድ በተወሰነ ወቅት የተገደቡ ናቸው፤ እናም ምናልባት በአንድ ሃያሲ የተቀናበሩ ይሆናሉ።

ጀስቲን ማርተር በ150 ዓ.ም. ለተጠቀሰው ምንባብ ተደጋጋሚ መግለጫ አቅርቧል። በዚያው ዘመን በዕድሜ ታናሹ የነበረው እሬኔዩስም ይህንኑ አድርጓል። እሬኔዩስ የፖሊካርፕ ተማሪ ስለ ነበር፥ የሐዋርያው ዮሐንስ መንፈሳዊ የልጅ ልጅ ነው ሊባል ይችላል።

የዚህን ምንባብ ጽኑዕነት ለመግለጽ አንድ ሰው ምናልባት በጥንታዊ መዛግብትና በጥንታዊ ሐዋርያት አባቶች ብቻ መደገፍ አያስፈልገውም ይሆናል። ሌላ መረጃ አለ፤ በሌሎች የወንጌል ክፍሎች የሚገኙ ተመሳሳይ ምንባቦችን መመልከት ይቻላል። የዚህ መልእክት ማዕከላዊ አሳብ፥ በሁሉም መዛግብት ውስጥ በመጠቀሱ እውነተኝነቱ በማያጠራጥረው በማቴዎስ 28፡19-20 ውስጥ ተደግሞ እናገኘዋለን። ዳሩ ግን የሚያምኑትን እንደሚከተሉ



የተነገሩት ምልክቶችስ? እነዚህ ምልክቶች የተገለጹና ተለይተው የሚታወቁ ናቸውን? እንዲህ ብለን ብቻ ነው ለመደምደም የምንችለው:- አዎን፤ እውነት ነው። (1ኛ) በዘመናት ሁሉ አጋንንት በክርስቲያን ደቀ መዛሙርት ወጥተዋል። ዛሬም ቢሆን ይህ ይደረጋል። (2ኛ) «በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ።» ይህ በዕለተ-ጴንጠቆስጤ ከመፈጸሙም በላይ፥ ተመሳሳይ ክስተቶች በሌሎች ስፍራዎችና ጊዜያት እንደ ተፈጸሙ የሚያሳዩ የተመዘገቡ መረጃዎች አሉን። (3ኛ) ክርስቲያን ሚሲዮናውያንን በመርዝ ለመግደል ተሞክሮ ምንም ውጤት እንዳላመጣ የሚያሳዩ ከተለያዩ ምንጮች የሆኑ ዘገባዎች አሉን። እንዲሁም ከመርከቡ ስብራት በኋላ (የሐዋርያት ሥራ 28፡3-6) ሐዋርያው ጳውሎስ በመርዛማ የእፉኝት እባብ ተነድፎ በእርሱ ላይ ምንም ጉዳት እንዳላመጣበት እንመለከታለን።

የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊም ራሱ በክርስቲያን ወጣቶች ካምፕ ውስጥ በእባብ ተነድፎ ምንም አልሆነም። በሌላ ካምፕ እያለ ልብሱን ሊለብስ ትልቅና ጥቁር ጊንጥ ከከነቴራው ውስጥ አገኘ። ነገር ግን ምንም አልሆነም። አጋጣሚ? ምናልባት። ዳሩ ግን እግዚአብሔርም የራሱ ዓላማ ነበረው። (4ኛ) ደግሞም አልፎ አልፎ የመፈወስ ስጦታ ያላቸው ክርስቲያኖች እንዳሉ ማንም የሚያውቀው ነገር ነው። ዛሬም ይህ ልምምድ ፍጹም የሚያስደንቁ ውጤቶችን እያስከተለ ይገኛል። ይህ ሁሉ መረጃ እንግዲህ እውነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደ ሆነና በዚህም ምክንያት ሊኖሩበትና ሊታመኑበት እንደሚገባ ያረጋግጣል።

«መጽሐፉ በመጀመሪያ ምንም ያህል ንጹሕ ቢሆንም፥ ባዕድ ነገር እስከ ገባ ጊዜ ድረስ ስለ ንጽሕናው የሚነገር ነገር አይኖርም» የሚለው ተደጋጋሚ ወቀሳ ተቀባይነት ያለው አይደለም።

ለምሳሌ ማንኛውም ጥንታዊ ቋንቋ ሥርዓተ-ነጥቦች፥ በምዕራፎች ወይም በቁጥሮች፥ በዐረፍተ ነገሮችና እንዲያውም በቃላት መካከል የተደረገ ክፍፍል የለውም። አራት ነጥብን፥ ነጠላ ሠረዝን፥ ትምህርተ-ጥቅስን፥ ወይም የጥያቄ ምልክትን የት እንደሚያስቀምጥ የሚወስነው ተርጓሚ በመጽሐፉ የትርጉምን ሥራ ለመሥራት ይገደዳል። ያለዚህም ማንኛውም ጥንታዊ መዝገብ፥ በጥንታዊው

ቋንቋ ላይ ልዩ ጥናት ላደረጉት ካልሆነ በስተቀር፥ ለዘመናዊ ሰው የሚገባ አይሆንም። የቁርዓኑን ዐረብኛ ጨምሮ ባዕድ ነገር እንዳልገባበት የሚነገርለት ጥንታዊ ጽሑፍ ሲኖር አይችልም። ከቁርዓን መጠናቀር በኋላ በዐረብኛ ቋንቋ ውስጥ የተጨመሩትን ምልክቶችና አናባቢዎች መመልከት ብቻ ይበቃናል።

አንድ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ካመነና ከተለወጠ በኋላ በሕይወቱ ስለሚያልፈው የሚለወጥ የእግዚአብሔር ኃይል ማንም ክርስቲያን እማኝ ሊመስክር ይችላል። ዳሩ ግን በሙስሊሞች አመለካከት፥ ይህ መጽሐፍ በሰው እሳብ ክምችት የተዋጡ ጥቂት የመለኮታዊ መልእክት ቅሬታዎችን ብቻ ይዟል።

በክርስትና ላይ የሚሄይሱ ሙስሊሞች፡-

«በሰውና በእንስሳ መካከል ያለው ልዩነት፥ ሰው ለማሰብ የማገናዘብ ብቃት ስላለው ነው። እንስሳ በደመነፍስ ይንቀሳቀሳል እንጂ አያገናዝብም። ግንዛቤ ሰውን ከእንስሳ የሚለየው ነው» በማለት አበክረው ይናገራሉ።

በዚህ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት ክርስቲያኖች አያገናዝቡም፤ አያስቡም የሚል ነው።

ቅን የሆነ አንባቢ በዚህ ጉዳይ ወደ ራሱ ማጠቃለያ ላይ ከመድረሱ በፊት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የቀረበን አንድ ተወዳጅ ትርጓሜ ከቁርዓን ትርጓሜ ጋር እንዲያወዳድር እናበረታታለን።

## ቅራኔዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

በሙስሊሞች የሚሰነዘሩት በርካታ ጥያቄዎች የሚያተኩሩት ለተመሳሳይ ሁኔታዎች በዋሉት ስሞችና ቁጥሮች ልዩነቶች ላይ ነው። እነዚህ መጽሐፉን የገለበጡ ሰዎች ስሕተቶች ቢሆኑም፥ መልእክቱን በተመለከተ ምንም ለውጥ የማያስከትሉ ናቸው።

በ2ኛ ዜና መዋዕል 36፡9 ላይ ኢዮአቄም መንገሥ ሲጀምር ስምንት ዓመቱ ነበር፤ ነገር ግን በ2ኛ ነገሥት 24፡8 ላይ አሥራ ስምንት ዓመቱ ነበር።



በ2ኛ ዜና መዋዕል 22፡2 ላይ አካዝያስ መንገሥ ሲጀምር አርባ ሁለት ዓመቱ ነበር፤ በ2ኛ ነገሥት 8፡26፥ ሃያ ሁለት ዓመቱ ነበር።

በሚከተሉት ስፍራዎች ተመሳሳይ ሁኔታዎች ይስተዋሉ ይሆናል፡-

2ኛ ዜና መዋዕል 4፡5 ከ1ኛ ነገሥት 7፡26 ጋር ሲነጻጸር

2ኛ ዜና መዋዕል 14፡3፤ 17፡6 ከ1ኛ ነገሥት 15፡14፤ 22፡43 ጋር ሲነጻጸር

2ኛ ዜና መዋዕል 9፡25 ከ1ኛ ነገሥት 4፡26 ጋር ሲነጻጸር

1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡16 ከ1ኛ ነገሥት 8፡12፤ መዝሙር (18)፡11 ጋር ሲነጻጸር

ዮሐንስ 1፡18 ከዘጸአት 33፡11 ጋር ሲነጻጸር

2ኛ ሳሙኤል 24፡24 ከ1ኛ ዜና መዋዕል 21፡25 ጋር ሲነጻጸር

2ኛ ሳሙኤል 8፡4 ከ1ኛ ዜና መዋዕል 18፡4 ጋር ሲነጻጸር

2ኛ ሳሙኤል 10፡18 ከ1ኛ ዜና መዋዕል 19፡18 ጋር ሲነጻጸር

2ኛ ሳሙኤል 24፡1፥ 9፥ 13፥ 24 ከ1ኛ ዜና መዋዕል 21፡1፥ 5፥ 11፥ 12፥ 22፥ 10 እና ዘፍጥረት 38፡7 ከማቴዎስ 1፡3 ጋር ሲነጻጸር

ማንኛውም ስፍራ የሚሰጠው የታሪክ ሰው በምንም ዓይነት መንገድ በዚህ ዓይነቱ ስሕተት ምክንያት መዛግብቱ ትአማኒነቱ እንደጐደላቸው፥ ወይም እንደ ተበላሹ ተቆጥረዋል ብሎ ሊደመድም አይችልም። በተጨማሪም፥ ከእነዚህ ስሕተቶች ውስጥ ማናቸውም ስፍራ የሚሰጣቸው ወይም ዋናውን ጉዳይ የሚነኩ አይደሉም።

ዝርዝር ወቀሳዎች እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡-

1. ለ«ዘመናዊ የሥነ-መለኮት አዋቂዎች» የፍጥረትና የጥፋት ውኃ ዘገባዎች «የይዘትና የስልት ልዩነቶቻቸው ሁለት ደራሲያንን በሚያጋልጡ» በሁለት ትረካዎች ላይ እና ዘገባዎቹን በመጠኑ መርምሮ ባገጣጠማቸው አርማ የማጣመር ሥራ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። በዘፍጥረት 6፡19 እግዚአብሔር ኖኅን «ከሕያው ሁሉ

ሁለት ሁለት እያደረግህ ወደ መርከብ ታገባለህ፤ ተባትና እንስት ይሁን» ብሎ እንዳዘዘ እናነባለን። ሃያሲው ሁለተኛው ደራሲ፥ ኖህ

«ከንጹሕ እንስሳ ሁሉ ሰባት ሰባት ተባትና እንስት፥ ንጹሕ ካልሆነ እንስሳም ሁለት ሁለት ተባትና እንስት» (ዘፍጥረት 7፡2-3) ከጥፋት ውኃ እንዲያድን ታዟል።

ከዚህ ላይ ያለውን ቅራኔ የሚፈልጉት ሙስሊሞች በምዕራፍ 8፡20 ላይ እነዚህ ትርፍ እንስሳት ለሚከተለው አገልግሎት እንደ ዋሉ አላስተዋሉም፡-

«ኖኅም ለእግዚአብሔር መሠውያን ሠራ፤ ከንጹሕም እንስሳ ሁሉ ወሰደ፤ በመሠውያውም ላይ መሥዋዕትን አቀረበ።»

ያ ዐረፍተ ነገር የከረረውን ቅራኔ ለማብራራት መቻል አለበት።

2. በሌላም «ቅራኔ» ውስጥ የከፍሉን አሳብ አለማስተዋል ኀልቶ እናገኛለን።

«የሚፈልገውም ያገኛል» (ማቴዎስ 7፡8)።

ከዚህ ክፍል ጋር እንደሚጋጭ የተጠቀሰው ክፍል በምሳሌ 1፡28 ላይ ይገኛል፡- «የዚያን ጊዜ ይጠሩኛል፥ እኔ ግን አልመልስም፤ ተግተው ይሹኛል፥ ነገር ግን አያገኙኝም።» ሃያሲው ሆን ብሎ ያስቀረው ምክንያት የሚከተለው ነው፡-

«እውቀትን ጠልተዋልና፥ እግዚአብሔርንም መፍራት አልመረጡምና፤ ምክሬን አልፈቀዱምና፥ ዘለፋዬንም ሁሉ ንቀዋልና፤ ስለዚህ የመንገዳቸውን ፍሬ ይበላሉ፥ ከራሳቸው ምክር ይጠግባሉ» (1፡29-31)።

ኢሳይያስ 1፡15፡-

«እጃችሁንም ወደ እኔ ብትዘረጉ ዓይኔን ከእናንተ እሰውራለሁ፤ ልመናንም ብታበዙ አልሰማችሁም።» የተዘለለው ምክንያት «እጆቻችሁ ደም ተሞልተዋል» የሚል ነው።

መዝሙር 18፡41፡-



«ጮኹ፥ የሚረዳቸው አልነበረም፤ ወደ እግዚአብሔርም ጮኹ፤ አልሰማቸውም።» ለዚህ «ግጭት» የተዘለለው ምክንያት «ከሕዝብ ክርክር ታድነኛለህ» (18፡43) የሚለው ነው።

ከዚህ ላይ የምንመለከተው ከቅንዓት በቀር ያለ ምንም ሌላ ምክንያት ዳዊትን ለመግደል በመሞከር በደል ስለ ፈጸሙት ጠላቶቹ ነው። እነርሱም በእግዚአብሔር አልተደመጡም፤ ጻድቁ ዳዊት ግን ተደምጧል። እግዚአብሔርን የማያገኙት ሰዎች የእግዚአብሔርን መንገድና ትእዛዛት ቸል ብለው የተዉት እንደ ሆኑ አንባቢው ይረዳል።

በኢሳይያስ 1፡16-20 ላይ የተሰጠው ቅጽበታዊ መፍትሔ፡-

«ታጠቡ ሰውነታችሁንም አንጹ፤ የሥራችሁን ክፋት ከዓይኔ ፊት አስወግዱ፤ ክፉ ማድረግን ተዉ፥ መልካም መሥራትን ተማሩ፥ ፍርድን ፈልጉ ... ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፤ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች። እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ፥ የምድርን በረከት ትበላላችሁ፤ እምቢ ብትሉ ግን ብታምፁም፥ ሰይፍ ይበላችኋል፤ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና።»

3. ለከነዓን አገር መያዝም የሚሠራው ተመሳሳይ መምሪያ ነው። ሃያሲያችን እግዚአብሔርን «ጨካኝ፥ ምሕረት የለሽ፥ ኃይለኛ አጥፊ» ብሎ ለመጥራት ይመርጣል።

ወደ ዋናው ቁም ነገር እንመልከት። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ምንባቦች (ኤርምያስ 13፡14፤ ዘዳግም 7፡16፤ 1ኛ ሳሙኤል 15፡3፤ ወዘተ.) ሁሉ አንድ የጋራ ነገር አላቸው፡- የከነዓናውያን ውድመት። እግዚአብሔር ይህን ትእዛዝ የሰጠበት ምክንያት ሕዝቡን ለመጠበቅ ሲል ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች እስራኤልን ለማጥፋት በከፍተኛ ደረጃ ታጥቀው ተነሥተው ነበር። የመጨረሻ ዓላማቸውም ከእስራኤላውያን ዘንድ መምጣት የነበረበትን መሢሕ የመከላከልና የእግዚአብሔር ቃል እንዳይፈጸም የማድረግ ገጽታ ነበር። በዘዳግም 20፡16-18 የሚከተለውን እናነባለን፡-

«...ምንም ነፍስ አታድንም። ነገር ግን ለአማልክቶቻቸው ያደረጉትን ርኩሰት ሁሉ ታደርጉ ዘንድ እንዳያስተምሩአችሁ፥ በአምላካችሁም በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንዳትሠሩ፥ አምላክህ እግዚአብሔር እንዳዘዘህ ... ፈጽመህ ታጠፉቸዋለህ።»

እንደሚገባኝ የሁሉን አዋቂነቱ ገጽታ የሆነውን የእግዚአብሔርን አስቀድሞ የማወቅ ሁኔታ ማለቱና በመሆኑም እርሱን ባለማወቅ ወይም በከፋት እነዚህን የመከራከሪያ ነጥቦች ለሚያቀርቡ ሁሉ በሚሠራው ወይንም በሚያዘውና በሚተወው ነገር ጣልቃ መግባቱ አጉል ድፍረት መሆኑን ማሳሰቡ ያስፈልጋል። እግዚአብሔር አማካሪዎችን አይፈልግም። ሥራችንም እግዚአብሔርን መተቸት ሳይሆን፥ የቃሉን ተአማኒነት ማረጋገጥና በእርሱም መኖር ነው፤ እንዲሁም ከተግሣጹ የምንማረውን ነገር ማግኘት ነው።

4. በተወሰኑ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ውስጥ እግዚአብሔር በሚቃጠል መሥዋዕትና በሌሎችም መሥዋዕቶች እንደሚደሰት ተገልጾልናል። እንዲሁም እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ያዝዛል ብለን ልናክል እንችላለን፡-

«የሥጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና፤ ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያልና፤ በመሠውያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት» (ዘሌዋውያን 17፡11)።

ሃያሲው ግን በሌሎች ምንባቦች ውስጥ እግዚአብሔር በሚቃጠሉ መሥዋዕቶች እንደማይደሰት በመመልከት ሁለቱ አቋሞች እንደሚቃረኑ ይናገራል። አሁንም ዓውደ ንባቡ እውነቱን ይገልጽልናል። ንስሐ በማይገቡና በማይታዘዙ ሰዎች የሚቀርበው መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አስጸያፊ ነው፡-

«ምናምንቴውን ቁርባን ጨምራችሁ አታምጡ፤ ዕጣን በእኔ ዘንድ አስጸያፊ ነው፤ መባቻችሁንና ሰንበታችሁን በጉባኤም መሰብሰባችሁን አልወድድም፤ በደልንም የተቀደሰውንም ጉባኤ አልታገሥም። መባቻችሁንና በዓላቶቻችሁን ነፍሴ ጠልታለች፤ ሸክም ሆነውብኛል፥ ልታገሣቸውም ደክሜያለሁ» (ኢሳይያስ 1፡13-14)።



«ዕውር መሥዋዕትንም ስታቀርቡ ይህ ክፉ አይደለምን? አንካሳውንና የታመመውን ስታቀርቡ ይህ ክፉ አይደለምን? ... በመሠውያዬ ላይ እሳትን በከንቱ እንዳታቃጥሉ ከእናንተ ዘንድ ደጅ የሚዘጋ ሰው ምነው በተገኘ! በእናንተ ደስ አይለኝም፥ ቁርባንንም ከእጃችሁ አልቀበልም ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ... በቅሚያ የያዛችሁትንም እንካሳውንም የታመመውንም አቅርባችኋል፤ እንዲሁ ቁርባንን ታመጣላችሁ፤ በውኑ ከእጃችሁ ይህን ልቀበለውን? ይላል እግዚአብሔር። እኔ ታላቅ ንጉሥ ነኝና፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር... በመንጋው ውስጥ ተባት እያለው ለጌታ ተስሎ ነውረኛውን የሚሠዋ ሸንጋይ ሰው ርጉም ይሁን» (ሚልክያስ 1፡8፥10፥ 13፥14)።

«በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ፥ መታዘዝ ከመሥዋዕት፥ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል። ዓመፀኝነት እንደ ምዋርተኛ ኃጢአት፥ እልከኝነትም ጣዖትንና ተራፊምን እንደ ማምለክ ነው» (1ኛ ሳሙኤል 15፡22-23)።

5. አንዳንድ ተቃውሞዎች በእግዚአብሔርና ከሰው ጋር በሚያደርጋቸው ነገሮች ላይ የተመሠረቱ ናቸው። እግዚአብሔር በጥቂቶች ተሰምቷል፤ ታይቷልም፡-

«እግዚአብሔርም ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር ፊት ለፊት ከሙሴ ጋር ይነጋገር ነበር» (ዘጸአት 33፡11)።

«እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ፡- ወዴት ነህ? አለው። እርሱም አለ፡- በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ ተሸሸግሁም» (ዘፍጥረት 3፡9-10)።

«ያዕቆብም፡- እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ፥ ሰውነቴም ድና ቀረች ሲል የዚያን ቦታ ስም ጵኒኤል ብሎ ጠራው» (ዘፍጥረት 32፡30)።

«እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፥ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር» (ኢሳይያስ 6፡1)።

እንደገናም የሚከተለውን እናነባለን፡-

«መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም» (ዮሐንስ 1፡18)።

«ድምፁን ከቶ አልሰማችሁም» (ዮሐንስ 5፡37)።

«ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም» (ዘጸአት 33፡20)፥ ወዘተ፨

እነዚህ ስለ አዳም፥ ሙሴና ኢሳይያስ የሚናገሩ ዐረፍተ ነገሮች ሥዕላዊ የአገላለጽ ባሕርይ እንዳላቸው አድርገን ነው የምንወስዳቸው። እግዚአብሔር መንፈስ ስለ ሆነ ልክ እንደ ዘፍጥረት 18፡1-2፤ 32፡24-28 ና 14፡18-20 ራሱን ካልገለጸ በሥጋ ሊታይ አይችልም። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥም ሰው እግዚአብሔርን ራሱን አይደለም የሚያየው፥ የእርሱን መገለጥ እንጂ። እግዚአብሔርን በ«ማየቱ» ረገድ፥ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች «በዚህ መንገድ የእግዚአብሔርን ክንድ አየን»፥ ወይም «በዚያ ውስጥ እግዚአብሔር ሲሠራ ተመልክተናል» ሲሉ አልሰማንም? በቁርዓንም ውስጥ ተመሳሳይ መመሪያ ተቀምጦ እንመለከታለን፡-

«እርሱ ያ በአንተ ላይ መጽሐፉን ያወረደ ነው፤ ከርሱ (ከመጽሐፉ) ግልጽ የኾኑ አንቀጾች አልሉ፤ እነሱ የመጽሐፉ መሠረቶች ናቸው፤ ሌሎችም ተመሳሳዮች አልሉ፤ እነዚያማ በልቦቻቸው ውስጥ ጥመት ያለባቸው ሰዎች፥ ማሳሳትን ለመፈለግና ትችቱን ለመፈለግ ከርሱ የተመሳሰለውን ይከታተላሉ። (ትክክለኛ) ትችቱን አላህ ብቻ እንጂ ሌላ አያውቀውም። በዕውቀትም የጠለቁት በርሱ አምንናል፤ ሁሉም ከጌታችን ዘንድ ነው፥ ይላሉ። የአእምሮ ባለቤቶችም እንጅ (ሌላው) አይገሠጽም» (ሱረቱ 3፡7)።

ከላይ የቀረቡት ምንባቦች ቃል በቃል መተርጐም የዘፍጥረትና የዘጸአት ጸሐፊ በአንድ ምዕራፍ ውስጥ (ዘጸአት 33) እንዲህ ያሉ የሚጋጩ ዐረፍተ ነገሮች በመጻፉ ሰነፍ እንደ ሆነ ያሳስባል። ይህ ሰው ሙሴ ነበር። ከዚህም ባሻገር፥ እግዚአብሔር እንደዚህ በግልጽ የመታየቱን ጉዳይ ጠቅላላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይቃወመዋል።

6. ሃያሲው ኤልሻዳዩ አምላክ እንደማይችል የተጠቀሰበትን የምንባብ ክፍል ያናንቃል፤



«በሸለቆው የሚኖሩት ግን የብረት ሰረገሎች ነበሩአቸውና ሊያወጣቸው አልቻለም» (መሳፍንት 1፡19)።

ዳሩ ግን ሃያሲው በጥቅሱ የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ፡-

«እግዚአብሔርም ከይሁዳ ጋር ነበረ፤ ይሁዳም ተራራማውን አገር ወረሰ» የሚለውን አላጤነም።

«ይሁዳም» የሚለው የዐረፍተ ነገሩ ሁለተኛ ክፍል «አልቻለም» ሲል ቃሉ በቀጥታ ይሁዳን እንጂ ጌታን አያመለክትም። ስለዚህም በብረት ሰረገሎቹ ምክንያት ይሁዳ የሸለቆውን ነዋሪዎች ሊያስለቅቅ አልቻለም። እግዚአብሔር ከአንድ ሰው ጋር ሆነ ማለት የግድ ነገሮች ሁሉ ያለ ምንም ችግር ይከናወናሉ ማለት አይደለም። (ለምሳሌ፡- እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የነበረው ዮሴፍ ለባርነት ተሸጧል፤ ታስሯልም። እግዚአብሔር ግን ይህንን ሁኔታ ወንድሞቹን ለማዳን ተጠቅሞበታል። የክርስቶስም ሞት ሽንፈት ይመስል ነበር፤ ዳሩ ግን ያ ከሁሉም የላቀ ድል ነበር።) እንዲሁም በሮሜ 8፡38 ላይ፡-

«ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥ ከፍታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረታትም ቢሆን፥ ...ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ» የሚለውን እናነባለን።

በሮሜ 8፡28 ላይም፡-

«እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን» ይላል።

ያም ጳውሎስ በዘመኑ ለነበሩት አሕዛብ የእግዚአብሔርን መልእክት በሚያስተላልፍበት ጊዜ ከተናገረው ጋር ይስማማል፡-

«እኛ ግን የተዋረድን ነን። እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን፥ እንጠማለን፥ እንራቆታለን፥ እንጐስማለን፥ እንከራተታለን... ሲሰድቡን...ሲያሳድዱን... ክፉ ሲናገሩን እንማልዳለን» (1ኛ ቆሮንቶስ 4፡10-13)።

«በሁሉ እንገፋለን ... እናመነታለን ... እንወድቃለን ...» (2ኛ ቆሮንቶስ 4፡8-9)።

የዚህ ማብራሪያ (ቁጥር 7)፡-

«የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ (የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር ክብር) በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን።»

እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለሕጉና ለተስፋ ቃሎቹ ራሱን በማስገዛቱ ሥልጣኑ እንደ ተወሰነ ለማከል እንወዳለን። እግዚአብሔር ሊዋሽ ወይም የተሰፋ ቃሉን ሊያጥፍ ስለማይችል፥ ሥልጣኑን ከፍሎ ለሰው ይሰጣል። ሰውም ቃሉን እየታዘዘ እግዚአብሔርን በተስፋ ቃሎቹ እንደሚጸና መጠባበቅ ይችላል።

7. ሌሎች ተቃውሞዎች ቅዱሳት መጻሕፍት እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ የክፉ ነገር ጀማሪ እንደ ሆነና በሌላ ጊዜ ደግሞ እንዳልሆነ የሚናገሩ ተቃራኒ አሳቦች እንዳሉበት ይጠቅሳሉ። እዚህ ላይ ያለው ችግር የፍልስፍና ጉዳይ ስለ ሆነ፥ ምክንያት በማቅረብ መፍትሔ ሊገኝለት አይችልም። እግዚአብሔር የሁሉም ፈጣሪ ከሆነ ዲያብሎስንም ፈጥሮታል። በዚህም መሠረት የክፉ ነገሮች ጀማሪ ነው ማለት ነው። በመሆኑም ለእነዚህ ሰው ለሚሠራቸው ክፉ ሥራዎች እግዚአብሔር ተጠያቂ መሆን ነበረበት፤ እናም ሰውን ለሥራዎቹ ተጠያቂ የሚያደርግ ከሆነ፥ ፍትሕ-እልባ የሆነ ተግባር መፈጸሙ ነው። ነገር ግን እንዲህ አይደለም። እግዚአብሔር ሰይጣንን አልፈጠረውም። ሰይጣን የተፈጠረው የብርሃን መልአክ ሉሲፈር ሆኖ ነበር። በኋላ ግን እግዚአብሔርን ለመገልበጥና በዙፋኑም ላይ ለመቀመጥ (ሰይጣን ማለት ተቃዋሚ ወይም ከሳሽ ማለት ነው) በማሴር ለማመፅ ወሰነ። ይህ ሁሉ ከሰብአዊ አእምሮ በላይ ቢሆንም አንድ ግልጽ የሆነ ነገር አለ። ይኸውም የብርሃኑ መልአክና ሰው ሁለቱም የተፈጠሩት ነጻ ፈቃድ ተሰጥቶአቸው ነው። ፍቅር ከኃይል አገዛዝ ውስጥ ስለማይፈልቅ ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆን ወይም ላለመሆን የመወሰን ነጻነት ነበራቸው። ስለ ሆነም እርሰ በርሳቸው እንደሚቃረኑ የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡9-12 ብርሃን መመርመር አለብን፡-

«ይድኑ ዘንድ የእውነትን ፍቅር ስላልተቀበሉ ለሚጠፉ፥ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች፥ በሐስተኞች ድንቆችም፥ በዓመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው። ስለዚህም ምክንያት፥ በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመፅ ደስ



ይላቸው የነበሩ ሁሉ ፍርድን እንዲቀበሉ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል።»

ሰው መከተል የፈለገውን ውሸት እንዲያምን የፈቀደለት እግዚአብሔር ነው።

በ(ሀ) ያሉት የምንባብ ክፍሎች ስብስብ በ(ለ) ካሉት የምንባብ ሰብስቦች ይቃረናል ተብሎ ይነገራል፡-

ሀ. «የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፤ ነፍስን ይመልሳል፤

የእግዚአብሔር ምስክር የታመነ ነው፤ ሕፃናትን ጠቢባን ያደርጋል።

የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው፥ ልብንም ደስ ያሰኛል፤

የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው፥ ዓይንንም ያበራል» [መዝሙር (19)፡7-8]።

«እግዚአብሔርስ የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለምና» (1ኛ ቆሮንቶስ 14፡33)።

«እርሱ አምላክ ነው፤ ሥራውም ፍጹም ነው፤መንገዱም ሁሉ የቀና ነው፤የታመነ አምላክ፥ ክፋትም የሌለበት፥ እርሱ እውነተኛና ቅን ነው» (ዘዳግም 32፡4)፤ እና

«ማንም ሲፈተን፡- በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና፤ እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም» (ያዕቆብ 1፡13)።

ለ. «ደግሞም መልካም ያልሆነውን ሥርዓት በሕይወት የማይኖሩበትንም ፍርድ ሰጠኋቸው» (ሕዝቅኤል 20፡25)።

«ከልዑል አፍ ክፉና መልካም ነገር አይወጣምን?» (ሰቆቃው ኤርምያስ 3፡38)።

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እነሆ ክፉ ነገር እፈጥርባችኋለሁ፥ አሳብንም አስብባችኋለሁ» (ትንቢተ ኤርምያስ 18፡11)።

«ወይስ ክፉ ነገር በከተማ ላይ የመጣ እንደ ሆነ ያደረገው እግዚአብሔር አይደለምን?» (አሞጽ 3፡6)።

በሚስተር ጁማል ችላ ወደተባሉት ወደ እነዚህ ቁጥሮች ዓውደ ንባቡን መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል።

ሚስተር ጁማል ሰቆቃው ኤርምያስ 3፡38ን የሚጠቅሱት፡-

«ከልዑል አፍ ክፉና መልካም ነገር አይወጣም» በማለት ነው። ሙሉው ምንባብ ግን እንደሚከተለው ይነበባል፡-

> «ጌታ ያላዘዘውን የሚልና የሚፈጽም ማነው? ከልዑል አፍ ክፉና መልካም ነገር አይወጣምን? ሕያው ሰው የሚያጉረመርም፥ ሰው ስለ ኃጢአቱ ቅጣት የሚያጉረመርም ስለ ምንድር ነው? መንገዳችንን እንመርምርና እንፈትን፥ ወደ እግዚአብሔርም እንመለስ።
>
> ልባችንን ከእጃችን ጋር በሰማይ ወዳለው ወደ እግዚአብሔር እናንሣ። በድለናል ዐምፀናልም፥ አንተም ይቅር አላልህም። በቁጣ ከደንኸን አሳደድኸንም፤ ገደልኸን፥ አልራራህም። ጸሎት እንዳያልፍ ራስህን በደመና ከደንህ። በአሕዛብ መካከል ጉድፍና ውዳቂ አደረግኸን» (ሰቆቃው ኤርምያስ 3፡37-45)።

ስለዚህ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣው ክፉ ነገር የኃጢአት ቅጣት ነው። ይህም ለሰው ሥራዎች ትክክለኛ የሆነ ሽልማት ነው። በሌሎች የምንባብ ክፍሎችም ተመሳሳይ ነገር እንመለከታለን፡-

> «በዚህም ጊዜ፡- መዓቴን አፈስስባቸዋለሁ ቁጣዬንም በምድረ በዳ አፈጽምባቸዋለሁ አልሁ። ነገር ግን እጄን መለስሁ፥ በፊታቸውም ባወጣኋቸው አሕዛብ ፊት ስሜ እንዳይረክስ ብዬ ስለ ስሜ ሠራሁ። ደግሞም ወደ አሕዛብ እበትናቸው ዘንድ፥ በአገሮችም እበትናቸው ዘንድ በምድረ በዳ ማልሁባቸው፤ ፍርዴን አላደረጉምና፤ ሥርዓቴንም ጥሰዋልና፤ ሰንበታቴንም አርክሰዋልና፤ ዓይናቸውም የአባቶቻቸውን ጣዖታት ተከትለዋልና ... እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ እንዲያውቁ አጠፋቸው ዘንድ፥ ማኅፀን የሚከፍተውን ሁሉ በእሳት ባሳለፉ ጊዜ፥ በመባቸው አረከስኋቸው።
>
> «ስለዚህ፥ የሰው ልጅ ሆይ፥ ለእስራኤል ቤት ተናገር፥ እንዲህም በላቸው፡- ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- በዚህም ደግሞ አባቶቻችሁ ባደረጉት ዓመፅ አስቆጡኝ ... ስለዚህ ለእስራኤል ቤት እንዲህ በላቸው፡- ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እንደ



> አባቶቻችሁ ልማድ ትረክሳላችሁን? ርኩሰታቸውንም ተከትላችሁ ታመነዝራላችሁን?» (ሕዝቅኤል 20፡21-24፥26፥27፥30)።

«የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ይህ ሸክላ ሠሪ እንደሚሠራ በውኑ እኔ በእናንተ ዘንድ መሥራት አይቻለኝምን? እነሆ፥ ጭቃው በሸክላ ሠሪ እጅ እንዳለ፥ እንዲሁ እናንተ በእኔ እጅ አላችሁ። ስለ ሕዝብ ስለ መንግሥትም እነቅል አፈርስም አጠፋም ዘንድ በተናገርሁ ጊዜ፥ ይህ ስለ እርሱ የተናገርሁበት ሕዝብ ከክፋቱ ቢመለስ፥ እኔ አደርግበት ዘንድ ካሰብሁት ክፉ ነገር እጸጸታለሁ። ስለ ሕዝብም ስለ መንግሥትም እሠራውና እተክለው ዘንድ በተናገርሁ ጊዜ፥ በፊቴ ክፉን ነገር ቢያደርግ፥ ቃሌንም ባይሰማ፥ እኔ አደርግለት ዘንድ ስለ ተናገርሁት መልካም ነገር እጸጸታለሁ። አሁን እንግዲህ ለይሁዳ ሰዎችና በኢየሩሳሌም ለሚቀመጡ፡- እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እነሆ፥ ክፉ ነገር እፈጥርባችኋለሁ፥ አሳብንም አስብባችኋለሁ፤ አሁንም ሁላችሁ ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ፥ መንገዳችሁንና ሥራችሁንም አቅኑ ብለህ ተናገራቸው። እነርሱ ግን፡- እንጨክናለን፤ አሳባችንን ተከትለን እንሄዳለን ሁላችንም እንደ ክፉው ልባችን እልከኝነት እናደርጋለን አሉ» (ኤርምያስ 18፡5-12)።

«የእስራኤል ልጆች ሆይ፥ እግዚአብሔር በእናንተ፥ ከግብጽ ምድር ባወጣሁት ወገን ሁሉ ላይ የተናገረውን ይህን ቃል ስሙ፤ እንዲህም ብሎአል፡- እኔ ከምድር ወገን ሁሉ እናንተን ብቻችሁን አውቄአችኋለሁ፤ ስለዚህ ስለ ኃጢአታችሁ ሁሉ እበቀላችኋለሁ። በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ በአንድነት ይሄዳሉን? ወይስ አንበሳ የሚነጥቀው ነገር ሳያገኝ በጫካ ውስጥ ያገሣልን? ወይስ የአንበሳ ደቦል አንዳች ሳይዝ በመደቡ ሆኖ ይጮኻልን? ወይስ ወፍ፥ አጥማጅ ከሌለው፥ በምድር ላይ በወጥመድ ይያዛልን? ወይስ ወስፈንጠር አንዳች ሳይዝ ከምድር ይፈነጠራልን? ወይስ በከተማ ውስጥ መለከት ሲነፋ ሕዝቡ አይፈራምን? ወይስ ክፉ ነገር በከተማ ላይ የመጣ እንደ ሆነ ያደረገው እግዚአብሔር አይደለምን? በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ምስጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም» (አሞጽ 3፡1-7)።

8. «መልካሙን ሥራችሁን (እንዲያዩ)...ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ» (ማቴዎስ 5፡16) የሚለው፥
«ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ» (ማቴዎስ 6፡1) ከሚለው ጋር ተቃራኒ ሆኖ ቀርቧል።

ሃያሲው በኢየሱስ «የተራራው ስብከት» ውስጥ በሚገኙት በእነዚህ በሁለቱ ዐረፍተ ነገሮች መካከል ግጭት ይመለከታል። እንደ ተለመደው በዚህ ስፍራም ዓውደ ምንባቡን ቸል በማለት ሲተወው እንመለከታለን። ምክንያቱም ከአንደኛው ዐረፍተ ነገር፡-

«በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ» የሚለውን ተከትሎ የሚመጣ ነው።

ኢየሱስ ስለ ሁለት የተለያዩ ጉዳዮች ነው የተናገረው፡-

1) ሥራዎቻችን እግዚአብሔርን ማክበር እንዳለባቸው፥
2) እነዚህንም ሥራዎች ከሰዎች ዘንድ ምስጋና ለማግኘት ብለን መሥራት እንደሌለብን።

ስለሆነም ምንም ግጭት አይፈጠርም።

9. ኢየሱስ «ሥጋን የሚገድሉትን አትፍሩ» (ሉቃስ 12፡4) ብሎ ቢያስተምርም በተግባር ሲታይ እርሱ ራሱ እንደ ፈራ ተነግሮናል። ምክንያቱም፥ «ከዚህም በኋላ ኢየሱስ አይሁድ ሊገድሉት ይፈልጉ ስለ ነበር በይሁዳ ሊመላለስ አይወድም ነበርና በገሊላ ይመላለስ ነበር» (ዮሐንስ 7፡1) የሚል እናነባለን።
ጊዜው ገና አልደረሰም ነበር። ስለ ሞቱ ብዙ ጊዜ ተንብዮአል፡-

«ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር» (ማቴዎስ 16፡21)።

«ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና ... እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም» (ዮሐንስ 10፡17-18)።



«የሚወጣበትም ወራት በቀረበ ጊዜ፥ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፊቱን አቀና ...» (ሉቃስ 9፡51) (በዚያ የሚጠብቀው ምን እንደ ሆነ ያውቅ ነበር!)።

ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚሄድ ባስታወቀ ጊዜ (ዮሐንስ 11፡15-16)፥ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ «ከእርሱ ጋር እንሞት ዘንድ እኛ ደግሞ እንሂድ» ብሏል። አሁንም ግጭቱ የተስተዋለው ምንም የሚቃረን አሳብ በሌለበት ስፍራ ነው። ክርክር ያስነሣው ክፍል የሚገልጸው ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ እንደ ፈራ ሳይሆን፥ በዚያ በተወሰነ ደረጃ ጊዜው ገና እንዳልደረሰ ነው። እንዲሁም ሃያሲያኑ ስለ ጌቴሰማኔ መጥቀሱን ይዘነጋሉ። በዚያ ስፍራ ክርስቶስ፡-

«ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች ... አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ» (ማቴዎስ 26፡38-39)

እንዳለ መጽሐፍ ቅዱስ ይዘግባል። ዳሩ ግን ከዚያ በመቀጠል፡-

«ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን» ብሏል።

የመስቀል ሞቱን በሚያስብበት ጊዜ ክርስቶስ እጅግ እንደ ታወከ ግልጽ ነው። ይህም እንደ ማንኛውም ሰው ሥቃይ ይሰማው ስለ ነበረ ነው።

10. በዘፍጥረት 17፡10 ላይ ግርዘት ታዞአል፡-
«በእኔና በአንተ መካከል፥ ከአንተም በኋላ በዘርህ መካከል የምትጠብቁት ቃል ኪዳኔ ይህ ነው፤ ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ።»
ይህም በገላትያ 5፡2 ላይ ጳውሎስ «ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም» በማለት ከተናገረው ጋር የሚቃረን ይመስላል።

አሁንም ግልጽ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ- መለኮት እውቀት እጦት ይስተዋላል። መገረዝን እንደ ምልክት አድርጎ ያጠቃለለው ቃል ኪዳን የተደረገው ከአብርሃምና ከዘሩ ጋር ነው። ይህ ቃል ኪዳን ወደ አሕዛብ መንደር የዘለቀበት ጊዜ የለም። ዳሩ ግን በእጅ የተደረገ የሥጋ መገረዝ በእግዚአብሔር ፊት በቂ እንዳልሆነ በብሉይ ኪዳን ውስጥም እንኳ በተደጋጋሚ ተገልጾ እንመለከታለን።

እግዚአብሔር የሕዝቡ ልብ እንዲገረዝ ደግሞ ደጋግሞ ጠይቆአል። ይህም ማለት ቃል ኪዳኑ ሜዳዊ ሥርዓት ሳይሆን፥ የሰውን ልብና ነፍስ ሊነካ የሚገባው የውስጥ ነገር ነው ማለት ነው። አዲሱ የተሰፋ ቃል ወይም እዲሱ ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔርን የምሕረት ስጦታ ለመቀበል ለሚፈልጉ ሁሉ በሩን ክፍት አድርጎላቸዋል። በመጨረሻም ብሉይ ኪዳን «ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር ጥላ ነውና» (ዕብራውያን 10፡1) በአዲስ ኪዳን ተተክቷል።

በአዲስ ኪዳን ዘመን ሰዎች ሌላ ግልጋሎት ያለውን የጥምቀት ሥርዓት ፈጽመዋል። ጥምቀት በራሱ ግን በሥጋ እንደ ተደረገ ግርዘት ሁሉ እርባና የሌለው ነው። ይህ ተግባር ትርጉም ያለው ከሆነ ብቻ አዲሱ ኪዳን በሰውየው ወይም በሴትዮዋ ሕይወት ውስጥ ውጤታማ ይሆናል። በጳውሎስ ጊዜ የነበሩ አይሁድ አሕዛብ የሆኑ አማኞች እንዲገረዙ ጠይቀዋል። እልፈውም በክርስቶስ ካለ እምነት በተጨማሪ የሙሴ ሕግም በጥብቅ እንዲጠበቅ ፈልገው ነበር። አሁን እንግዲህ አከራካሪ የሆነው የጥቅስ ዓውደ ንባብ ተቀባይነትን ሊያገኝ ይገባል። እንዲህ ይላልና፡-

> «ሕግንም ሁሉ እንዲፈጽም ግድ እለበት ብዬ ለሚገረዙት ሁሉ ለእያንዳንዶች ደግሜ እመሰክራለሁ። በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል... በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ፥ በፍቅር የሚሠራ እምነት እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና... ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ገና እስከ አሁን መገረዝን ብሰብክ እስከ አሁን ድረስ ለምን ያሳድዱኛል? እንኪያስ የመስቀል ዕንቅፋት ተወግዶአል» (ገላትያ 5፡3-4፥ 6፥ 11)።

በዚህ የምንባብ ክፍል ውስጥ ሁለት ወደ እግዚአብሔር ዘንድ መምጫ መንገዶች እንዳሉ ተረድተናል፡- ለመዳን የእግዚአብሔርን ቃል ሙሉ በሙሉና ሁልጊዜ (ያዕቆብ 2፡10) በመጠበቅ የማይቻለውን አሮጌ መንገድ በመከተል፥ ወይም አዲሱን ኪዳን በመቀበልና በራስ ሥራዎች ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ በመደገፍ። ይሁንና ብዙውን ጊዜ ሰው በትዕቢቱ ምክንያት የእግዚአብሔርን ምሕረትና ጸጋ ቸል ብሎ ያልፋል። «እንቅፋት» የተባለው መስቀሉ ራሱ እንደ ሆነ ግልጽ ነው። እግዚአብሔር በደጋግ ሥራዎቻችን ራሳችንን ለማዳን እንደማንችል



በማወጅ የራስ-ብቃትን ገደል ውስጥ ይከተዋል። (እባክህ ከገጽ 115-116 ያለውን ልብ በል።)

እስልምና የደግ ሥራን መንገድ ስለ መረጠ፥ ጸጋን ሊሰጥ አይችልም። ዳሩ ግን በመጨረሻው ቀን በሙታንና በሕያዋን ላይ የሚፈረደውን የእግዚአብሔርን ቅን ፍርድ ይጠባበቃል። እምቢ ያሉት ይቅርታ በኋላ አይገኝም።

11. በሃያሲያኑ አባባል በዘሌዋውያን 20፡21 ላይ፡-

    «ሰውም የወንድሙን ሚስት ቢያገባ ርኩሰት ነው» የሚለው

    በዘዳግም 25፡5፡-

    «ወንዳማማቾች በአንድነት ቢቀመጡ፥ አንዱም ልጅ ሳይኖረው ቢሞት፥ የሞተው ሰው ሚስት ሌላ ሰው ታገባ ዘንድ ወደ ውጭ አትሂድ፤ ነገር ግን የባልዋ ወንድም ወደ እርስዋ ገብቶ እርስዋን ያግባ» ከሚለው ጋር ይቃረናል። በአንደኛው ምንባብ ሰው የወንድሙን መበለት ማግባት ሲፈቀድ፥ በሌላኛው ተከልክሎአል። ሃያሲው፥ የወንድሙን ሚስት በምንም ዓይነት መንገድ መውሰድ የለበትም የሚለው ትእዛዝ (ዘሌዋውያን 20፡21)፥ ስለ ወንድሙ መበለት ከሚናገረው ከዘዳግም 25፡5 ጋር አለመቃረኑን እንዴት እንዳላስተዋለ አይገባንም።

12. በማቴዎስ 1 እና በሉቃስ 3 ላይ የተጠቀሱት የኢየሱስ የትውልድ ሐረጎች እንደሚለያዩ ብዙውን ጊዜም ተጠቅሷል። ክርስቲያኖች ይህንን ያውቃሉ። ሊሆን የሚችለው መልስ በማቴዎስ ውስጥ የምናገኘው የዮሴፍ የትውልድ ሐረግ ሲሆን፥ በሉቃስ ውስጥ የምናገኘው የማርያም (እዚህ ላይ ኤሊ የዮሴፍ አማት መሆኑ ነው) እንደ ሆነ ነው።

13. የይሁዳ አሟሟት በሁለት የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ዘገባዎች መቅረቡ አንዳንድ ጊዜ ጥያቄ ውስጥ ይገባል። በማቴዎስ 27፡5 ላይ ይሁዳ ራሱን እንደ ሰቀለ ሲናገር፥ በሐዋርያት ሥራ 1፡18፡-
    «በግንባሩ ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ አንጀቱም ሁሉ ተዘረገፈ።»

«በግንባሩ ተደፋ» የሚለው ቃል አዲስ ኪዳን በተጻፈበት በግሪክ ቋንቋ ብዙም ግልጽ ባይሆንም ምናልባት «አበጠ» የሚል ትርጉም ይኖረዋል። የኋለኛው ጥቅስ የሚያመለክተው ከሞተ በኋላ ስለሆነው ነገር እንደ ሆነ ለማሳሰብ እንወዳለን። ምናልባት በድኑ መበስበስ ከጀመረ በኋላ ከተሰቀለበት ገመድ ወድቆ ይሆናል።

14. ብዙ ጊዜ የተጠቀሰው «ግጭት» በአንድ ወገን፥

«የሕግን ሥራ በማሥራት ሥጋ የለበስ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው» (ሮሜ 3፡20) እና

«ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን ...» (ገላትያ 2፡16) የሚሉት በሌላ ወገን፥ ከያዕቆብ 2፡21፥22፥ 24 እና ከሮሜ 2፡13 ጋር የሚጋጩ ይመስላሉ፡-

«አባታችን አብርሃም... በሥራ የጸደቀ አልነበረምን? እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ፥ በሥራም እምነት እንደ ተፈጸመ ትመለከታለህን? ...ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ።»

«ከእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ።»

የኋለኛውን ጥቅስ በተመለከተ፥ አሁንም ዐውደ ንባቡን ማጤን አለብን። ይህ የሚያመለክተው በአሮጌው ኪዳን ወደነበሩት ሰዎች ነው፡- «ሕግም ሳላቸው ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል፤ በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና»(ሮሜ 2፡12-13)።

መጽሐፍ ቅዱስን ላይ ላዩን ማጥናት እንዲህ ወዳሉት ስሕተቶች ይመራል። አንድን ምንባብ ከክፍሉ ጋር አዛምደንና ቅደም ተከተሉን ጠብቀን ካልተመለከትን፥ የምናገኘው ጭብጥ የተወላገደ ይሆናል። ስለ ተጠቀሱት ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችም ወደ ዓውደ ንባቡ ለማመልከት እንፈልጋለን። ሃያሲያኑ ስለ አብርሃም በሥራ መጥቀሳቸውን መቀጠል ነበረባቸው፡-



«አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን? እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ በሥራም እምነት እንደ ተፈጸመ ትመለከታለህን?» ይህ ለ«ችግሩ» ምላሽ ያመጣል።

ሙሉው የምንባቡ ክፍል ግልጽ የሆነውን መልእክት ማለትም የአፍ እምነት (በእግዚአብሔር መኖርና በአንድ ባሕርያቱ ማመን) ሙት እንደ ሆነ ያስገነዝበናል። እንግዲህ «ሕያው» እምነት ማለት እግዚአብሔር ለሚናገረው ቃል ምላሽ የሚሆን ሥራ ነው። «አቤቱ፥ ሌሊቱን ሁሉ አድረን ስንደክም ምንም አልያዝንም፤ ነገር ግን በቃልህ መረቦቹን እጥላለሁ» (ሉቃስ 5፡5)።

15. ሌላው የተለመደ አስቸጋሪ ጥያቄ ማቴዎስ 27፡9-10ን ይመለከታል፡-

«በዚያን ጊዜ በነቢዩ በኤርምያስ የተባለው፡- ... የተገመተውን ዋጋ ሠላሳ ብር ያዙ ... የሚል ተፈጸመ»።

ይህ ምንባብ የሚገኘው በኤርምያስ ውስጥ ሳይሆን፥ በዘካርያስ 11፡12-13 ውስጥ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ «ናዚል» ነው ብንል ኖሮ ይህ አደገኛ ችግር በሆነ ነበር። ቀደም ብሎ እንደ ተገለጸው፥ ክርስቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎችን እግዚአብሔር መልእክትን እንደ ሰጣቸው አድርገው እንጂ፥ የእግዚአብሔር የታይፕ መኪና እንደ ሆኑ አድርገው አይመለከቱአቸውም። ይህም መልእክት ባመዛኙ የጸሐፊውን ቃላት የተላበሰ፥ የእርሱን ባሕርይ፥ ስልትና ፀባይ፥ አንዳንድ ጊዜም እውቀቱንና ጥበቡን የሚያንጸባርቅ ነው። እግዚአብሔር ራሱን ለሰው በመረዳት ችሎታው መጠን፥ ለሚኖርበት ጊዜና አካባቢ አስተሳሰቦች ግንዛቤ በመስጠት ይገልጻል። (ወደ ገጽ 14-17 እናጣቅሳለን።)

ክርክር ባስከተለው በማቴዎስ 27 ውስጥ ማቴዎስ የሚዘግበው ታሪካዊ ትረካ አለን። ትረካው፥ ማለትም መልእክቱ በመንፈስ ቅዱስ በመነዳት የተዘጋጀ ነው (2ኛ ጴጥሮስ 1፡21)። የምንባቡ ጸሐፊ የሚገኘው በዘካርያስ ውስጥ ስለ ሆነ፥ የማቴዎስ ወደ ኤርምያስ ማጣቀስ ስሕተት ነው። ይሁን እንጂ፥ ይህ መልእክቱን አይለውጠውም። ምናልባት ችግሩ በቀደሙት መዛግብት ውስጥ ግንዛቤ አግኝቶ ይሆናል። አንዳንዶች፡-

«በዚያን ጊዜ በነቢዩ የተነገረው ተፈጸመ»

በማለት የኤርምያስን ስም ከመጥቀስ ተቆጥበዋል። በዚህ መሠረት «ኤርምያስ» የሚለው ቃል ጣልቃ-ገብነት ሊሆን ይችላል። ዳሩ ግን ዘካርያስ አንድን ያልተመዘገበ የኤርምያስ ቃል እየጠቀሰ ሊሆን የመቻሉ ሁኔታ ከፍተኛ ነው (ቶሪ፡- «ፈታኝ ሁኔታዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ» ተመልከት)።

16. እንዲሁም (ኢየሱስ በቤት ውስጥ በተወለደበት) በማቴዎስ 2፡11 እና (በግርግም በተወለደበት) በሉቃስ 2፡7 መካከልም «ግጭት» አለ። በማቴዎስ 2፡11 ላይ ስለ ኢየሱስ መወለድ የሚናገር ነገር ስለሌለ፥ ምናልባት ሃያሲው ምንባቦቹን በበቂ ጥንቃቄ አልመረመረም ይሆናል። በኢየሱስ መወለድና በ«ጠቢባኑ» ከምሥራቅ መምጣት መካከል በቂ የጊዜ ገደብ ነበረ። ሄሮድስ መጀመሪያ ኮከቡን በተመለከቱ ጊዜ ከአዋቂዎች ተረድቶ ከሁለት ዓመትና ከዚያም በታች የሆኑ ሕፃናት እንዲገደሉ ማድረጉ በጣም ጥሩ እሳብ ይሰጠናል። የሳምንት ዕድሜ ያለውን ሕፃን በሜዳ ላይ ከሚጫወተው ከሁለት ዓመት ልጅ ጋር ማን ያሳስተዋል? ደግሞም ከምሥራቅ ምናልባትም ከባቢሎን እስከ ፍልስጤኤም አገር ያለው መንገድ የተወሰነ የጊዜ ርዝማኔ እንደ ወሰደ መመልከት አለብን። በዚያን ወቅት ማርያምና ዮሴፍ ከግርግም ወደ ቤት ከተዛወሩ ብዙ ጊዜ ሆኖአቸዋል።

17. ሌላው «ግጭት» በሉቃስ 3፡23 ላይ ኢየሱስ ሠላሳ ዓመት ያህል እንደ ሆነውና በዮሐንስ 8፡57 ላይ ፈሪሳውያን ለኢየሱስ፡-
«ገና ሃምሳ ዓመት ያልሆነህ»

ማለታቸው ነው። አንድ ሰው ሠላሳ ዓመቱ ከሆነ ገና ሃምሳ ዓመት እንዳልሞላው ግልጽ ነው።

## በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የቀረቡ ተቃውሞዎች

1. ሃያሲው ወደ ዘሌዋውያን 19፡27 በመጥቀስ፥ ሰው የጢሙን ዙሪያ ቢቆረጥ ወይም ቢተወው፥ እግዚአብሔርን ለምን እንደሚገደው ይጠይቃል።

«የራስ ጠጕራችሁንም ዙሪያውን አትከርክሙት፤ ጢማችሁንም ዙሪያውን አትቈረጡት።»

ይህ አግባብ ያለው ጥያቄ ቢሆንም፥ ሙስሊሙን ሃያሲ ለምን ጢሙን «በሁሉም ጎኖች እኩል አድርጎ» ማሳደግ እንዳለበት በመጠየቅ መልሱን እንሰጣለን።

እርግጥ

«ለሙስሊም ጢሙን ማሳደግ ሱናት» ነው።

እንዲሁም «ጢሞች መቀባት፥ መታጠብና መበጠር፥ እንዲሁም ትሎችን በብሩሽ አማካኝነት መወገድ ይገባል» (ሚሽካት 1፥ ገጽ 602) ያለባቸው ለምንድነው ብለን እንጠይቃለን።

2. «ውሻ ውኃ እንደሚጠጣ በምላሳቸው የሚጠጡ ሰዎች ከሁሉ የተሻሉ ወታደሮች እንደሚሆኑ በእርግጥ ታምናላችሁን?» ተብለን በመሳፍንት 7፡5 ከሚገኘው ጥቅስ አኳያ እንጠየቃለን። ይህ ታሪክ ትክክል ባልሆነ ሁኔታ በቁርዓን ውስጥ ተደግሞ እናገኘዋለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ በዚህ ዓይነት መንገድ የተመረጡት የጌዴዎን ሰዎች ነበሩ። በቁርዓን ውስጥ (ሱረቱ 2፡249) ግን በዚህ ዓይነት የተፈተኑት የሳኦል ወታደሮች ሆነው እናገኛለን። እንደ ብዙዎቹ ሌሎች ሁሉ ይህም ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ሳይሆን፥ ንግግርን ለማጣፈጥ ሲባል የቀረበ ይመስለናል። እንዳንድ ጊዜም የጌዴዎንን ድል በተመለከተ ተጠይቀናል።

3. «አንድ ሰው በአንድ ጊዜ በግራ እጁ ችቦ፥ በቀኙ ቀንደ መለከት በመያዝ፥ ቀንደ መለከቱን ሊነፋና የእግዚአብሔርና የጌዴዎን ሰይፍ ብሎ በመጮኽ፥ ማሰሮውን ለመስበር የሚችል ይመስልሃል?»
በተጠቀሰው ክፍል (መሳፍንት 7፡20) በየትኛውም ስፍራ ይህ ሁሉ በአንድ ቅጽበት እንደ ተፈጸመ አይናገርም።

4. «ፋቁሔ በአንድ ቀን መቶ ሃያ ሺህ ሰዎችን እንደ ገደለ ለማመን ትችላለህን?» (2ኛ ዜና መዋዕል 28፡6)።
ሒትለር 6 ሚሊዮን አይሁዶችን መግደሉ እርግጠኛ የሆነውን ያህል፥ ይህም እውነት እንደ ሆነ እናምናለን።

5. እግዚአብሔር አንድን ሰው «ሚስት ታጫለህ፤ ሌላም ሰው ከእርስዋ ጋር ይተኛል» (ዘዳግም 28፡30) ሲል ተናገረ መባሉ በንቀት ይወሳል።

የዚህ ምዕራፍ ዓውደ ንባብ የእስራኤልን ሕዝብ የሚመለከት ትንቢት ነው። በዚህ ክፍል (ዘዳግም 28፡1-14) እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ታዝዘውት ቢሆን ኖሮ ምን ይሆን እንደ ነበርና ከቁጥር 15 በመቀጠል ደግሞ ባይታዘዙት የሚደርስባቸው መርገም በሰፊው ሲዘረዘር ከተተነበዩት መካከል ይህም ቁጥር ይገኛል። የአጋጣሚው ውስጠ ወይራ መሐመድ ራሱ ይህ ትንቢት እንዲፈጸም ብርቱ አስተዋጽኦ ማበርከቱ ነው። ከመሐመድ ቁባቶች አንዷ ሪሃና የተባለች አይሁዳዊት ሴት ነበረች። እርሷም ከኩራይዛው የአይሁድ ነገድ ሽንፈትና ከወንዶቹ ጭፍጨፋ በኋላ እንደ ምርኮኛ መርጦ የወሰዳት ነች። (እብን ኢሻቅ፡- ሶራቱር ራሱል ቅጽ 693 ገጽ 466)።

6. በ2ኛ ጴጥሮስ 3፡3-10 የኢየሱስ ምጽአት በቶሎ የሚፈጸም እንዳልሆነ ተጠቅሷል።

«ጌታ... ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል።»

ይህም በሚከተለው ዐሪፍተ ነገር ውስጥ ተብራርቷል፡-

«በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፥ ሺህም ዓመት እንደ አንድ ቀን እንደ ሆነ አትርሱ።» የእግዚአብሔርን ከጊዜ ውጪ መሆን ያመለክታል። ተቺው ሚስተር ጁማል ይህንን «ለውይይት የማይቀርብ ፈር የሳተ ነው» በማለት ይጠሩታል። እንግዲህ እኚህ ሰው በቁርዓን ስለሚገኙት ስለሚከተሉት የምንባብ ክፍሎች የሚያውቁት የላቸውም ማለት ነው፡-

«አላህም ቀጠሮውን በፍጹም የማይጥስ ሲኾን፥ በቅጣት ያቻኩሉሃል፤ እጌታህም ዘንድ አንዱ ቀን ከምትቆጥሩት (ቀን) እንደ ሺሕ ዓመት ነው» እና «መላእክቱና መንፈሱም ልኩ አምሳ ሺሕ ዓመት በኾነ ቀን ውስጥ ወደርሱ ያርጋሉ (ይወጣሉ)» (ሱረቱ 22፡47 እና 70፡4)።



እነዚህ የመከራከሪያ ዐሪፍተ ነገሮች ተደጋጋሚና አላስፈላጊ በመሆናቸው ለተወገዱት ለሌሎቹ በርካታ መከራከሪያ ነጥቦች ተወካዮች ይሁኑ።

ከሞላ ጐደል በሁሉም ጉዳዮች ላይ የቀረቡት «ግጭቶች» የሙግት ጥመኛ አእምሮ ፍጡሮች እንደ ሆኑ ለመመልከት እንችላለን። በጣም መሃይም ወይም በጣም ደፋር ወይም መንፈስ ደካማ በመሆኑ፥ የእርሱ ከሆነው ጋር በመቃረኑ ምክንያት የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክቶች በማጣጣል ወደ ማጠቃለያ ከመድረሱ በፊት መረጃውን አይቶ በእውነታዎች ብርሃን ነገሮችን አይወስንም።

አሁን ሙስሊሙ አንባቢ ከክሶቹ ብዙዎቹ ዋጋ የሌላቸው እንደ ሆኑ ተረድቷል። ይሁን እንጂ አሁንም ወደ እግዚአብሔር ቃል ውስጥ አንድም ስሕተት እንኳ እንዴት ሊገባ ይችላል ይል ይሆናል። ሃያሊያኖቻችንን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለሚገኙ 100000 የስሕተቶች መዘርዝር (የሚስተር ጁማል ጥቅስ) ወይም ቢያንስ 50000 ለሚሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ስሕተቶች (በሚስተር ዲዳት መጽሐፍ «መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነውን?») መሠረት እንዲያቀርቡ መጠየቃችን አላግባብ ሆኖ አናገኘውም። ከአንድ ወይም ከሌላ ካልታወቀ እና ተቀባይነት ከሌለው «ክርስቲያን» ቢመጡ እንኳ፥ እንዲህ ያለውን ፌዝ አለማጠናከሪያ ልንቀበል አንችልም።

ሃያሲያኑ «ስሕተቶች» ብለው ካላተሟቸው መካከል እጅግ የከረሩት ተገኝተው ተገምግመዋል። ይሁንና እነዚህ «ስሕተቶች» እና «ብልሽቶች» መሠረት የሌላቸውና ከከፋ ጥላቻ የተነሣ የተሰነዘሩ መሆናቸውን ለመገንዘብ ችለናል። ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው (ገጽ 20-21)፥ 7959 ሊሆኑ ከሚችሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ቁጥሮች መካከል ከዮሐንስ 7፡53-8፡11 በተጨማሪ በስምንቱ ውስጥ ብቻ ጣልቃ የገባ ነገር የሚገኝባቸው ይሆን ይሆናል። እነዚህም ቢሆኑ ያስከተሉት የአላብ መዛባት የለም። የተጠቀሱት ግጭቶችና ተቃውሞዎችም ቢሆኑ በደካማ መሠረት ላይ የተጣሉ ናቸው። ሙሉ በሙሉ ታሪካዊ በሆኑ ዘገባዎች ውስጥ የተለያዩ ቁጥሮችን ወይም ስሞችን ከሚያካትቱ ከ10 የግልበጣ ስሕተቶች በተጨማሪ (ገጽ32-33)፥ ከተጠቀሱት ውስጥ አጠያያቂ ሊሆኑ የሚችሉ ገለጻዎች የተሰጡባቸውን ሁለቱን ብቻ (ስፍራ

ከሚሰጣቸው እነኚህ ብቻ ናቸው) ለማውጣት እንችላለን (በገጽ 47-49 የሚገኙ 12ኛና 15ኛ ነጥቦች)።

ከላይ የቀረበው ወቀሳ ከ3500-2000 ዓመታት በፊት በተጻፈና ከ400 ዓመታት ገደማ በፊት የማተሚያ ቤት ሳይቋቋም፥ በተደጋጋሚ በእጅ ሲገለበጥ በቆየ፡ መጽሐፍ ቅዱስን በሚያህል ግዙፍ መጽሐፍ ዓውድ ውስጥ ሲታይ፡ ጽሑፉን ከተአማኒነት በላይ ከፍ ያደርገዋል።

ሙስሊሞች በቁርዓን ውስጥ ግጭት እንደሌለና የሰው እጅም እንዳልነካው እንዲቀበሉ ተደርገው ነው የሚያድጉት። ቁርዓንና ሃዲስን በጥልቀት በምንመለከትበት «ክርስቲያኖች ሙስሊሞችን ይጠይቃሉ» በተባለው መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን እሳቦች ሁሉም ሰው እንዲያነብ ለማበረታታት እንወዳለን። ይህ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሊኖሩ ለሚችሉት የመገልበጥና ለሌሎችም ተመሳሳይ ስሕተቶች ማካካሻ ለማቅረብ አይደለም። ለብዙ ተከታታይ ዓመታት እየተገለበጡ ሲቆዩ ስሕተቶች ሾልከው ይገቡባቸዋል። ከላይ የቀረቡት ሊወዳደሩዋቸው እንኳ የማይችሉትን የጠለቀ ተፈጥሮ ያላቸውን ሌሎች ችግሮች መጠቆም ይኖርብናል። እኛ በመለኮታዊ መንፈስ መነዳትን በተመለከተ ስለሚቀርበው የእውነታዎች ማረጋገጫ እና ስለ መረጃ ነው የምንነጋገረው። ብድር ለመመለስ ወይም ክርክሩን ለመርታት እየጣርን እንዳልሆን ለአንባቢው ደግመን በቅንነት ለማረጋገጥ እንወዳለን። ዳሩ ግን ከማስተዋልህ የተሰወሩና የማታውቃቸው፥ ሆኖም ግን መርምረህ ማየት ያለብህን እውነቶች እንድትረዳቸው እንወዳለን። ምክንያቱም እነዚህ እውነቶች መለኮታዊ ራእይን ክወዴት እንደምታገኝ ላለብህ ጥያቄ እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው።

## ክርስቲያኖች በውርስ ኃጢአት ያምናሉን?

ይህን ጥያቄ ለመመለስ መጀመሪያ የቃላትን ፍቺ መስጠት አለብን። «የውርስ ኃጢአት» ማለት በትክክል ምን ማለት ነው? ክርስቲያን ለመሆን መጽሐፍ ቅዱሳውያን መሆን ይኖርብናል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ውርሰ ኃጢአት ምን ይላል? ምንም! ምናልባት ሊገለገልበት የሚችለው ሌላ ሐረግ አለ። እርሱም የመጀመሪያ ኃጢአት ነው። ይህም አዳምና ሔዋን በዔድን ገነት የአትክልት ስፍራ የፈጸሙት ኃጢአት ነው። የእነርሱ ኃጢአት በቀደሙት ዘመናት እንደ ታሰበው ወሲብ አይደለም። የወሲብ



ስሜት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ነው። ዳሩ ግን አላግባብ ከግልጋሎት ሊውል ይችላል። ይህም ከሆነ ኃጢአት ይሆናል። ነገር ግን በጋብቻ ትስስር ውስጥ ሲፈጸም በራሱ ኃጢአት አይደለም።

በመዝሙር (51)፡5 ውስጥ፥ «እነሆ፥ በዓመፃ ተፀነስሁ» የሚል አንድ ጥቅስ አለ። ነገር ግን ምንባቡን በጥንቃቄ ብንመለከት መፀነሱ ኃጢአት እንዳልሆነ እንገነዘባለን። ዳሩ ግን በኃጢአተኝነት ውስጥ ሆኖ ፅንሱ ተከናወነ። በእነዚህ በሁለቱ አመለካከቶች መካከል የሰማይና የምድር ያህል ርቀት ይገኛል።

በዚህ ትምህርት ላይ የሚናገሩ ሁለት ምንባቦች ብቻ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ (ሮሜ 5፡12-18 እና 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡21-22)። በዚህ ቦታ ኃጢአት በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም እንደ መጣና በዚህም በአንድ ሰው መተላለፍ ሳቢያ ኩነኔ ለሰው ሁሉ እንደ ደረሰ በግልጽ ይናገራል። እንዲሁም ደግሞ ሁሉም ሰው ኃጢአትን ስላደረገ የኃጢአት ውጤት የሆነው ሞት ወደ ሰው ሁሉ እንደ ደረሰ ይናገራል።

ስለዚህ ማንም ሰው አዳም ኃጢአትን ስለ ሠራ አይኮነንም። ሰው የሚኮነነው እርሱ ራሱ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ስለ ሠራ ነው። ስለ ሆነም ስለ መጀመሪያው ኃጢአት እንጂ፥ ስለ ተወረሰው ኃጢአት መናገሩ ትክክል አይደለም።

ኃጢአት በአዳም ተጀምሮ ከዚያን ጊዜ አንሥቶ ከትውልድ እስከ ትውልድ እስከ አሁንም ድረስ ሰው ሁሉ ወደ ኃጢአት የሚነዳውን ኃይል፥ ኃጢአታዊ ባሕርዩን ወርሷል። እናም ኃጢአት ስለምንሠራ ኃጢአተኞች ነን። ስለ ሆነም ማንም ሰው የኃጢአት ፍላጎትን እንጂ ማንኛውንም ኃጢአት ከቀደምት አባቶቹ አልወረሰም።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለ«ሕመሙ» ፈውስን እንደ ሰጠ ለማሳሰብ እንወዳለን። «በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች አንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ» (ሮሜ 5፡19)። ይህ ሰው ኢየሱስ ነው። ግዳጅ እንደሌለ እንመለከታለን። የአንድ ሰው ኃጢአቱ ወደ ልጆቹ ኃጢአት ወዘተ... መራ፤ ዳሩ ግን እያንዳንዱ ሰው ለሚሠራቸው ሥራዎቹ የግሉ ፈቃድ አለው። እንደዚሁም ከኃጢአት ከስ በእግዚአብሔር የጽድቅ ችሎት ፊት ነጻ መሆን የሚቻለው በግድ ሳይሆን፥ በምርጫ ነው።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጸያፍ አባባሎችና አስቃቂ ድርጊቶች

ብዙ ሙስሊሞች፡-

> «የብሉይ ኪዳን ግብረ-ገባዊ ባሕርይ ጎልዳፋና አረመኔያዊ ነው» የሚል አስተሳሰብ አላቸው።

ይህ መጽሐፍ ቅዱስ በ«ሳንሱር» አድራጊዎች መፈተን እስከሚገባው «ጸያፍ አባባሎችን» እንዳዘለ ተደርጎ የተነገረ ነው።

ወደ ውዝግቡ ሳንገባ፥ ሁለት ነጥቦችን ለመግለጽ እንወዳለን፡- የእነዚህ «ጸያፍ አባባሎች» በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መገኘት ከሚከተሉት ሁለት ነገሮች አንዱን ያረጋግጣል፡-

ሀ) ደራሲውና በየዘመናቱ የነበሩ አንባቢዎች ሁሉ ሊስተናገድ እንደሚገባ ወሲብ ቀስቃሽ ነገር አድርገው ወስደውታል፤ ወይም

ለ) ለተገለጠላቸው ቃል ከነበራቸው አክብሮት የተነሣ እጅግ አሳፋሪና አስጸያፊ የሆኑ ሁቆችን ስለ ቅድመ-አያቶቻቸው ማለትም ሎጥ ከልጆቹ ጋር ግንኙነት ስለ መፈጸሙ፥ ወይም ስለ አስከፊው የንጉሥ ዳዊት ኃጢአት፥ ወይም በትዕግር ላይ የተፈጸመውን ዓይነትና እንዲሁም በመሳፍንት ምዕራፍ 19 ላይ እንደ ተመዘገበው ሴትን የመድፈር አድመኛነት ያሉትን ቢያጋልጥም እንኳ፥ ሊለውጡት አልደፈሩም።

መጽሐፍ ቅዱስ የአይሁዶችን የተጻፈ ታሪክ አካትቶ ይዟል። የማንኛውም አገር ታሪክ ጸሐፊዎች ታሪከን ለመመዝገብ የሚጥሩት ያን አገርና ሕዝብ በሚያስከብር መንገድ ነው። የተመሳሳይ ክስተቶች ታሪካዊ ዘገባዎች እንደየአመለካከታቸው መንጋደድ መጠን ከአገር ወደ አገር በስፋት ሊለያዩ ይችላሉ። በእስራኤላውያን አሳፋሪ ኃጢአቶች ሀቀኛ ዘገባ ውስጥ፥ ማንም ሰው የአይሁዶችን ገጽታ ለማሻሻል እንዳልሞከረ ግልጽ ምልክት ለማየት እንችላለን። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ዘገባ አንድ ወጥና ተአማኒነት ያለው ስለ መሆኑ ሚዛን ደፊ እውነታ ነው።

ለ«ሴት» የሚያገለግለው የዕብራይስጥ ቃል «የሚያመለከተው ወንድ በእርሷ ላይ ያለውን የፍትወት ፍላጎት ብቻ» እንደ ሆነ ይነገረናል።



ይህ ዐረፍተ ነገር እውነትነት ያለው አይደለም። «እሻ» የሚለው የዕብራይስጥ ቃል የ«እሽ» እንስታዊ-ገጽታ ነው። እሽ ማለት ወንድ ማለት ነው። ብድር ለመመለስ ባንሻም፥ በፊት መሐመድ ወደ ጦርነት ለመሄድ ከተዘጋጀ በኋላ «ከእርሷ ጋር የወሲብ ግንኙነት እየፈጸመ ለመኖር ፈልጎ የሴቲቱን የግል ክፍል ሕጋዊ ያደረገውን ሰውዬ» ነጻ ስላደረገበት ሁኔታ በ«ሚሽካት» ውስጥ (2፥ ገጽ 426) ከሚገኘው ሃዲስ ለማጣቀስ ዳድቶናል። ይህ ዛሬ ሕጋዊ ሴትኛ አዳሪነት ተብሎ ሊጠራ የሚችል ነው።

ክርስቲያኖችም በእስልምና ውስጥ ስለሚፈጸሙት ጭካኔዎች ተመሳሳይ ነገሮችን መናገር ይችላሉ። ቢያንስ ቢያንስ የቀድሞው የእስልምና ድል በጭካኔ የተሞላ ስለ መሆኑ ለመካድ (ምንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ የተጋነነ ቢሆንም) አይቻልም። የሆነው ሆኖ በጭካኔዎች መዝገብ ውስጥ የምናየው የመጽሐፍ ቅዱስን ተአማኒነት የሚያሳየንን ምልክት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የኃጢአትን ተግባር እንዲሁ አያልፍም፤ የሚመጣበትን የእግዚአብሔርን ፍርድ ያውጃል እንጂ፥ ለቆሸሹ ሥራዎች ምንም ዓይነት ውዳሴ አያቀርብም (2ኛ ሳሙኤል 11፡26፥27-12፡1-19 ተመልከት)።

> «የኦርዮም ሚስት ባልዋ ኦርዮ እንደ ሞተ በሰማች ጊዜ ለባልዋ አለቀሰች። የልቅሶዋም ወራት ሲፈጸም ዳዊት ልኮ ወደ ቤቱ አስመጣት፤ ሚስትም ሆነችው፥ ወንድ ልጅም ወለደችለት፤ ነገር ግን ዳዊት ያደረገው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሆነ።

> «እግዚአብሔርም ናታንን ወደ ዳዊት ላከ፥ ወደ እርሱም መጥቶ አለው፡- በአንድ ከተማ አንዱ ባለጠጋ አንዱም ድሀ የሆኑ ሁለት ሰዎች ነበሩ። ባለጠጋውም እጅግ ብዙ በግና ላም ነበረው። ለድሀው ግን ከገዛት አንዲት ታናሽ በግ በቀር አንዳችም አልነበረውም፤ አሳደጋትም፥ ከልጆቹም ጋር በእርሱ ዘንድ አደገች እንጀራውንም ትበላ፥ ከዋንጫውም ትጠጣ፥ በብብቱም ትተኛ ነበር፥ እንደ ልጁም ነበረች። ወደ ባለጠጋውም እንግዳ በመጣ ጊዜ ከበጉና ከላሙ ወስዶ ለዚያ ወደ እርሱ ለመጣው እንግዳ ያዘጋጅለት ዘንድ ሳሳ የዚያንም የድሀውን ሰው በግ ወስዶ ለዚያ ለመጣው ሰው አዘጋጀ። ዳዊትም በዚያ ሰው ላይ እጅግ ተቆጥቶ ናታንን፡- ሕያው እግዚአብሔርን!

ይህን ያደረገ ሰው የሞት ልጅ ነው። ይህን አድርጎአልና አላዘነምና ስለ አንዲቱ በግ አራት ይመልስ አለው።

«ናታንም ዳዊትን አለው፡- ያ ሰው አንተ ነህ። የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- በእስራኤል ላይ ንጉሥ ልትሆን ቀባሁህ፥ ከሳኦልም እጅ አዳንሁህ፤ የጌታህንም ቤት ሰጠሁህ፥ የጌታህንም ሚስቶች በብብትህ ጣልሁልህ የእስራኤልንና የይሁዳን ቤት ሰጠሁህ፤ ይህም አንሶ ቢሆን ኖሮ ከዚህ የበለጠ እጨምርልህ ነበር። አሁንስ በፊቱ ክፉ ትሠራ ዘንድ የእግዚአብሔርን ነገር ለምን አቃለልህ? ኬጢያዊውን ኦርዮን በሰይፍ መትተሃል፥ ሚስቱንም ለአንተ ሚስት ትሆን ዘንድ ወስደሃል እርሱንም በአሞን ልጆች ሰይፍ ገድለሃል። ስለዚህም አቃልለኸኛልና፥ የኬጢያዊውንም የኦርዮን ሚስት ለአንተ ሚስት ትሆንህ ዘንድ ወስደሃልና ለዘላለም ከቤትህ ሰይፍ አይርቅም። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እነሆ፥ ከቤትህ ክፉ ነገር አስነሣብሃለሁ፤ ሚስቶችህንም በዓይንህ ፊት እወስዳለሁ፥ ለዘመድህም እሰጣቸዋለሁ፥ በዚህችም ፀሐይ ዓይን ፊት ከሚስቶችህ ጋር ይተኛል። አንተ ይህን በስውር አድርገኸዋል፤ እኔ ግን ይህን በእስራኤል ሁሉ ፊትና በፀሐይ ፊት አደርገዋለሁ። ዳዊትም ናታንን፡- እግዚአብሔርን በድያለሁ አለው። ናታንም ዳዊትን፡- እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልሃል፤ አትሞትም። ነገር ግን በዚህ ነገር ለእግዚአብሔር ጠላቶች ታላቅ የስድብ ምክንያት አድርገሃልና ስለዚህ ደግሞ የተወለደልህ ልጅ ፈጽሞ ይሞታል አለው። ናታንም ወደ ቤቱ ተመለሰ።

«እግዚአብሔርም የኦርዮ ሚስት ለዳዊት የወለደችለትን ሕፃን ቀሠፈ፥ እጅግም ታምሞ ነበር። ዳዊትም ስለ ሕፃኑ እግዚአብሔርን ለመነ፤ ዳዊትም ጾመ፥ ገብቶም በመሬት ላይ ተኛ። የቤቱም ሽማግሌዎች ተነሥተው ከምድር ያነሡት ዘንድ በአጠገቡ ቆሙ፤ እርሱ ግን እንቢ አለ፥ ከእነርሱም ጋር እንጀራ አልበላም። በሰባተኛውም ቀን ሕፃኑ ሞተ። የዳዊትም ባሪያዎች፡- ሕፃኑ በሕይወት ሳለ ብንነግረው አልሰማንም፤ ይልቁንስ ሕፃኑ እንደ ሞተ ብንነግረው እንዴት ይሆን? በነፍሱ ክፉ ያደርጋል ብለው ሕፃኑ እንደ ሞተ ይነግሩት ዘንድ ፈሩ። ዳዊትም ባሪያዎቹ በሹክሹክታ ሲነጋገሩ



ባየ ጊዜ ዳዊት ሕፃኑ እንደ ሞተ አወቀ፤ ዳዊትም ባሪያዎቹን፡- ሕፃኑ ሞቶአል? አላቸው። እነርሱም፡- ሞቶአል አሉት» (2ኛ ሳሙኤል 11፡26-12፡19)። ተመሳሳይ ሁኔታ በኢያሱ 8፡18-26 ላይ ተመዝግቦአል።

## ያልተፈጸሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች

የሚሽካት ተርጓሚ (4 ገጽ 396) የሚከተለውን ይናገራል፡-

> «በተአምራት ውስጥ ትልቁ ነገር ትንቢት ማለትም ለወደፊት ስለሚሆኑት ነገሮች አስቀድሞ መናገር ነው። ይህ የፖለቲካ ትንበያ ሳይሆን፥ ስለወደፊት ምሥጢራት ከመለኮታዊ እውቀት የሚመነጭ ንግርት ነው። ትንቢት በሚከተለው ምክንያት ከሁሉም የላቀ (ተአምር) ነው፡- ትንቢት በታሪክ ሊረጋገጥ ሲችል፥ ተአምር ግን አይችልም። ተአምራት የእግዚአብሔርን ኃይል ሲገልጹ፥ ትንቢት ግን የእግዚአብሔርን የቅድሚያ እውቀት ይገልጻል። እውቀት ከኃይል እንደሚበልጥ ሁሉ፥ ትንቢትም ከተአምር ይበልጣል።»

እውነተኛ ትንቢት ከሰብአዊ መጪውን የማወቅ ችሎታ በላይ መሆንና በአጠቃላይ መልኩ ለዚህ ወይም ለዚያ ክስተት እንዳይውል በቂ ዝርዝሮች ሊኖሩት ይገባል። በመጽሐፍ ቅዱስ መመዘኛዎች መሠረት፥ ትንቢቶች እንደ ነቢዩ መታወቂያዎች ናቸው፡-

> «እግዚአብሔር ያልተናገረውን ቃል እናውቅ ዘንድ እንዴት ይቻለናል? ብትል፥ ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ የተናገረው ነገር ባይሆን ባይመጣም፥ ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው፤ ነቢዩ በድፍረቱ ተናግሮታል፤ እርሱን አትፍራው» (ዘዳግም 18፡21-22)።

> «ማስረጃችሁን አምጡ . . . ያምጡ፥ የሚሆነውንም ይንገሩን . . . የቀደሙት ነገሮች ምን እንደ ሆኑ ተናገሩ፥ የሚመጡትንም አሳዩን። አማልክትም መሆናችሁን እናውቅ ዘንድ በኋላ የሚመጡትን ተናገሩ» (ኢሳይያስ 41፡21-23)።

እንደ አጠቃላይ መመሪያ በርካታ ትንቢቶች ገና ክፍጻሜአቸው እንዳልደረሱ መግለጽ አለብን። የእስራኤል መንግሥት እንደገና

መመሥረትና የአይሁዶች ወደ ቀድሞዪቱ ምድራቸው መመለስን የመሳሰሉ አንዳንድ ትንቢቶች በዘመናችን በመፈጸም ላይ ይገኛሉ። እስከ አሁን አብዛኛዎቹ የትንቢት ቃላት ከፍጻሜ ደርሰዋል።

ሙስሊም ሃያሲያን የመጽሐፍ ቅዱስን መለኮታዊ ባሕርይ ፉርሽ ለማድረግ አንዳንድ ያልተፈጸሙ ትንቢቶችን ለቅመው አውጥተዋል።

> «ይህ ሁሉ እስኪሆኚ ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም» (ማቴዎስ 24፡34)

የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ዐረፍተ ነገር ለአብነት ቀርቧል።

ከእነዚህ ሃያሲያን የሚሰነዘረው አሳብ «ይህ ትውልድ ከብዙ ዘመናት በፊት አልፎአል» የሚል ነው። ጥያቄው የትኛው ትውልድ የሚል ነው? ዓውደ ንባቡ የበለጠ መረጃ ይሰጠናል።

> «ምሳሌውንም ከበለስ ተማሩ ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያቈጠቍጥ፥ ያን ጊዜ በጋ እንደ ቀረበ ታውቃላችሁ፤ እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ ሰታዩ በደጅ እንደ ቀረበ እወቁ። እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም። ሰማይና ምድር ያልፋሉ፥ ቃሌ ግን አያልፍም» (ማቴዎስ 24፡32-35)።

ይህ «የበለስዋ ቅጠል በሚያቈጠቍጥበት ጊዜ» የሚኖር ትውልድ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በለስ የእስራኤል ሕዝብ ምሳሌ ነች። ለ2000 ዓመታት ያህል «ሞታ» ከኖረች በኋላ፥ እስራኤል አሁን ቅጠሏ እያቈጠቈጠ ነው።

ሌላው የውሸት ትንበያ የተባለው ደግሞ የሚከተለው ዐረፍተ ነገር ነው፡-

> «የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ እዚህ ከሚቆሙት ሞትን የማይቀምሱ አንዳንድ አሉ» (ማቴዎስ 16፡28)።

የሰው ልጅ የመንግሥቱ የልደት ቀን በሆነው በበዓለ ኀምሳ ዕለት በመንግሥቱ (ስለ መንግሥቱ የሰጣቸውን ምሳሌዎች ልብ በል) መጥቷል።



በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ይህን ሲናገር ከሰሙት ብዙዎቹ በበዓለ ኀምሳው ዕለት በሕይወት ነበሩ።

እንዲሁም በናቡከደነፆር ጢሮስ እንደምትወድም በሕዝቅኤል 26፡7-10 የተነገረው ትንቢት እንዳልተፈጸመ ተነግሯል።

> «ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፡- እነሆ፥ ከሰሜን የነገሥታት ንጉሥ የባቢሎንን ንጉሥ ናቡከደነፆርን ከፈረሶችና ከሰረገሎች ከፈረሰኞችም ከጉባኤና ከብዙ ሕዝብ ጋር (ደሴቲቱን ለማጥቃት? ጂ. ኤን.) በጢሮስ ላይ አመጣለሁ። በሜዳ ያሉትን ሴቶች ልጆችሽን በሰይፍ ይገድላቸዋል፥ አምበም ይሠራብሻል አፈርንም ይደለድልብሻል ጋሻም ያነሣብሻል ... ከፈረሶቹም ብዛት የተነሣ ትቢያቸው ይከድንሻል ሰዎችም በትናደች ቅጥር ወደ ከተማ እንደሚገቡ እርሱ በበሮችሽ ሲገባ፥ ከፈረሰኞችና ከመንኰራኵሮች ከሰረገሎችም ድምጽ የተነሣ ቅጥርሽ ትናወጣለች» (በትንሿ ደሴት ግንብ ላይ? ጂ. ኤን.)።

ከዚያ ቀጥሎ ለሰብአዊ ገለጻ የቀረበው ተውላጠ ስም ከ«እርሱ» ወደ «እነርሱ» ሲለወጥ እንመለከታለን፡-

«ቅጥርሽንም ያፈርሳሉ... ድንጋይሽንና እንጨትሽን መሬትሽንም በባሕር ውስጥ ይጥላሉ» (ቁጥር 12)።

ይህ የሆነው ከየብሱ በ700 ሜትር ያህል ወደሚርቀው ደሴት በባሕሩ ውስጥ የሚያገናኘው ድልድይ ከተሠራ በኋላ ነው።

> «የተራቆተ ድንጋይ አደርግሻለሁ» (ቁጥር 14)።

ከርክሩን ያስነሣው ይህ የኋለኛው ሐረግ ነው፡-

> «ከእንግዲህ ወዲህ አትሠሪም» (ቁጥር 14)።

ዳሩ ግን ምን? የሚል ጥያቄ እናነሣለን። ቤቶችና ቅጥሮች ወይም በዚያን ጊዜ በዓለም ታዋቂ የንግድ ማዕከል የነበረችውን እጅግ ደማቅ ከተማን? ኋለኛውን በተመለከት፥ ትንቢቱ ትክክል ነበር። ሙሉ በሙሉ ባይሆንም እንኳ፥ ናቡከደነፆር ጢሮስን ደምስሷታል።

ጢሮስ ሁለት ክፍሎች ነበሯት። ትንሿ ጢሮስ በደሴት ላይ የነበረችው ስትሆን፡ ትልቋ ጢሮስ በየብሱ ላይ የነበረች ነች። ናቡከደነፆር በየብሱ ላይ የነበረችውን ወይም ጥንታዊቷን ጢሮስ በማሸነፍ ደሴቲቱ ጢሮስን (ጢሮስ ማለት ድንጋይ) ለ13 ዓመታት ከብቧታል። የጢሮስን ንጉሥ ተከትለው የነገሡ ገዥዎቹ የባቢሎን ገባሮች ከመሆናቸው በስተቀር፥ ታሪክ ስለ ጥቃቱ ውጤት ያስቀመጠልን ነገር የለም። (ጆሲፈስ በአፒዮን 1፡21 ውስጥ ከፊንቄ ዜና ሲዘግብ ጢሮስ በፊንቄ ውስጥ ስለምትገኝ፥ ምናልባት አሳፋሪ የሆነውን ውጤት ሸሽጎት ይሆናል።)

ይሁንና ታላቁ እስክንድር የጥንቷን ጢሮስ ፍርስራሽ እስከ ደሴቲቱ ከተማ በመቆለል በድልድይነት ተጠቅሞ ከተማይቱን ሲደመስሳት ትንቢቱ ተፈጽሟል። ይህ በሕዝቅኤል ትንቢት ውስጥ ተነግሮ ነበር። ጢሮስ ብዙ ጊዜ ተመልሳ እንደ ተሠራች እናውቃለን። ዳሩ ግን በርካታ ጊዜያት ስለ ተደመሰሰች የቀድሞ ኃይሏንና እንቅስቃሴዋን መልሳ ለመቀዳጀት አልቻለችም። ላለፉት 800 ዓመታት በባሕር ውስጥ ሰው የማይኖርባት ድንጋይ ሆና በመቆየት የሕዝቅኤልን ትንቢት የመጨረሻ ክፍል አሟልታለች።

ይህ ሁሉ ግን ባንጻሩ ጊዜ ያለፈበትና የራቀ ትንቢት ነው። ከዚህ ላይ ማቆሙ ትንቢትን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያቀርበው ይህንኑ እንደ ሆነ ሊያስመስል ይችላል። ነገር ግን በፍጹም እንደዚህ አይደለም። እስኪ የሚከተለውን እንመልከት፡-



# የተፈጸሙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ትንቢታዊ ጭብጦች አሉ፤ እነርሱም በአለትንፋስ-እግዚአብሔር የተመዘገበው እግዚአብሔር ለእስራኤል የገባው ቃል ኪዳን እና በዚያ ውስጥ የሚገኘው የእርሱ ምሪት ናቸው። ሁለቱም ጭብጦች ከሙሴ (1500 ዓ.ዓ.) ጀምሮ እስከ ሚልክያስ (400 ዓ.ዓ.) ድረስ ለተለያዩ ነቢያት ተሰጥተዋል። አንደኛው የቀድሞውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ አይሁድንና ታሪካቸውን የሚመለከት ሲሆን፥ ሌላኛው የጌታን መሢሕ ይመለከታል። በዕብራይስጥ መሢሕ፥ በግሪክ ክርስቶስ ማለት «የተቀባ» ማለት ነው። ወይም በዘመናዊ አገላለጽ ገዢው ካህን ማለት ነው፤ የእነዚህን ዓላማዎች ያህል በእግዚአብሔር ዓይን ፊት ትኩረት የሚሰጠው ሌላ ርዕስ- ነገር የለም። አሁን ኢየሱስን በተመለከተ ከተነገሩት ትንቢቶች እንጀምር። ለማሳጠር ያህል ጥቂቶች ብቻ ተመርጠዋል፡-

## ኢየሱስን በተመለከተ አንዳንድ ትንቢቶች

ስለ ኢየሱስ የትውልድ ስፍራና ቅደመ-ሕላዌ የተነገረ ትንቢት 700 ዓ.ዓ. አካባቢ፡-

> «አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ እእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን እወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዢ የሚሆን ይወጣልኛል» (ሚክያስ 5፡2)።

ፍጻሜው፡-

> «ዮሴፍም ደግሞ ከዳዊት ቤትና ወገን ስለ ነበረ ከገሊላ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ ቤተ ልሔም ወደምትባል ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ይሁዳ፥ ፀንሳ ከነበረች ከእጮኛው ከማርያም ጋር ይጻፍ ዘንድ ወጣ። በዚያም ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ፥ የበኩር ልጅዋንም ወለደች፥ በመጠቅለያም ጠቀለለችው በእንግዶችም ማደሪያ ስፍራ ስላልነበራቸው በግርግም አስተኛችው» (ሉቃስ 2፡4-7)።

ከድንግል ስለመወለዱ፥ መለኮታዊነቱና የተለየ ልጅነቱ የተነገረ ትንቢት 700 ዓ.ዓ. አካባቢ፡-

«ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» (አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር) (ኢሳይያስ 7፡14)።

«ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፥ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል» (ኢሳይያስ 9፡6)።

ፍጻሜው፡-

«የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች። እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ በስውር ሊተዋት አሰበ። እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፥ እነሆ፥ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለ፡- የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱም ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ። በነቢይ ከጌታ ዘንድ፡- እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም፡- እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው» (ማቴዎስ 1፡18-23)።

ስለመምጫው ጊዜ የተነገረ ትንቢት 520 ዓ.ዓ. አካባቢ፡-

«ዓመፃን ይጨርስ፥ ኃጢአትንም ይፈጽም፥ በደልንም ያስተሰርይ፥ የዘላለምን ጽድቅ ያገባ፥ ራእይንና ትንቢትን ያትም (ከዚያ በኋላ የተጨመረ ትንቢታዊ ራእይ አይደለም)፥ ቅዱስ ቅዱሳኑንም ይቀባ (መቀባት ማለት ከፍ ማድረግ፥ ማንገሥ፥ መቀደስ) ዘንድ በሕዝብህና (የዳንኤል ሕዝብ ማለት አይሁድ) በቅድስት ከተማህ (ኢየሩሳሌም) ላይ ሰባ ሱባዔ (70 በ 7 ዓመታት ለ 490 ዓመታት) ተቀጥሮአል። ስለዚህ እወቅ አስተውልም፤ ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከ አለቃው እስከ መሚሕ ድረስ ሰባት ሱባዔና ስድሳ ሁለት ሱባዔ (49 ዓመታትና 434



ዓመታት) ይሆናል፤ እርሷም በጭንቀት ዘመን ከጎዳናና ከቅጥር ጋር ትሠራለች» (ዳንኤል 9፡24-25)። ነህምያ ከንጉሥ አርጤክስስ (465-425 ዓ.ዓ.) ትእዛዝ ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ ኢየሩሳሌምን መልሶ ለመሥራት በእርግጥ 49 ዓመታት አስፈልገዋል። ትእዛዙንም የሰጠው በ20ኛው የንግሥና ዓመቱ ማለትም በ445 ዓ.ዓ. ነበር (ነህምያ 2፡1፥8)። ኢየሩሳሌም መልሳ የተሠራችው በፈታኝ ጊዜ ውስጥ እንደ ነበረ የነህምያ መጽሐፍ ይናገራል። ለዚህም ምክንያቱ በርካታ ጠላቶች ሥራውን ለማቆም ይጥሩ ስለ ነበር ነው። የቀሩት 434 ዓመታት ወደ 38 ዓ.ም. ያመጡናል። ምንም እንኳ ይህ ክርስቶስ በድል ወደ ኢየሩሳሌም ከገባ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ቢሆንም፥ የሚከተሉትን እውነቶች መመርመር አለብን፡-

ሀ) በጊዜው የነበሩ የታሪክ ጊዜያት እንደ ቅርቦቹ በጣም ትክክለኛ አልነበሩም። ለዚህም ምክንያቱ ትክክለኛ የሆነ የቀን መቁጠሪያ አለመኖርና ለዓመት የተለያየ ርዝማኔ መስጠቱ ነው (እስራኤል ባለ 354 ቀናት የጨረቃ ዓመት ነበራት)።

ለ) ይህ የተገለጸው ክስተት በታሪክ ውስጥ ከማንኛውም ሌላ ነገር ጋር ስለማይገጥም፥ ስሕተቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን ከታሪክ ሊሆን እንደሚችል ድምዳሜ ላይ መድረስ ይኖርብናል።
«ከስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባትም በኋላ መሢሕ ይገደላል፥ በእርሱም ዘንድ ምንም የለም፤ የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፋሉ፤ ፍጻሜውም በጎርፍ ይሆናል፥ እስከ መጨረሻም ድረስ ጦርነት ይሆናል፤ ጥፋትም ተቀጥሮአል» (ዳንኤል 9፡26)።

(«የሚመጣው አለቃ» ሮማዊው ድል አድራጊና የንጉሥ ሄድሪያን ልጅ የሆነው ቲቶ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። እርሱም ከመሚሑ መገደል በኋላ በመምጣት በ70 ዓ.ም. ኢየሩሳሌምንና ቤተ መቅደሷን አጥፍቷል። ከዚያም በኋላ «ጥፋት ተቀጥሮአል» እና እስከዚህ ክፍለ ዘመን ቀጥሏል!)

ለማዳንና ለመፈወስ እንደሚመጣ የተነገረ ትንቢት 700 ዓ.ዓ. አካባቢ፡-

«እነሆ፥ አምላካችሁ በበቀል በእግዚአብሔርም ብድራት ይመጣልና፥ መጥቶም ያድናችኋልና በርቱ፥ አትፍሩ በሉአቸው።

በዚያን ጊዜም የዕውሮች ዓይን ይገለጣል የደንቆሮችም ጆሮ ይከፈታል» (ኢሳይያስ 35፡4-5)።

ፍጻሜው፡-

«ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ» (ማቴዎስ 1፡21)።

«የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና» (ሉቃስ 19፡10)።

«ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፥ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው። ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል።

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና። በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል። ብርሃንም ወደ ዓለም ስለ መጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለ ወደዱ ፍርዱ ይህ ነው። ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፥ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም፤ እውነትን የሚያደርግ ግን ሥራው በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደ ሆነ ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል» (ዮሐንስ 3፡13-21)።

«አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል እርሱም፥ ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፤ ልዩነት የለምና፤ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ። እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስሪያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለ መተው ጽድቁን



ያሳይ ዘንድ ነው ራሱም ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው» (ሮሜ 3፡21-26)።

«እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፤ በእርሱም ደግሞ ወደ ቆምንበት ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል፤ በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን» (ሮሜ 5፡1-2)።

«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም። በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና» (ሮሜ 8፡1-2)።

«ኢየሱስም ቆሞ ወደ እርሱ እንዲያመጡት አዘዘ። በቀረበም ጊዜ፡- ምን ላደርግልህ ትወዳለህ? ብሎ ጠየቀው። እርሱም፡- ጌታ ሆይ፥ አይ ዘንድ ነው አለ። ኢየሱስም፡- እይ፤ እምነትህ አድኖሃል አለው። በዚያን ጊዜም አየ፥ እግዚአብሔርንም እያከበረ ተከተለው። ሕዝቡም ሁሉ አይተው እግዚአብሔርን አመሰገኑ (ሉቃስ 18፡40-43)።

«ኢየሱስም በምኵራቦቻቸው እያስተማረ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር። ዝናውም ወደ ሶርያ ሁሉ ወጣ በልዩ ልዩ ደዌና ሥቃይም ተይዘው የታመሙትን ሁሉ አጋንንትም ያደሩባቸውን በጨረቃም የሚነሣባቸውን ሽባዎችንም ወደ እርሱ አመጡ፥ ፈወሳቸውም» (ማቴዎስ 4፡23-24)።

«ዮሐንስም በወህኒ ሳለ የክርስቶስን ሥራ ሰምቶ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ላከና፡- የሚመጣው አንተ ነህን ወይስ ሌላ እንጠብቅ? አለው። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡- ሄዳችሁ ያያችሁትን የሰማችሁትንም ለዮሐንስ አውሩለት ዕውሮች ያያሉ አንካሶችም ይሄዳሉ ለምጻሞችም ይነጻሉ ደንቆሮችም ይሰማሉ፥ ሙታንም ይነሣሉ ለድሆችም ወንጌል ይሰበካል በእኔም የማይሰናከለው ሁሉ ብፁዕ ነው» (ማቴዎስ 11፡2-6)።

«በመሸም ጊዜ አጋንንት ያደረባቸውን ብዙዎችን ወደ እርሱ አመጡ በነቢዩ በኢሳይያስ፡- እርሱ ድካማችንን ተቀበለ ደዌያችንንም ተሸከመ የተባለው ይፈጸም ዘንድ፥ መናፍስትን በቃሉ አወጣ፥ የታመሙትንም ሁሉ ፈወሰ» (ማቴዎስ 8፡16-17)።

የኢየሱስን ስም በሚመለከት የተነገረ ትንቢት 700 ዓ.ም. አካባቢ፡-

«ደሴቶች ሆይ፥ ስሙኝ፥ እናንተም በሩቅ ያላችሁ አሕዛብ፥ አድምጡ፤ እግዚአብሔር ከማኅፀን ጠርቶኛል፥ ከእናቴም ሆድ ጀምሮ ስሜን አንሥቶአል፤ አፌንም እንደተሳለ ሰይፍ አድርጎአል፥... እስከ ምድር ዳር ድረስ መድኃኒት [በዕብራይስጥ=የሽዋ=ኢያሱ]፥ ይህ በእስራኤል ምድር በተመላለሰበት ዘመን የኢየሱስ ትክክለኛ ስሙ ነበር) ትሆን ዘንድ ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌ ሰጥቼሃለሁ ይላል። የእስራኤል ታዳጊ ቅዱሱም፥ እግዚአብሔር፥ ሰዎች ለሚንቁት ሕዝብም ለሚጠላው ለገዥዎች ባሪያ እንዲህ ይላል» (ኢሳይያስ 49፡1-7 እና ሌሎችም በርካታ ምንባቦች)።

ፍጻሜው፡-

«ልጅም ትወልዳለች (ማርያም)፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ» (ማቴዎስ 1፡21) በማለት መልአኩ ለዮሴፍ ነግሮታል።

በኢሳይያስ ትንቢት ውስጥ የኢየሱስን አምላክነትና ልጅነት የሚገልጸውን ክፍል ከመቃወማቸው በስተቀር፥ እስካሁን በተጠቀሱት ነጥቦች ላይ ሙስሊሞች ከክርስቲያኖች ጋር ሊስማሙ ይችላሉ። ዳሩ ግን እግዚአብሔር የተናገረውን የዚህን ነገር ሚዛን ደፋ ጭብጥ በትንቢትና ፍጻሜው ውስጥ መመርመር አለብን። የሚከተሉት ነገሮች ስሌላ ለማንም ሰው ሊባሉ እንደማይችሉ ልብ በል፡-

1. እጅግ አስደናቂ በሆነ ሁኔታ ተወልዷል።

2. ማንኛውንም ዓይነት በሽታ ይፈውስ ነበር።

3. ማናቸውንም ዓይነት ርኩስ መናፍስት ያስወጣ ነበር።



4. ኃጢአት ያልነካው ቅዱስ ነበር (ሱረቱ 19፡19፤ ዕብራውያን 4፡15፤ 1ኛ ዮሐንስ 3፡5፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21፤ 1ኛ ጴጥሮስ 2፡22፤ ኢሳይያስ 53፡9፤ ወዘተ.)

5. እርሱ የእግዚአብሔር ቃል ነው (ሱረቱ 4፡171፤ ዮሐንስ 1፡1-2፥ 14)

6. እርሱ ከእግዚአብሔር የሆነ መንፈስ ነው (ሱረቱ 4፡171)።

7. ለፍጻሜ ከመድረሱ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት እንዲህ ባለ ዝርዝር ሁኔታ ተተንብዮስታል።

ይህ ብቻ አይደለም። ስለ ኢየሱስ የሕይወት ድምዳሜ በብሉይ ኪዳን የተነገረውን ትንቢትና ፍጻሜውን ቀጥለን እንመለከታለን፡-

ኢየሱስ ትሑት ሆኖ በአህያ ላይ በመቀመጥ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚገባ የተነገረ ትንቢት 480 ዓ.ዓ. አካባቢ፡-

«አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፥ እጅግ ደስ ይበልሽ፥ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ፥ እልል በዪ፤ እነሆ፥ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው ትሑትም ሆኖ በአህያም፥ በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል» (ዘካርያስ 9፡9)።

ፍጻሜው፡-

«ወደ ኢየሩሳሌምም ቀርበው ወደ ደብረ ዘይት ወደ ቤተ ፋጌ ሲደርሱ፥ ያንጊዜ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ላከ፥ እንዲህም አላቸው፡- በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፥ በዚያን ጊዜም የታሰረችን አህያ ውርንጫም ከእርስዋ ጋር ታገኛላችሁ ፈትታችሁ አምጡልኝ። ማንም አንዳች ቢላችሁ፡- ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ፤ ወዲያውም ይሰዳቸዋል።

ለጽዮን ልጅ፡- እነሆ፥ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉአት፡- ተብሎ በነቢይ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ። ደቀ መዛሙርቱም ሄደው ኢየሱስ እንዳዘዛቸው አደረጉ፥ አህያይቱንና ውርንጫዋንም አመጡለት፥ ልብሳቸውንም በእነርሱ ላይ ጫኑ፥ ተቀመጠባቸውም።

ከሕዝቡም እጅግ ብዙዎች ልብሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ፥ ሌሎችም ከዛፍ ጫፍ ጫፉን እየቆረጡ በመንገድ ላይ ያነጥፉ ነበር። የሚቀድሙትም ሕዝብ የሚከተሉትም፦ ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው ሆሣዕና በአርያም እያሉ ይጮኹ ነበር» (ማቴዎስ 21፥ 1-9)።

ስለ ኢየሱስ አልፎ መሰጠት የተነገረ ትንቢት 480 ዓ.ም. አካባቢ፦

«ደግሞ የሰላሜ ሰው የታምንሁበት... በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣ» [መዝሙር (41)፥ 9]።

«እኔም፦ ደስ ብሎአችሁ እንደ ሆነ ዋጋዬን ስጡኝ ያለዚያ ግን ተዉት አልሁ። እነርሱም ለዋጋዬ ሠላሳ ብር መዘኑ። እግዚአብሔርም፦ የተስማሙበትን የከበረውን ዋጋዬን በግምጃ ቤቱ ውስጥ አኑረው አለኝ። እኔም ሠላሳውን ብር ወስጄ በእግዚአብሔር ቤት ባለው በግምጃ ቤቱ ውስጥ አኖርሁት» (ዘካርያስ 11፥ 12-13)።

ፍጻሜው፦

«ከአሥራ ሁለቱም አንዱ የአስቆሮቱ ይሁዳ አሳልፎ ሊሰጠው ወደ ካህናት አለቆች ሄደ። ሲሰሙም ደስ አላቸው ብርም ይሰጡት ዘንድ ተስፋ ሰጡት። በሚመች ጊዜም እንዴት አድርጎ አሳልፎ እንዲሰጠው ይፈልግ ነበር።

«በመሸም ጊዜ ከአሥራ ሁለቱ ጋር መጣ። ተቀምጠውም ሲበሉ ኢየሱስ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ ከእናንተ አንዱ፥ እርሱም ከእኔ ጋር የሚበላው አሳልፎ ይሰጠኛል አለ። እነርሱም ያዝኑ፥ እያንዳንዳቸውም፦ እኔ እሆንን? ይሉት ጀመር። እርሱም መልሶ፦ ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ከእኔ ጋር ወደ ወጭቱ እጁን የሚያጠልቀው ነው። የሰው ልጅስ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይሄዳል ነገር ግን የሰው ልጅ አልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት ያ ሰው ባልተወለደ ይሻለው ነበር አላቸው።

«ወዲያውም ገና ሲናገር ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ይሁዳ መጣ፥ ከእርሱም ጋር ብዙ ሰዎች ሰይፍና ጐመድ ይዘው ከካህናት አለቆችና ከጻፎች ከሽማግሌዎችም ዘንድ መጡ። አሳልፎ የሚሰጠውም፦ የምስመው እርሱ ነው ያዙት ተጠንቅቃችሁም ውሰዱት ብሎ



ምልክት ሰጥቶአቸው ነበር። መጥቶም ወዲያው ወደ እርሱ ቀረበና፦ መምህር ሆይ፥ መምህር ሆይ፥ ብሎ ሳመው እነርሱም እጃቸውን በእርሱ ላይ ጭነው ያዙት» (ማርቆስ 14፥ 10-11፤ 17-21፤ 43-46)።

«በዚያን ጊዜ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ እንደ ተፈረደበት አይቶ ተጸጸተ፥ ሠላሳውንም ብር ለካህናት አለቆችና ለሽማግሎች መልሶ፦ ንጹሕ ደም አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ አለ። እነርሱ ግን፦ እኛስ ምን አግዶን አንተው ተጠንቀቅ አሉ። ብሩንም በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ። የካህናት አለቆችም ብሩን አንሥተው፦ የደም ዋጋ ነውና ወደ መባ ልንጨምረው አልተፈቀደም አሉ። ተማከረውም የሸክላ ሠሪውን መሬት ለእንግዶች መቃብር ገዙበት። ስለዚህ ያ መሬት እስከ ዛሬ ድረስ የደም መሬት ተባለ» (ማቴዎስ 27፥ 3-8)።

ስለ ኢየሱስ በችሎት ፊት መገፋት የተነገረ ትንቢት 700 ዓ.ም. አካባቢ፦

«ጀርባዬን ለገራፊዎች ጉንጬንም ለጠጉር ነጪዎች ሰጠሁ፥ ፊቴንም ከውርደትና ከትፋት አልመለስሁም» (ኢሳይያስ 50፥ 6)።

ፍጻሜው፦

«እነርሱም፦ ሞት ይገባዋል ብለው መለሱ። በዚያን ጊዜ በፊቱ ተፉበት ጐሰሙትም፥ ሌሎችም በጥፊ መትተው፦ ክርስቶስ ሆይ፥ በጥፊ የመታህ ማን ነው? ትንቢት ተናገርልን አሉ» (ማቴዎስ 26፥ 66-68)።

«በዚያ ቆሞ የነበረው ከሎሌዎች አንዱ... ኢየሱስን በጥፊ መታው» (ዮሐንስ 18፥ 22)።

ስለ ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሰቃየትና መሞት የተነገረ ትንቢት 700 ዓ.ዓ. አካባቢ፦

«ባየነውም ጊዜ እንወደው ዘንድ ደም ግባት የለውም። የተናቀ ከሰውም የተጠላ፥ የሕማም ሰው፥ ደዌንም የሚያውቅ ነው ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው፥ እኛም አላከበርነውም።

«በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸከሞአል እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።

«ተጨነቀ ተሣቀየም አፉንም አልከፈተም ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፥ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን (በሁለት ጥፋተኞች መካከል ተሰቅሏል) አደረጉ፥ ከባለጠጎችም ጋር (በሀብታም ሰው መቃብር ተቀብሯል) በሞቱ ሆኖም ግፍን አላደረገም ነበር፥ በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም ነበር።

«እግዚአብሔርም በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ ነፍሱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል፥ ዕድሜውም ይረዝማል፥ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል። ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል፤ ደስም ይለዋል ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን (ሁሉንም አይደለም) ያጸድቃል፥ ኃጢአታቸውንም ይሸከማል። ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፥ ከኃያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፥ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ስጥቶአልና፥ ከዓመፀኞችም ጋር ተቈጥሮአልና እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፥ ስለ ዓመፀኞችም ማለደ» (ኢሳይያስ 53፡2-12)።

በ1000 ዓ.ዓ. አካባቢ፡-

«አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ? እኔን ከማዳንና ከጩኸቴ ቃል ሩቅ ነህ... የሚያዩኝ ሁሉ ይላገጡብኛል፤ ራሳቸውን እየነቀነቁ በከንፈሮቻቸው እንዲህ ይላሉ፡- በእግዚአብሔር ተማመነ፥ እርሱንም ያድነው፤ ቢወድደውስ ያድነው። አንተ ግን ከሆድ አውጥተኸኛልና፥ በእናቴ ጡት ሳለሁም በአንተ ታመንሁ... እንደ ነጣቂና እንደሚጮህ አንበሳ በላዬ አፋቸውን ከፈቱ። እንደ ውኃ



ፈሰስሁ አጥንቶቼም ሁሉ ተለያዩ፤ ልቤ እንደ ሰም ሆነ፥ በአንጀቴም መካከል ቀለጠ። ኃይሌ እንደ ገል ደረቀ፥ በጒሮሮዬም ምላሴ ተጣጋ፥ ወደ ሞትም አሸዋ አወረድኸኝ። ብዙ ውሾች ከበበውኛልና፤ የክፉተኞች ጉባኤም ያዘኝ፤ እጆቼንና እግሮቼን ቸንከሩኝ። አጥንቶቼ ሁሉ ተቈጠሩ፤ እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም። ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፥ በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ» [መዝሙር (22)፡1፥7-9፥13-18] ።

ፍጻሜው፡-

«ኢየሱስም መለሰ፡- መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን፥ ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም አለው። ጲላጦስም፡- እንግዲያ ንጉሥ ነህን? አለው። ኢየሱስም መለሰ፡- እኔ ንጉሥ እንደ ሆንሁ አንተ ትላለህ። እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል አለው። ጲላጦስ፡- እውነት ምንድር ነው? አለው።

«ይህንም ብሎ ዳግመኛ ወደ አይሁድ ወጥቶ፡- እኔስ አንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትም። ነገር ግን በፋሲካ አንድ ልፈታላችሁ ልማድ አላችሁ፤ እንግዲህ የአይሁድን ንጉሥ ልፈታላችሁ ትወዳላችሁን? አላቸው። ሁሉም ደግመው፡- በርባንን እንጂ ይህን አይደለም እያሉ ጮኹ። በርባን ግን ወንበዴ ነበረ።

«በዚያን ጊዜም ጲላጦስ ኢየሱስን ይዞ ገረፈው። ወታደሮችም ከእሾህ አክሊል ጐንጕነው በራሱ ላይ አኖሩ ቀይ ልብስም አለበሱት፤ እየቀረቡም፡- የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፥ ሰላም ለአንተ ይሁን ይሉት ነበር፤ በጥፊም ይመቱት ነበር። ጲላጦስም ደግሞ ወደ ውጭ ወጥቶ፡- እነሆ፥ አንዲት በደል ስንኳ እንዳላገኘሁበት ታውቁ ዘንድ እርሱን ወደ ውጭ አወጣላችኋለሁ አላቸው። ኢየሱስም የእሾህ አክሊል ደፍቶ ቀይ ልብስም ለብሶ ወደ ውጭ ወጣ። ጲላጦስም፡- እነሆ ሰውዬው አላቸው። የካህናት አለቆችና ሎሌዎች ባዩትም ጊዜ፡- ስቀለው ስቀለው እያሉ ጮኹ። ጲላጦስም፡- እኔስ አንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትምና እናንተ ወስዳችሁ ስቀሉት አላቸው። አይሁድም መለሰው፡- እኛ ሕግ አለን፥ እንደ ሕጋችንም ሊሞት

አለን፥ እንደ ሕጋችንም ሊሞት ይገባዋል፥ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎአልና አሉት። ስለዚህ ጲላጦስ ይህን ነገር በሰማ ጊዜ እጅግ ፈራ፤ ተመልሶም ወደ ገዡ ግቢ ገባና ኢየሱስን፡- አንተ ከወዴት ነህ? አለው። ኢየሱስ ግን አንድ እንኳ አልመለሰለትም። ስለዚህ ጲላጦስ፡- አትነግረኝምን? ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ ወይም ልፈታህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? አለው። ኢየሱስም መልሶ፡- ከላይ ካልተሰጠህ በቀር በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን ባልነበረህም፤ ስለዚህ* ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ኃጢአቱ የባሰ ነው አለው።

«ከዚህ በኋላ ጲላጦስ ሊፈታው ፈለገ፤ ነገር ግን አይሁድ፡- ይህንስ ብትፈታው የቄሣር ወዳጅ አይደለህም፤ ራሱን ንጉሥ የሚያደርግ ሁሉ የቄሣር ተቃዋሚ ነው እያሉ ጮኹ። ጲላጦስም ይህን ነገር ሰምቶ ኢየሱስን ወደ ውጭ አወጣው፥ በዕብራይስጥም ገበታ በተባለው ጸፍጸፍ በሚሉት ስፍራ በፍርድ ወንበር ተቀመጠ። ለፋሲካም የማዘጋጀት ቀን ነበረ፤ ስድስት ሰዓትም የሚያህል ነበረ፤ አይሁድንም፡- እነሆ ንጉሣችሁ አላቸው። እነርሱ ግን፡- አስወግደው፥ አስወግደው፥ ስቀለው እያሉ ጮኹ። ጲላጦስም፡- ንጉሣችሁን ልሰቀለውን? አላቸው። የካህናት አለቆችም፡- ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም ብለው መለሱለት። ስለዚህ በዚያን ጊዜ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው።

«ኢየሱስንም ይዘው ወሰዱት፤ መስቀሉንም ተሸክሞ በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደ ተባለው የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሉት ወጣ። በዚያም ሰቀሉት፥ ከእርሱም ጋር ሌሎች ሁለት፥ አንዱን በዚህ አንዱን በዚያ ኢየሱስንም በመካከላቸው ሰቀሉ። ጲላጦስም ደግሞ ጽሕፈት ጽፎ በመስቀሉ ላይ አኖረው፤ ጽሕፈቱም፡- የአይሁድ ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ የሚል ነበር። ኢየሱስም የተሰቀለበት ስፍራ ለከተማ ቅርብ ነበረና ከአይሁድ ብዙዎች ይህን ጽሕፈት አነበቡት፤ በዕብራይስጥና በሮማይስጥ በግሪክም ተጽፎ ነበር። ስለዚህ የአይሁድ ካህናት አለቆች ጲላጦስን፡- እርሱ፡- የአይሁድ ንጉሥ ነኝ እንዳለ እንጂ የአይሁድ ንጉሥ ብለህ አትጻፍ አሉት። ጲላጦስም፡- የጻፍሁትን ጽፌአለሁ ብሎ መለሰ።



«ጭፍሮችም ኢየሱስን በሰቀሉት ጊዜ ልብሶቹን ወስደው ለእያንዳንዱ ጭፍራ አንድ ክፍል ሆኖ በአራት ከፋፈሉት፤ እጀ ጠባቡን ደግሞ ወሰዱ። እጀ ጠባቡም ከላይ ጀምሮ ወጥ ሆኖ የተሠራ ነበረ እንጂ የተሰፋ አልነበረም። ስለዚህ እርስ በርሳቸው፡- ለማን እንዲሆን በእርሱ ዕጣ እንጣጣልበት እንጂ አንቅደደው ተባባሉ። ይህም፡- ልብሴን እርስ በርሳቸው ተከፋፈሉ በእጀ ጠባቤም ዕጣ ተጣጣሉበት የሚለው የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው።

«ጭፍሮችም እንዲህ አደረጉ። ነገር ግን በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ፥ የእናቱም እኅት፥ የቀለዮጳም ሚስት ማርያም፥ መግደላዊትም ማርያም ቆመው ነበር። ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን፡- አንቺ ሴት፥ እነሆ ልጅሽ አላት። ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን፡- እናትህ እነኋት አለው። ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት።

«ከዚህ በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉ እንደ ተፈጸመ አውቆ የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ፡- ተጠማሁ አለ። በዚያም ሆምጣጤ የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር፤ እነርሱም ሆምጣጤውን በሰፍነግ ሞልተው በሁሶፕም አድርገው ወደ አፉ አቀረቡለት። ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ፡- ተፈጸመ አለ፥ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ።

«አይሁድም የማዘጋጀት ቀን ስለ ሆነ ያ ሰንበት ትልቅ ነበረና ሥጋቸው በሰንበት በመስቀል ላይ እንዳይኖር፥ ጭናቸውን ሰብረው እንዲያወርዱአቸው ጲላጦስን ለመኑት። ጭፍሮችም መጥተው የፊተኛውን ጭን ከእርሱም ጋር የተሰቀለውን የሌላውን ጭን ሰበሩ፤ ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን እርሱ ፈጽሞ እንደ ሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም፤ ነገር ግን ከጭፍሮች አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደምና ውኃ ወጣ። ያየውም መስክሮአል፤ ምስክሩም እውነት ነው፤ እናንተም ደግሞ ታምኑ ዘንድ እርሱ እውነት እንዲናገር ያውቃል። ይህ የሆነ፡- ከእርሱ አጥንት አይሰበርም የሚል የመጽሐፉ ቃል እንዲፈጸም ነው። ደግሞም ሌላው መጽሐፍ፡- የወጉትን ያዩታል ይላል (ዮሐንስ 18፡36-19፡37)።

ስለ ኢየሱስ ትንሣኤ የተነገረ ትንቢት 1000 ዓ.ዓ. አካባቢ፡-

«ሁልጊዜ እግዚአብሔርን በፊቴ አየዋለሁ፤በቀኜ ነውና አልታወከም። ስለዚህ ልቤን ደስ አለው ምላሴም ሐሤት አደረገች፤ሥጋዬ ደግሞ በተስፋ ታድራለች፤ነፍሴን በሲኦል (እዚህ ላይ ሲዖል = የምድር ታች መቃብር) አትተዋትምና፥ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም» [መዝሙር (16)፡8-10]።

ፍጻሜው፡-

«ነገር ግን ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው ከእነርሱም ጋር አንዳንዶቹ ወደ መቃብሩ እጅግ ማልደው መጡ። ድንጋዩንም ከመቃብሩ ተንከባሎ አገኙት፥ ገብተውም የጌታን የኢየሱስን ሥጋ አላገኙም። እነርሱም በዚህ ሲያመነቱ፥ እነሆ፥ ሁለት ሰዎች የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሰው ወደ እነርሱ ቀረቡ፤ ፈርተውም ፊታቸውን ወደ ምድር አቀርቅረው ሳሉ፥ እንዲህ አሉአቸው፡- ሕያውን ከሙታን መካከል ስለ ምን ትፈልጋላችሁ? ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም። የሰው ልጅ በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ሊሰጥና ሊሰቀል በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ ግድ ነው እያለ ገና በገሊላ ሳለ ለእናንተ እንደ ተናገረ አስቡ። ቃሎቹንም አሰቡ፥ ከመቃብሩም ተመልሰው ይህን ሁሉ ለአሥራ አንዱና ለሌሎች ሁሉ ነገሩአቸው። ይህንም ለሐዋርያት የነገሩአቸው መግደላዊት ማርያምና ዮሐና የያዕቆብም እናት ማርያም ከእነርሱም ጋር የነበሩት ሌሎች ሴቶች ነበሩ። ይህም ቃል ቅዠት መስሎ ታያቸውና አላመኑአቸውም» (ሉቃስ 24፡1-11)።

ስለ ዕርገቱ የተነገረ ትንቢት 1000 ዓ.ዓ. አካባቢ፡-

«እግዚአብሔር ጌታዬን፡- ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው» [መዝሙር (110)፡1]።

ፍጻሜው፡-



«እነርሱም በተሰበሰቡ ጊዜ፡- ጌታ ሆይ፥ በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን? ብለው ጠየቁት። እርሱም፡- አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ። ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው። እርሱም ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኵር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ፥ እነሆ፥ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በእጠገባቸው ቆሙ፤ ደግሞም፡- የገሊላ ሰዎች ሆይ፥ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፥ እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው። (የሐዋርያት ሥራ 1፡6-11)።

ገና ያልተፈጸመው የእስራኤልን ንስሐ መግባትና ወደ ኢየሱስ መመለስ የሚናገር ትንቢት 480 ዓ.ዓ. አካባቢ፡-

«በዳዊትም ቤት ላይ፥ በኢየሩሳሌምም በሚኖሩት ላይ፥ የሞገስንና የልመናን መንፈስ እፈስሳለሁ ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ ሰውም ለአንድያ ልጁ እንደሚያለቅስ ያለቅሱለታል ሰውም ለበኵር ልጁ እንደሚያዝን በመራራ ኅዘን ያዝኑለታል» (ዘካርያስ 12፡10)።

ሰዎች ልጁ ኢየሱስን ከአባቱ ከእግዚአብሔር ለመለየት የሚፈልጉበትን የአሁኑን ሁኔታችንን በተመለከተ የተነገረ ትንቢት 1000 ዓ.ዓ. አካባቢ፡-

«የምድር ነገሥታት ተነሡ፥ አለቆችም በእግዚአብሔርና በመሢሑ ላይ (የተቀባ = መሢሕ = ክርስቶስ) እንዲህ ሲሉ ተማከሩ፡- ማሰርያቸውን እንበጥስ፥ ገመዳቸውንም ከእኛ እንጣል... ትእዛዙን እናገራለሁ እግዚአብሔር አለኝ፡- አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወለድሁህ። ለምነኝ፥ አሕዛብን ለርስትህ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ እሰጥሃለሁ... ተግሣጹን ተቀበሉ ጌታ እንዳይቆጣ እናንተም በመንገዱ እንዳትጠፉ፥ ቍጣው ፈጥና ትነድዳለችና። በእርሱ የታመኑ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው» (መዝሙር 2፡2-3፤ 7-8፤ 12)።

በዓለም ውስጥ የትኛውም ሃያሲ እነዚህን የተፈጸሙ ትንቢቶች ማብራሪያ በመስጠት ሊያናንቃቸው አይችልም። ይህ ስታሪክ ሁሉና ከሃይማኖት መጻሕፍት ሁሉ የተለየ እንግዳ ነገር ነው። እርሱም ከመልእክቱ ጋር ተያይዞ ለሰው ልጅ የተላለፈ የእግዚአብሔር ማኅተም ነው። ይኸውም ማንኛውም ትጉህና ቅን አንባቢ፣ ሃይማኖተኞች የራሳቸውን አመለካከቶች በሌሎች ላይ ለመጫን ፈልገው ያዘጋጁትን መጽሐፍ እያነበበ እንዳልሆነ ሙሉ ለሙሉ እርግጠኛ እንዲሆን ነው። ከላይ በቀረበው መረጃ ላይ ማንም ሰው መጽሐፍ ቅዱስ ተለውጧል ብሎ ለመናገር ሊደፍር አይችልም።

ይሁንና ምናልባት ብሉይ ኪዳን በከፊል እንኳ ቢሆን ይህንን «ትንቢት» «ለማቅረብ» ሲባል ከአዲስ ኪዳን በኋላ ተጽፎ ይሆን? የሚል ጥያቄ ይነሣ ይሆናል። ከበርካታ ምክንያቶች ሳቢያ ይህ የማይታሰብ ነገር ነው። አይሁዶች መጽሐፍ ቅዱስን በከፍተኛ ጥንቃቄ ይጠብቁ ነበር። አነርሱ ራሳቸውም ቢሆን፣ ከራሳቸው እምነትና ልምድ ጋር ይጋጩ ስለ ነበር፣ በቅዱስ መጽሐፋቸው ውስጥ እነዚህ ትንቢቶች በመኖራቸው ደስተኞች አልነበሩም። ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ምንባቦች መካከል በየስንበቱ በማንኛውም ምኩራብ በሚደረግ ንባብ ላይ እስመደመጣቸው ራሱ የሚጠቁመው ነገር አለ። ከዚህም በተጨማሪ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ብሉይ ኪዳን በስፋት ከመሠራጨቱም በላይ ከ200-100 ዓ.ም. መካከል ወደ ግሪክ ተተርጉሞአል። ከዚያ ወዲያ በስፋት የተሠራጨውን መጽሐፍ መልሶ መከለስና ማሳተም በፍጹም የማይቻል ነገር ነው። በተጨማሪም ከክርስትና ቀደምትነት ያላቸው የብሉይ ኪዳን ቅጂዎች እነዚህን ትንቢቶች አካተው ይዘው ከእጃችን ይገኛሉ።

ከአዲስ ኪዳንስ ጋር እንዲስማማ አድርጎ ማዘጋጀት አይቻልምን? ክርስቶስ እነዚህን ነገሮች ተገንዝቦ ሆን ብሎ ሊፈጽማቸው አልኖረም? ይህንንስ ያቀናጁት ደቀ መዛሙርቱ አልነበሩምን?

እነዚህ ክስተቶች ከማናቸውም ምስክሮች ርቀው በድብቅ አልተፈጸሙም። የተፈጸሙት በገሃድ በመሆኑ እስራኤል ሁሉ ያውቃቸው ነበር። እነዚህ ነገሮች ማታለያዎች ቢሆኑ ኖሮ፣ ወንጌሉ በአራት ዘጋቢዎች አማካኝነት ሲመዘገብና የወንጌሉም ትምህርት በመልእክቶች ውስጥ ሲብራራ



ጠቅላላው ሕዝበ-እስራኤል በተቃውሞ ይነሣ ነበር። በአንጻሩ ግን ሕዝቡ በርካታ የዓይን ምስክሮችን እንዲጠይቅ በሐዋርያት ተገፋፍቷል።

ጳውሎስ ስተከሰስ ጊዜ በንጉሥ አግሪጳ ፊት እንዲህ ብሏል:-

> «በእርሱ ፊት ደግሞ ስግልጥ የምናገረው ንጉሥ ይህን ነገር ያውቃል፤ ከዚህ ነገር አንዳች እንዳይሰወርበት ተረድቼአለሁና፤ ይህ በስውር የተደረገ አይደለምና» (የሐዋርያት ሥራ 26:26)።

እንዲሁም ጴጥሮስ በበዓለ ኀምሳ ዕለትና ከስቅለቱ ብዙም ሳይስነብት እጅግ ብዙ ለሆነ የአይሁድ ሕዝብ እንዲህ ብሏል:-

> «የእስራኤል ሰዎች ሆይ፣ ይህን ቃል ስሙ፤ ራሳችሁ እንደምታውቁ፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች ስምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ፤ እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው እሳቡና በቀደመው እውቀቱ ተሰጥቶ በዓመፀኞች እጅ ስቅላችሁ ገደላችሁት። እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው፣ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና» (የሐዋርያት ሥራ 2:22-24)።

አይሁዶች የኢየሱስን የመስቀል ላይ ሞት እንዳላስተባበሉ እንገነዘባለን። ያስተባበሉትና የካዱት ነገር ቢኖር መሚሕነቱን ነው።

> ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጴጥሮስና ሌሎችም ሐዋርያት ይህንን በማስተማራቸው ወደ ወኅኒ ወርደው ነበር። በአይሁድ ሸንጎ በተጠየቁ ጊዜም እንዲህ ብለው መለሱ:-

> «እናንተ በእንጨት ላይ ስቅላችሁ የገደላችሁትን ኢየሱስን የአባቶቻችን አምላክ አስነሣው፤ ይህን እግዚአብሔር፣ ለእስራኤል ንስሐን የኃጢአትንም ስርየት ይስጥ ዘንድ፣ ራስም መድኃኒትም አድርጎ በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው። እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን፣ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የስጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው» (የሐዋርያት ሥራ 5:30-32)።

እንደዚሁም ጳውሎስ ድርብ ዋስትናዎችን ጠቅሷል፡- «መጽሐፍ እንደሚል» (የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች) እና በዚያን ጊዜ በሕይወት የነበሩና ሊጠየቁ የሚችሉ የበርካታ ምስክሮች መረጃ ነው። ይህም ለእስራኤሎች ብዙም አስፈላጊ ስላልነበር፥ የተጠቀሰው ለግሪክ ሰዎች ነው፡-

> «እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ፡- መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፥ ተቀበረም፥ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፥ ለኬፋም (ጴጥሮስ) ታየ በኋላም ለአሥራ ሁለቱ፤ ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነርሱም የሚበዙቱ እስከ አሁን አሉ አንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል፤ ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ ኋላም ለሐዋርያት ሁሉ ታየ» (1ኛ ቆሮንቶስ 15፡3-7)።

ይህም ትንሽ ቆይቶ እንደገና በሐዋርያው ጴጥሮስ ድጋፍ አግኝቷል። እርሱም የዓይን ምስክሮች ዘገባ ላይ ትኩረት ከሰጠ በኋላ የተፈጸሙትን ትንቢቶች «የበለጡ ማረጋገጫዎች» አድርጎ ያቀርባል። ምስክር ሊዋሽ ይችላል። እንዲያውም ብዙ ምስክሮች ሊዋሹ ይችላሉ። ዳሩ ግን በትንቢትና ፍጻሜው ውስጥ ምንም መዛባት አይኖርም።

> «የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልሃት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ። ከገናናው ክብር፡- በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ያ ድምፅ በመጣለት ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ክብርንና ምስጋናን ተቀብሎአልና እኛም በቅዱሱ ተራራ ከእርሱ ጋር ሳለን ይህን ድምጽ ከሰማይ ሲወርድ ሰማን። ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን ምድርም እስኪጠባ ድረስ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪወጣ ድረስ፥ ሰው በጨለማ ስፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየተጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ። ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ» (2ኛ ጴጥሮስ 1፡16-21)።



ከወንጌል ዘጋቢዎች መካከል ብቸኛ ምሁር የሆነው ሉቃስ በሚከተለው ሁኔታ ዘገባውን ይጀምራል፡-

> «ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን፥ በኛ ዘንድ ስለ ተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለ ሞከሩ፥ እኔ ደግሞ ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ» (ሉቃስ 1፡1-4)።

ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ፥ ኢየሱስ ስለሚመጣበት ጊዜ የተነገረውን ትንቢት፥ የልደቱን ሁኔታ (ከድንግል)፥ በጊዜውና በወቅቱ ያልተለመደ በመሆኑ ለተናገረው ነቢይ እንኳ የማይከስትለትን ወይም የአሟሟቱን መንገድ (በስቅላት) መርጧል ለማለት እንዴት ይቻላል! ደግሞስ ተአምራቶቹን እንዴት ሊሠራ ይችል ነበር?

በቀደመው አሳብ መሠረት፥ ቀጥሎ የተመለከቱትን የሚስተር ጁማልን ቃሎች (ገጽ20-21) የሚመስሉ የሙስሊሞችን አባባሎች ችላ ብለን መተው አለብን፡-

> «በአንድ ወቅት መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነበረ . . . አሁን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ግን በማንኛውም የአስተሳሰብ ደረጃ በእስትንፋስ-እግዚአብሔር የተሰጠ የእግዚአብሔር ቃል ተብሎ ሊጠራ አይችልም . . . እምነት መጽሐፍ ቅዱስን ከነስሕተቶቹ እና ከነማይመስሉ ነገሮቹ ሙሉ በሙሉ መቀበልን ይጠይቃል። በሌላ በኩል አስተውሎት፥ ስብአዊ ማስተዋልን የሚያጥላሉ ነገሮችን ከመቀበል ወደ ኋላ ይላል» (እባክህ ተጨማሪ ታሪካዊ መረጃዎችን በገጽ 145 ተመልከት)።

ቁርዓን በእግዚአብሔር መንፈስ የተሰጠ ነው ለሚለው ድጋፍ፥ ቀደም ሲል በመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተጠቀሱት ያለ ጠንካራና አሳማኝ መረጃ በመሰብሰብና በማቅረብ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የተለወጠና ኢ-ተአማኒ ነው ስለ መባሉ አመለካከቶቹን እንዲገመግም ማንኛውንም እውነተኛ ሙስሊም እናደፋፍራለን።

ቁርዓን ተቀባይነት ኖሮት ከፍጻሜ የደረሰ አንድም ትንቢት የለውም። እንዲሁም በእስልምና ውስጥ ለማናቸውም የነቢይነት ምልክቶች ድጋፍ የሚሆኑ ተቀባይነት ያላቸው የመረጃ ምስክሮች አናገኝም። ቁርዓን መለኮታዊ ምንጭ እንዳለው ያቀረበው አንድ ሰው ብቻ ነው። ተከታዮቹን ለማሳመን መብቃቱ ሌላ ጉዳይ ነው። ይኼ ግን በራሱ ተቀባይነት የሌለው መረጃ ነው። ምክንያቱም በሺህ የሚቆጠሩ ሌሎች የሃይማኖት ቡድን መሥራቾችም ተመሳሳይ የሆነ ነገር አድርገዋል።

እንደዚህ ዓይነት ዐረፍተ ነገሮች ቁጣ ወይም ጥርጣሬ ሊቀሰቅሱና አለመቀበልን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ እናውቃለን። እዚህ ላይ የአልቀበልም ባይነቱ መሠረት ግን መንፈሳዊነትም አዋቂነትም ሳይሆን፥ በስሜቶች ወይም በፍርሃት ውስጥ መስመጥ ነው። እንዲሁም በእንደዚህ ዓይነት ዐረፍተ ነገሮች የሙስሊም ወዳጆቻችንን ስሜቶች በመጉዳታችን እናዝናለን። ለእግዚአብሔር እውነትና በሕያው እግዚአብሔር ፊት ስላለህ መንፈሳዊ ስፍራ በጣም ግድ እንደሚለን ተረዳልን።

## አይሁዶችን በተመለከተ ከተነገሩ አንዳንድ ትንቢቶች ትውውቅ

ከታሪክ፥ በተለይም ከአይሁድ ታሪክ ጋር ትውውቅ ያለው ማንም ሰው፥ ከብዙ ዓመታት በፊት በነቢያት የተነገረውንና ራሱ ክስተቱን ለማቀናጀት አይቸገርም።

በ1500 ዓ.ዓ. ሙሴ በመንፈስ ተመርቶ የሚከተለውን ተናግሯል:-

> «የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ፥ ዛሬም ያዘዝሁህን ትእዛዙን ሁሉ ብታደርግ ብትጠብቅም፥ አምላክህ እግዚአብሔር ከምድር አሕዛብ ሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያደርግሃል። የአምላክህንም የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ እነዚህ በረከቶች ሁሉ ይመጡልሃል ያገኙህማል። አንተ በከተማ ቡሩክ ትሆናለህ፥ በእርሻም ቡሩክ ትሆናለህ። የሆድህ ፍሬ፥ የምድርህም ፍሬ፥ የከብትህም ፍሬ፥ የላምህም ርቢ፥ የበግህም ርቢ ቡሩክ ይሆናል። እንቅብህና ቡሃቃህ ቡሩክ ይሆናል። አንተም በመግባትህ ቡሩክ ትሆናለህ፥ በመውጣትህም ቡሩክ ትሆናለህ።
>
> «ነገር ግን የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል ባትሰማ፥ ዛሬም ያዘዝሁህን ሥርዓቱንና ትእዛዙን ሁሉ ባትጠብቅ ባታደርግም፥



> እነዚህ መርገሞች ሁሉ ይመጡብሃል ያገኙህማል። በከተማ ርጉም ትሆናለህ፥ በእርሻም ርጉም ትሆናለህ። እንቅብህና ቡሃቃህ ርጉም ይሆናል። የሆድህ ፍሬ፥ የምድርህም ፍሬ፥ የላምህም ርቢ፥ የበግህም ርቢ ርጉም ይሆናል። አንተ በመግባትህ ርጉም ትሆናለህ፥ በመውጣትህም ርጉም ትሆናለህ። እኔን ስለ ተውኸኝ፥ ስለ ሥራህ ክፋት፥ እስከትጠፋ ፈጥነህም እስክታልቅ ድረስ በምትሠራው ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር መርገምን፥ ሽሽትን፥ ተግሣጽን ይሰድድብሃል።
>
> «እግዚአብሔርም አንተን በአንተም ላይ የምታነግሠውን ንጉሥ አንተና አባቶችህ ወዳላወቃችኋቸው ሕዝብ ይወስድሃል፤ በዚያም ሌሎችን የእንጨትና የድንጋይ አማልክት ታመልካለህ። እግዚአብሔርም በሚያገባህ በአሕዛብ መካከል ሁሉ ድንጋጤ ምሳሌም ተረትም ትሆናለህ። እጅግ ዘር ወደ እርሻ ታወጣለህ አንበጣም ይበላዋልና ጥቂት ትሰበስባለህ። ወይን ትተክላለህ ታበጀውማለህ ትልም ይበላዋልና ከእርሱ ምንም አትሰበስብም፥ የወይን ጠጁንም አትጠጣም። የወይራ ዛፍ በአገርህ ሁሉ ይሆንልሃል፤ ወይራህም ይረግፋልና ዘይቱን አትቀባም። ወንዶችና ሴቶች ልጆች ይወለዱልሃል፤ በምርኮም ይሄዳሉና ለአንተ አይሆኑልህም። ዛፍህን ሁሉ የምድርህንም ፍሬ ኩብኩባ ይወርሰዋል። በአንተ መካከል ያለ መጻተኛ በአንተ ላይ ከፍ ከፍ ይላል፥ አንተም ዝቅ ዝቅ ትላለህ። እርሱ ያበድርሃል፤ አንተ ግን አታበድረውም፤ እርሱ ራስ ይሆናል፥ አንተም ጅራት ትሆናለህ። የአምላክህንም የእግዚአብሔርን ቃል ስላልሰማህ፥ ያዘዘህንም ትእዛዙንና ሥርዓቱን ስላልጠበቅህ፥ እስክትጠፋ ድረስ እነዚህ መርገሞች ሁሉ ይወርዱብሃል፥ ያሳድዱህማል፥ ያገኙህማል። በአንተም በልጅ ልጅህም ላይ ለዘላለም ለምልክትና ለድንቅ ይሆናሉ።
>
> «ሁሉን አብዝቶ ስለ ሰጠህ አምላክህን እግዚአብሔርን በፍሥሐና በሐሤት አላመለክህምና በራብና በጥማት በዕራቁትነትም ሁሉንም በማጣት እግዚአብሔር ለሚልክብህ ለጠላቶችህ ትገዛለህ፤ እስኪያጠፋህም ድረስ በአንገትህ ላይ የብረት ቀንበር ይጭናል። እግዚአብሔር ቋንቋቸውን የማታውቀውን፥ ፊታቸው የደነደነውን፥ ሽማግሌውንም የማያፍሩትን፥ ሕፃኑንም የማይምሩትን ሕዝብ ንስር

እንደሚበርር ከሩቅ አገር ከምድር ዳር ያመጣብሃል። እስክትጠፉ ድረስ የከብትህን ፍሬ የምድርህንም ፍሬ ይበላሉ፤ እስኪያጠፉህም ድረስ እህልን የወይንም ጠጅ ዘይትንም የላምህንና የበግህን ርቢ አይተዉልህም። በአገርህ ሁሉ ያሉ፥ ትታመንባቸው የነበሩ፥ የረዘሙ የጸኑም ቅጥሮች እስኪፈርሱ ድረስ፥ በከተሞችህ ደጆች ሁሉ ከብበው ያስጨንቁሃል፤ አምላክህም እግዚአብሔር በሰጠህ ምድር ሁሉ በደጆች ሁሉ ከብበው ያስጨንቁሃል። ጠላቶችህም ከብበው ባስጨነቁህና መከራ ባሳዩህ ጊዜ አምላክህ እግዚአብሔር የሚሰጥህን የሆድህን ፍሬ የወንዶችና የሴቶች ልጆችህን ሥጋ ትበላለህ። በአንተ ዘንድ የተለሳለሰና በቅምጥልነት ሁልጊዜ ይኖር የነበረ ሰው በወንድሙ፥ አቅፋውም በምትተኛ በሚስቱ፥ በቀሩትም ልጆች ይቀናል፤ በደጆችህ ሁሉ ውስጥ ጠላቶችህ ከብበው ባስጨነቁህና መከራ ባሳዩህ ጊዜ ሌላ ነገር የቀረው የለምና ከሚበላው ከልጆቹ ሥጋ ለአንዱ አይሰጥም።

«ደግሞም ይህ ሕግ ባለበት መጽሐፍ ውስጥ ያልተጻፈውን ደዌ ሁሉ መቅሠፍትም ሁሉ እስከትጠፋ ድረስ እግዚአብሔር ያመጣብሃል። የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ቃል አልሰማችሁምና ከብዛታችሁ የተነሣ እንደ ሰማይ ከዋክብት የነበረው ቁጥራችሁ ጥቂት ሆኖ ይቀራል። እግዚአብሔርም በጎ ያደርግላችሁ ዘንድ ያበዛችሁም ዘንድ ደስ ይለው እንደ ነበረ፥ እንዲሁ እግዚአብሔር ሲያጠፋችሁ ሲያፈርሳችሁም ደስ ይለዋል፤ ትወርሱአትም ዘንድ ከምትገቡባት ምድር ትነቀላላችሁ። እግዚአብሔርም ከምድር ዳር እስከ ዳርቻዋ ድረስ ወዳሉ አሕዛብ ሁሉ ይበትንሃል፤ በዚያም አንተና አባቶችህ ያላወቃችኋቸውን ሌሎችን አማልክት፥ እንጨትንና ድንጋይን፥ ታመልካለህ። በእነዚያም አሕዛብ መካከል ዕረፍት አታገኝም፥ ለእግርህም ጫማ ማረፊያ አይሆንም፤ በዚያም እግዚአብሔር ተንቀጥቃጭ ልብ፥ ፈዛዛ ዓይን፥ ደካማም ነፍስ ያመጣብሃል። ነፍስህም ታመነታለች፤ ሌሊትና ቀንም ትፈራለህ፥ በሕይወትህም አትታመንም፤ አንተ ስለ ፈራህበት ስለ ልብህ ፍርሃት፥ በዓይንህም ስለምታየው አስተያየት፥ ማለዳ፡- መቼ ይመሻል? ትላለህ፤ ማታም፡- መቼ ይነጋል? ትላለህ?» (ዘዳግም 28፡1-6፤ 15-20፤ 36-55፤ 61-67)።



በዚህ ዓለም ውስጥ የአይሁዳውያን ስኬታማነት የሚያስቀና መሆኑን እንመለከታለን። ፀረ-ሴማዊነት እንቅስቃሴ ሁሉ የመነጨው ከዚሁ ነው። አይሁዶች በንግድ፥ በሥነ-ጥበብና በሳይንስ የተዋጣላቸው ናቸው። ከሁሉም የበለጠ ቁጥር ያላቸው የኖቤል ተሸላሚዎችን አበርክተዋል። ለምን? ወደ ታሪካቸው መመልከቱ ይረዳናል።

## የእነዚህን ትንቢቶች ፍጻሜ የሚያሳይ የአይሁድ ታሪክ በአጭሩ

እስኪ የእዚህን ሕዝብ ታሪክ በተቻለ ዓቅም በአጭሩ እንቃኝ። በታሪክ የአጥቢያ ዘመን ማለትም በ1936 ዓ.ዓ. ከጥፋት ውኃ በኋላ 412 ዓመታት ሲቆጠር፥ እግዚአብሔር ሴማዊውን አብርሃምን የአዲሱ ሕዝብ አባት እንዲሆን ከከለዳውያን አገር ከዑር ከተማ ጠራው፡-

> «እግዚአብሔርም አብራምን አለው፡- ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባቶችህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ። ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን፤ የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ» (ዘፍጥረት 12፡1-3)።

ይህ በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ የተስፋ ቃል እንዳልሆነና በመጽሐፍ ቅዱሰም ውስጥ በየትም ስፍራ ይህን የሚሽር ምንባብ እንደሌለ ልብ በል። በሁኔታዎች የማይወሰነው የተስፋ ቃል ለልጁ ለይስሐቅና ለልጅ ልጁ ለያዕቆብም ተረጋግጧል። የአብርሃም ትውልዶች በቁጥር 70 ሲሞሉ ወደ ግብጽ ተሰደው ጌሴም በተባለች ስፍራ ተቀመጡ። በዚያም በዘፍጥረት 15፡13-14 እንደ ተተነበየው ለ400 ዓመታት ያህል በባርነት ለመሥራት ተገደዱ።

በአይሁድ ታሪክ ውስጥ ቀጣዩ ታላቅ ከስተት ዘጸአታቸው ነው። ከግብጽ እርነት የመውጣታቸው ጊዜ ሲቃረብ እግዚአብሔር የመከራ ጽዋቸውን በማምረር አዘጋጃቸው። ወደ እግዚአብሔርም በጮኹ ጊዜ ያወጣቸው ዘንድ ሙሴን ላከላቸው። ከግብጽ በወጡ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሕግ ተሰጠ፤ የመገናኛ ድንኳን ተሠራ፤ መሥዋዕት የሚቀርብበት የአምልኮ ሁኔታ ተመቻቸ፤ እንዲሁም «የአይሁድ ማኅበር» ተመሠረተ። ዳሩ ግን በዓመቱ መጨረሻ ላይ ወደ ቃዴስ በርኔ ሲደርሱና ጉዞአቸውን ቀጥለው

ምድሪቱን ለመውረስ እምቢ ሲሉ፥ በበረሃ ውስጥ ለ40 ዓመታት እንዲቅበዘበዙ በማስገደድ እግዚአብሔር ቀጣቸው። በበረሃውም ውስጥ በድንቅ ሁኔታ በልተው፥ ለብሰውና «በእሳትና በደመና ዓምድ» ተመርተው ተጉዘዋል።

ከ40 ዓመታት ማብቂያ ላይ በኢያሱ መሪነት የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው ወደ ተስፋዪቱ አገር በመግባት ወርሰዋታል። ከዚያም ሦስተኛው የእስራኤሎች የታሪክ ክፍል ተጀመረ። ይኸውም ለ450 ዓመታት የጊዜ ገደብ የቆየው የመሳፍንት ዘመን ነው። መንግሥቱም በመጀመሪያ በሽማግሌዎች በኋላም በመሳፍንት ይተዳደር የነበረ መለኮታዊ መንግሥት ነበር። ሕዝቡ ግን በዓይን በማይታይ ንጉሥ ለመተዳደር ፈቃደኛ አልነበሩም። በዙሪያቸው እንደሚገኙ ሌሎች ሕዝቦች ዓይነት ንጉሥ ፈለጉ። ስለዚህም ወደ ነቢዩ ሳሙኤል ዘንድ ሄደው ንጉሥ ጠየቁት። ሳሙኤል የእርሱን አስተዳደር በመቃወም እንደ ሆነ በማሰብ ቢያዝንም፥ ነገሩን ወደ እግዚአብሔር ባቀረበ ጊዜ፡-

> «እኔን እንጂ አንተን አልናቁምና በሚሉህ ነገር ሁሉ የሕዝቡን ቃል ስማ» (1ኛ ሳሙኤል 8፥7)

በማለት መለሰለት።

ከዚያም ሳሙኤል የሚመረጠው ንጉሥ ምን እንደሚያደርግባቸው በመግለጽ ሕዝቡን ቢያስጠነቅቅም፥ ማስጠንቀቂያው ዋጋ አልነበረውም፤ በመሆኑም ሳኦል ተመረጠ። ይህ የታሪካቸው አራተኛ ክፍል ጅማሬ ነበር። ሳኦል ለ40 ዓመታት ከነገሠ በኋላ እግዚአብሔር በመረጠው ሰው በዳዊት ተተካ። እርሱም ለ40 ዓመታት ከነገሠ በኋላ ለልጁ ለሰሎሞን አስረከበው። ሰሎሞንም በተራው 40 ዓመታት ገዝቷል። በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ ተመሠረተ። ዘመነ-መንግሥቱ ከሁሉም በላይ የከበረ ሲሆን፥ ደካማ ጎኑም እጅግ ብዙ ጣዖት አምላኪ ሚስቶች ማግባቱና የጣዖታትን አምልኮ ወደ ኢየሩሳሌምም እንዲያስገቡ መፍቀዱ ነበር። ይህ የአይሁድ ሕዝብ የውድቀት መጀመሪያው ነበር። ከሰሎሞን ሞት በኋላ በ975 ዓ.ዓ. መንግሥቱ ተከፋፈለ። ልጁ ሮብዓም ሁለቱን ነገዶች ይሁዳና ብንያምን፥ እንዲሁም ኢየሩሳሌምንና ቤተ መቅደሱን ይገዛ ነበር። ያለ አግባብ በሌሎቹ ነገዶች ሳይ የነገሠው



ኢዮርብዓም ሰማርያን ዋና ከተማ አደረጋት። እስራኤል በመባል የታወቀው ክፍል በፍጥነት እያሽቆለቆለ ሄዶ በ721 ዓ.ዓ. አሥሩ ነገዶች በአሦራውያን ተማርከው ተወሰዱ። ይሁዳ በመባል የተለዩት ሁለቱ ነገዶች ከዚህ በኋላ ለአንድ መቶ ዓመታት ቢቆዩም፥ በ606 ዓ.ዓ. በባቢሎናውያን ተማርከው ተወሰዱ። እንዲሁም በ587 ዓ.ዓ. ኢየሩሳሌም በናቡከደነፆር ተደመሰሰች። በዚህም በነበሩት ታላላቅ ነቢያት አገልግሎት ጎልቶ የሚታየው የነገድ ጦርነት ዘመን አበቃ።

በይሁዳ መማረክና በኢየሩሳሌም መውደም በዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ የተገለጸው ረዥሙ ክፍለ ጊዜ ተጀመረ። ይህ ወቅት ገና አልተገባደደም።

የታሪካቸው አምስተኛው ክፍል በ70 ዓመቱ የባቢሎን ምርኮ ፍጻሜ እና አይሁዶች ቤተ መቅደሳቸውን እንደገና ለመሥራት ወደ ኢየሩሳሌም በመመለሳቸው ተጀመረ። አይሁዶች ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ቢፈቀድላቸውም ቅሉ፥ የበላይነትን ለመቀዳጀት ግን እንደገና አልበቁም ነበር። ምንም እንኳ በአብዛኛው በራሳቸው ዘሮች ቢተዳደሩም፥ ለተለያዩ ድል አድራጊዎች ማጎብደዳቸው ግን አልቀረም። ይህም የሆነው «ገዢ» እስኪመጣ ድረስ በትረ መንግሥት ከይሁዳ እንደማይታጣ በተነገረው ትንቢት ፍጻሜ ምክንያት ነው (ዘፍጥረት 49፡10)።

የሚከተለው ትንቢት ይሁዳ በብሔራዊ ደረጃ በናቡከደነፆር መሪነት (በ605-538 ዓ.ዓ. አካባቢ) በባቢሎናውያን ከመማረካቸው ቀደም ብሎ በኤርምያስ የተነገረ ነው።

> «እነሆ፥ ለራስህና ለወዳጆችህ ሁሉ ፍርሃት አደርግሃለሁ፤ እነርሱም በጠላቶቻቸው ሰይፍ ይወድቃሉ ዓይኖችህም ያያሉ፤ ይሁዳንም ሁሉ በባቢሎን ንጉሥ እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ፥ እርሱም ወደ ባቢሎን ያፈልሳቸዋል በሰይፍም ይገድላቸዋል። የዚህችንም ከተማ ባለጠግነት ሁሉ ጥሪትዋንም ሁሉ ክብርዋንም ሁሉ የይሁዳንም ነገሥታት መዝገብ ሁሉ በጠላቶቻቸው እጅ አሳልፌ እሰጣለሁ፥ እነርሱም ይበዘብዙአቸዋል ይዘውም ወደ ባቢሎን ያፈልሱአቸዋል» (ኤርምያስ 20፡4-5)።

> «ይህችም ምድር ሁሉ ባድማና መደነቂያ ትሆናለች እነዚህም አሕዛብ ለባቢሎን ንጉሥ ሰባ ዓመት ይገዛሉ» (ኤርምያስ 25፡11)።

«የምድርህን ፍሬ ድካምህንም ሁሉ የማታውቀው ሕዝብ ይበላዋል፤ አንተም ሁልጊዜ የተጨነቅህ የተገፋህም ትሆናለህ። ዓይኖችህም ከሚያዩት የተነሣ ዕብድ ትሆናለህ። እግዚአብሔር ፈውስ በሌለው በክፉ ቍስል ጉልበትህንና ጭንህን ከእግርህ ጫማ እስከ አናትህ ድረስ ይመታሃል።

«እግዚአብሔርም አንተን በአንተም ላይ የምታነግሠውን ንጉሥ አንተና አባቶችህ ወዳላወቃችኋቸው ሕዝብ ይወስድሃል፤ በዚያም ሌሎችን የእንጨትና የድንጋይ አማልክት ታመልካለህ» (ዘዳግም 28፡33-36)።

በ168 ዓ.ዓ. አንቲዮከስ ኤፒፋኔስ የተባለው የሶሪያ ንጉሥ ፍልስጥኤምን ከግብጻውያን እጅ አስጥሏል። ሁለት ጊዜ ኢየሩሳሌምን በማሸነፍ ዘርፏል። ቤተ መቅደስንም አርክሶታል፤ ዘግቶታል። የአይሁድም ሕዝብ በመቃብያውያን መሪነት በዓመፅ ለመነሣት ከፍተኛ የሆነ የቁጣ ስሜት እስኪያሳዩ ድረስ ጭካኔ በተመላበት ሁኔታ አሳድዶአቸዋል። ዓመፃቸውም ከ160-40 ዓ.ዓ. ድረስ ቆይቷል።

በ63 ዓ.ዓ. ይሁዳ በሮም አገዛዝ ሥር ስትወድቅ፥ ለሚቀጥሉት 60 ዓመታት የሮም መንግሥት በቅድስት አገር ላይ አገዛዙን አጠናከረ። በዚህ ጊዜ 5 ዓ.ዓ. አካባቢ ብዙዎች የትንቢት ምሁራን «መሢሑ አለቃ» የሚመጣበት ጊዜ ሩቅ አለመሆኑን ከነብዩ ዳንኤል ተረድተው (ዳንኤል 9፡24-27) የእስራኤልን መጽናናት እየተጠባበቁ አዘውትረው በቤተ መቅደስ ውስጥ ያሳልፉ ነበር።

ኢየሱስም በቤተ ልሔም ተወለደ። በእረኞች ተጎበኘ። ከጥቂት ሳምንታት በኋላም በቤተ መቅደስ በስምዖንና በሐና እውቅና አገኘ።

ከምሥራቅ የመጡ ሰብአ ሰገል እጅ መንሻ አቀረቡለት፤ ወደ ግብጽም ከወረደ በኋላ ወደ ናዝሬት ተመልሶ የልጅነትና የወጣትነት ጊዜውን በዚያ አሳልፏል። ዕድሜው 30 ዓመት ሲሞላ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ወርዶ በመጥምቁ ዮሐንስ በመጠመቅ ሕዝባዊ አገልግሎቱን ጀመረ። ይሁንና መሢሕ ነኝ ማለቱ ለአይሁዶች አልተዋጠላቸውም። ይሰቀል ዘንድ፡

«ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን»



በማለት እየጮኹ ለአሕዛብ አሳልፈው ሰጡት። ይህ እንዴት ቃል በቃል እንደ ተፈጸመ ከታሪክ መጻሕፍት ውስጥ እናነባለን። በ70 ዓ.ም. የሮማ ወታደሮች በመምጣታቸው ኢየሩሳሌምና መቅደሱ በቲቶ ተደምስሰው፥ አይሁዶችም በምድር ሕዝቦች መካከል ተበተኑ። ይህም በዳንኤል መጽሐፍ በዘጠነኛው ምዕራፍ ውስጥ እንደ ተተነበየው ነው።

መሢሑን ባለመቀበላቸውና በመግደላቸው የአይሁድ ዘር ትካዜ ተጀመረ።

በ50 ዓ.ም. በኢየሩሳሌም ከተማ ከሮማውያን ጋር በተደረገው ብጥብጥ 30000 ሰዎች ተገድለዋል። ይሁንና ከሁሉ የከፋው ሥቃያቸው የተጀመረው በ66 ዓ.ም. በይሁዳ የሮም ባለሥልጣን በሆነው በጌስዩስ ፍሎረስ ነው። የእርሱም ጭቆና ወደ ተስፋፋ ዓመፅ መራቸው። በዚህም ጊዜ ንጉሠ ነገሥት ኔሮ ቬስፔስያንንና ልጁ ቲቶን ከ60000 ወታደሮች ጋር ላከ። እርሱም ዝነኛ የአስሞኒያን ዘር ጄኔራልና የታወቀ የታሪክ ጸሐፊ ከሆነው ከጆሲፈስ ጋር በላይኛው ገሊላ ተገናኘ። ጆሲፈስ በጆታፓታ ራሱን አጠናክሮ ሲዋጋ፥ ከ47 ቀናት ከበባ በኋላ ከ40000 ወታደሮች በላይ ሲሞቱበት በመጨረሻው ሊሸነፍ በቅቷል። ከዚያም የገሊላ ድል መመታት ተከተለ። በዚያ ጦርነት ውስጥ ብዙ ሺህ ወታደሮች አለቁ። ቬስፔስያን በኔሮ ሞት ምክንያት ወደ ሮም ስለ ተጠራ፥ ይሁዳና ኢየሩሳሌም ተረፉ። ቬስፔስያን ንጉሠ ነገሥት ከሆነ በኋላ የቅድስቲቱን አገር እንዲያስገብርና ኢየሩሳሌምን እንዲይዛት ልጁ ቲቶን ላከ።

በ70 ዓ.ም. በሚያዝያ ወር 100000 የሮማ ወታደሮች በኢየሩሳሌም ዙሪያ ተሰለፉ። ትልቅ ከተማ ብትሆንም ከበባውን ለመከላከል ግን በደንብ አልተዘጋጀችም ነበር። ተቀናቃኝ ቡድኖች ለሥልጣን ሲሉ እርስ በርሳቸው በመናቆር ላይ ነበሩ። ከተማዪቱ 90 የመከላከያ ማማዎች የነበሯትና በሦስት ተደራራቢ ቅጥሮች የታጠረች ነበረች። ከበባውም ለአራት ወራት ቀጠለ። በትላልቅ ካቦዎች በመታገዝ ትላልቅ ሞተሮች በግድግዳዎቹ ላይ ድንጋዮችን ማዝነብ ያዙ። በከተማዪቱ ውስጥ ረሀብ ነገሠ። ሚስቶች ከባሎች፥ ልጆች ከወላጆቻቸው፥ እናቶች ከሕፃናት ልጆቻቸው ምግብን ቀምተዋል። እንዲሁም አንዳንድ እናቶች ከእናትነት ባሕርይ ወጥተው ልጆቻቸውን ቀቅለው በልተዋል። ብዙዎቹ ከከተማይቱ ቢሸሹም የባሰ ነገር ደርሶባቸዋል። በቲቶ ተይዘው ለመቀጣጫ ከከተማዪቱ ግንብ ውጭ ይሰቀሉ ነበር። የተከበቡት ሰዎች ሁኔታ እጅግ አስቃቂ

ከመሆኑ የተነሣ፥ ቲቶ እርሱ ኃላፊነት እንደሌለበት እንዲመሰክርለት ወደ እግዚአብሔር ተማርቷል።

በመጨረሻም በሐምሌ 29ቀን 70 ዓ.ም. አቶኒያ የተባለው ማማ ተያዘ። ሮማውያን ቤተ መቅደሱን ወረሩት፤ ምንም እንኳ በሮማውያን ከዓለም አስደናቂ ነገሮች እንደ አንዱ የሚታየውን ውቡን ቤተ መቅደስ እንዳያተርፉት ቢያዛቸውም፥ ከወታደሮቹ አንዱ በበሩ በኩል የተቀጣጠለ ችቦ ወደ ውስጥ በመወርወሩ፥ ሄሮድስ ያሠራው ቤተ መቅደስ በእሳት ወደመ። ቤተ መቅደሱ ከተመሠረተበት ድንጋይ በስተቀር የተረፈ ነገር አልነበረም።

በጥቃቱ ከ1000000 በላይ ሰዎች እንደ ረገፉና 97000 የሚሆኑ ሰዎች በምርኮኛነት እንደ ተወሰዱ፥ ከእነርሱም ውስጥ መልክ ቀና የሆኑ ወጣት ወንዶች እንደ አሸናፊው ግዳይ ሆነው ወደ ሮም እንደ ተላኩ ጆሲፈስ ይናገራል። በዚህም፡-

> «የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፋሉ» (ዳንኤል 9፡26)

የሚለው የዳንኤል ትንቢት ተፈጸመ።

በቲቶ የተፈጸመው የኢየሩሳሌም ውድመት አይሁዶችን በሰፋትና በርቀት ቢበትናቸውም፥ ይህ የጥፋቱ ፍጻሜ አልነበረም። ከ65 ዓመታት በኋላ፥ በ136 ዓ.ም. ከዚያ የጥፋት ማዕበል በበቂ ሁኔታ አገግመው በሮማ አገዛዝ ላይ ዓመፅ ለማነሣሣት ችለዋል። አሁንም እነርሱን የመበተኑን ሥራ ሃድሪያን አከናወነው። ለሦስት ዓመታት ተከታትሎ በቆየው በዚህ ጦርነት፥ ፍልስጥኤምን አወደመ፤ 580000 ሰዎችን አጠፋ፤ ጽዮንንም አረሳት (በዚህም ከ885 ዓመታት በፊት የተነገረው የሚክያስ 3፡12 ትንቢት ተፈጸመ)። እንዲሁም በኢየሩሳሌም ይዞታ ወደሠራት ወደ አዲስቱ የሮማ ከተማ ኤሊያ ካፒቶሊና ቢደርሱ እንደሚገድላቸው በማስጠንቀቅ ከልክሎአቸዋል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በፍልስጥኤም ምንም ያክል አይሁዶች አልቀሩም።

በ362 ዓ.ም. ንጉሡ ጁልያን የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች ለመጠገን ጀመረ። ይህ ጌታ በትንቢት ከተናገረው የሚቃረን ሲሆን፥ ከፍርስራሹ የተነሣው እሳት ሠራተኞቹን አባርሯቸዋል።



ከሃድሪያን 140 ዓ.ም. እስከ ቆንስጣንጢኖስ ባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ በተሰደዱበት በሮም ግዛት ሁሉ አይሁዶች በመጠኑ ይበለጽጉና ይስፋፉ ጀመር። እንዲያውም የባዕድ አምላኪዎች በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ላይ ባስነሡት ስደት ላይ ተሳትፈዋል። ዳሩ ግን በ312 የቆንስጣንጢኖስ ወደ ክርስትና እምነት መግባት ይህን ሁሉ ለወጠው። ከዚያም አይሁዶች የተኮነኑና የተሰደዱ ክፍሎች ሆኑ። ይህም የሮማ ቤተ ክርስቲያን የፖለቲካ ሥልጣንንና የአባሎችዋን መሃይምነት በመጠቀም፥ የአይሁድን ሕዝብ በእግዚአብሔር ስም ያሳደደችበትን አሳዛኝ ወቅት አስከትሏል።

ጭጋጉ እየጠቆረ ሄዶ በታሪክ ውስጥ የውድቀት ጽልመት የጣለባቸውን «ቅዱስ ጦርነት» ተብሎ የሚታወቀውን የመጀመሪያውን «የመስቀል ዘመቻ» በ1096 ዓ.ም. አስከትሏል። ከተሃድሶ ዘመን በኋላ ብዙ እስከሚቆይም ጨለማው ከላያቸው አልተገፈፈም ነበር።

በ1020 ዓ.ም. ካኑት አይሁዶችን ሁሉ ከእንግሊዝ አገር አባረረ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ለአይሁዶች የተፈቀደው ብቸኛው የቀብር ስፍራ በሎንደን የሚገኘው ክሪክልጌት ነበር። ከዚያም በአውሮፓ ለመጠመቅ የማይፈቅዱትን አይሁዶች ሁሉ ለመጨፍጨፍ ሲባል ቅዱስ ጦርነት ተቀስቅሷል። ሔንሪ ዳግማዊ ከመስቀል ዘመቻዎቹ ለአንደኛው ወጪውን ለመሸፈን አይሁዶች 60000 ፓውንድ እንዲከፍሉ አዟል። በ1189 ዓ.ም. ሪቻርድ ቀዳማዊ ወደ ዙፋን በመጣ ጊዜ በአይሁዶች ላይ የግድያ ጥቃት ያስከተለ ብጥብጥ በመቀስቀሱ ከሞትና ከዘረፋ ያመለጠ የአይሁድ ቤተሰብ አልነበረም።

ቀጣዩ ዓመት ዋናው የዮርክ የአይሁድ መምህርና 500 ተከታዮቹ በዮርክ የግንብ ሕንፃ ውስጥ ተከብበው ማምለጡ የማይሞከር ሲሆንባቸው እርስ በርሳቸው የተራረዱበትን አሳዛኝ ሁኔታ አሳይቷል። በመጨረሻ ላይ የሞተው ዋናው የአይሁድ መምህር የእልቂቱን እሳት አስቀድሞ ከለኰሰ በኋላ የራሱን ሕይወት አጥፍቷል። ከባቢያዎቹም ወደ ውስጥ ሰብረው በገቡ ጊዜ፥ የተከበቡትን ሰዎች በመሠውያ ላይ እንደ ቀረበ መሥዋዕት አንድ ትልቅ ከምር ሆነው አገኙአቸው።

እስከ ኤድዋርድ ቀዳማዊ ዘመን እስከ 1272 ዓ.ም. ድረስ ዘውዱ የአይሁዳዊውና የእርሱ የሆነ ነገር ሁሉ ባለንብረት ከእስፖንጅ ውኃ

ተጨምቆ እንደሚወጣ ሁሉ ከአይሁዳዊውም ሀብት ተጨምቆ ይወጣ ዘንድ በየወቅቱ ሀብትን ማካበት የሚፈቀድለት እንደ ሆነ ይናገራል። ኤድዋርድ ቀዳማዊ በቁጥር 16500 የሚሆኑ አይሁዶችን ከእንግሊዝ አገር በማባረሩ፥ ለአራት መቶ ዓመታት ያህል የብረታንያ ትቢያ በአይሁድ መረገጡን የሚያሳይ መረጃ የለም።

በ1306 ዓ.ም. የኢየሩሳሌምን ጥፋት በማስታወስ በተጾመበት ቀን ጠዋት በፈረንሳይ የሚገኙ አይሁዶች በሙሉ፥ ወንዶች፥ ሴቶችና ሕፃናት ባጠቃላይም 100000 ሰዎች ንብረታቸውን ለመንግሥት ግምጃ ቤት አስረክበው ከአገር ተባርረዋል። ከአሥር ዓመታት በኋላ እንዲመለሱ ቢፈቀድላቸውም፥ ወዲያው «ፓስቱረው» የተባለ የእረኞችና የወንጀለኞች ቡድን በሺሆቹ ጠራርገው አስወጥተዋቸዋል። በ1683 ዓ.ም. አይሁዶች የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት የሆኑ አገሮችን ሁሉ እንዲለቁ ሲታዘዙ፥ ሉዊ 15ኛ በፈረንሳይ ውስጥ ትክክለኛ ርስት እንዲኖራቸው እስከ ፈቀደበት እስከ 1723 ድረስ፥ ሁኔታው አልተቀየረም ነበር።

አውሮፓን ያካለለው (1348-50) «ጥቁር ሞት» ከሕዝቡ አንድ አራተኛውን ሲፈጅ በቀላል አኗኗራቸውና የሌዋውያኑ ሕግ ከሚያዝዘው የንጽሕና አጠባበቅ የተነሣ አይሁዳውያንን አልጎዳቸውም ነበር። ይህ አንጻራዊ የሆነው ከመቅሠፍት የመዳናቸው ጉዳይ፥ የመቅሠፍቱ ምንጮች እነርሱ ራሳቸው እንደ ሆኑ እንዲጠረጠሩና የውኃ ጉድጓዶቹንና ምንጮቹን እንደ መረዙ ሆኖ እንዲከሰሱ ምክንያት ሆኖባቸዋል። በጀርመን አገር፥ የተባለው መርዝ የተቀመመበት ነገር፥ የተጓጓዘበት የመያዣው ቀለምና መርዙን የጨመሩት ሰዎች ሁሉ እንደ ታወቁ ተነግሯል። ውጤቱም በጀርመን እየተዘዋወሩ የማያምኑትን ሰዎች መፍጀትን በሚሰብኩት ጨካኝ ገራፊዎች እጅ መሰቃየታቸው፥ በበርሚል ውስጥ መቀቀላቸውና በእሳት መቃጠላቸው ነበር። በእስትራስበርግ 2000 ነፍሳት የሚሆኑ ሁሉም የማኅበረሰቡ አባላት በእሳት ወደ ግዙፍ ርብራብ ተጎትተው ተቃጥለዋል።

እንዲሁም የክርስቲያኖችን ልጆች ሰርቀው ለፋሲካ መሥዋዕት እንደሚያቀርቡም ተከሰዋል። ደግሞም የተቀደሰውን «ኅብስት» በመስረቅ በቢላዋ እንደሚወጉት ተወንጅለዋል። በ1560 ከፕራግ ከተማ ተባርረዋል፤ በመቀጠልም በኮንስታንቲኖፕል ከአይሁዶች ሰፈር 3000



ቤቶች ተቃጥለው፥ ወደ 50 000 000 ክራውን (በቀድሞ የእንግሊዝ ሳንቲም፥ አንድ ክራውን = 5 ሽልንግ) የሚገመት ንብረት ተዘርፏል።

በእስፔይን አደገኛ የቃለ መጠይቅ ስልት ተቀይሶ ነበር። ይህም የተደረገው ከእምነታቸው ያፈነገጡትን አይሁዶች ለማስፈራራት ነበር። መሬት ተከፍታ እንደ ዋጠቻቸው ሁሉ፥ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሴቶችና ወንዶች እንዲሁ ጠፉ። ከእነርሱም አንዳንዶቹ በጭራሽ ያልተመለሱ ሲሆን፥ ሌሎች ለረዥም ጊዜ በጨለማ ጎሬዎች ውስጥ ታስረው ከመቆየታቸው የተነሣ፥ ገርጥተው፥ ከስተውና ወፈፌ ሆነው ከዓመታት በኋላ ተመልሰዋል። አሁንም አሁንም በርካታ ሕዝብ በየመንገዱ ወደ መቃጠያው ስፍራ ይጎርፋል፤ ወደ እሳቱ ወላፈን ከመጣላቸው በፊት እምነታቸውን እንደ ተዉ በይፋ ይናገራሉ በሚል ቀቢጸ-ተስፋ ሥቃይ ይደርስባቸዋል።

ብዙዎቹ ከፍርድ ቤቱ አዳራሽ ሲወጡ፥ በመሬት ውስጥ ለውስጥ በተሠራ መተላለፊያ በኩል «ከብረቷ ወይዘሪት» ክፍል ራሳቸውን ያገኙታል። በዚህም ክፍል ውስጥ የሚገኘው ከብረት የተሠራ እስቀያሚና ውስጡ ክፍት የሆነ የሴት ምስል ሲሆን፥ ሞላው ሲነካ ወለል ብሎ በመከፈት በበርካታ ተጎጂዎቹ የሻገቱ አያሌ የብረት ምስማሮች የተሰገሰጉበትን ትንሽ ክፍል ያሳያል። አበሰኛው ሰው በሚገባበት ጊዜ ምስሉ መዘጋት ይጀምራል። ምስማሮቹም በሳስተውት እስኪገቡ በብረት እቅፉ ያጣብቀዋል። ዋና ዋና ብልቶቹ ሲበሳሱም ሰውየው እሪታውን ይለቀዋል። እንዳከተመለት በድኑ ከሥር እያዛጋ ወደሚጠብቀው አዘቅት እንዲገባ በድጋሚ ይከፈታል። ይህ ብቻ አልነበረም። በ1492 ዓ.ም. ፈርዲናንድ እና ኢሳቤላ አይሁዶች ሁሉ ከእስፔይን እንዲወጡ የሚያዝ ሕግ ደንግገዋል። ማዘዣውንም ለማሠረዝ አንድ አይሁዳዊ 600,000 ክራውኖች አቀረበ። ንጉሡና ንግሥቲቱ ለመቀበል ሲያመነቱ እስፓንያዊው ኃይለኛው መርማሪ ቶርኪመዳ ወደ ተሸማቀቁት ገዢዎች ዘንድ እየተቆነነ ቀርቦ የተሰቀለው ክርስቶስ የተቀረጸበትን መስቀል ሽቅብ በማንሣት፡-

> «ይሁዳ በሠላሳ ብር የሸጠውን እርሱን ተመልከቱ፤ እናንተም አሁን ከዚያ በበለጠ ዋጋ ሸጡትና የስምምነታችሁን መዝገብ በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡ» ብሎ ጮኸ።

ገዚዎቹ በአጥባቂ ዶሚንካን ፊት ተንቀጠቀጡ፤ አይሁዶች ከአገሩ መውጣት ነበረባቸው። ለዝግጅት ይሆናቸውም ዘንድ አራት ወራት ተሰጣቸው። ሊቀበላቸው የሚወድ አንድም ወደብ ስላልነበረ፥ ወዴት እንደሚሄዱ የሚያውቁት ነገር የለም። አንዳንዶች ወደ አፍሪካ በመዝለቅ በዚያ በባርነት ተሸጡ። አንዳንዶቹ ወደ ጣሊያን ደረሱ። በአጠቃላይ ሥቃያቸው የማይነገር ነበር። ከ200 ዓመታት በኋላ በ1680 ዓ.ም. በአይሁዶች ላይ የነበረው የኢስፔይን መንፈስ አልተለወጠም ነበር።

ስለ ሆነም እጅግ እንደሚያስፈራ ቅዠት ለብዙ ዘመናት በአብርሃም ዘር ላይ የወደቁትን አሰጨናቂ ቅጣቶችና ስደቶች ታሪክ ይዘግባል። ስብአዊነትና ሥልጣኔ በነገሠበት በዛሬው ዘመን እንኳ ሂትለርና አእምሮአቸው የተነካባቸው አክራሪ ግብረ-አበሮቹ በካምፖችና በመርዘኛ ክፍሎች እንዴት 6,000,000 አይሁዶችን በዘዴ እንደ ፈጁአቸው በአእምሮአችን ገና ያልተረሳ ትኩስ ትውስታ ነው። በዚያ ሁሉ ረዥም የጨለማ ዘመን ስደታቸው አይሁዶች ከምድር ገጽ ያለመጥፋታቸው ተአምር፥ ለተወሰነ ዓላማ ተጠብቀው ቆይተዋል ከማለት በስተቀር ምክንያት የሚሰጥበት አይሆንም። (ይህ ታሪካዊ ዘገባ ለሙንና ደራሲውን አሁን ከማላስታውሰው ጥራዝ ከ20 ዓመታት በፊት የገለበጥሁት ነው።)

በስደት ውስጥ ያለፈ ሕዝብ በምንም ዓይነት አይሁዶች ብቻ አልነበሩም፤ ዳሩ ግን እንደ እነርሱ አብዝቶ የተሰደደ ሕዝብ የለም። ለ2,000 ዓመታት ያህል በስደት መከራ ውስጥ በማለፍና በዓለም ሁሉ መበተንን እንደ እነርሱ የተቋቋመ ሕዝብ የለም። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን እንደሚከተለው ተንብዮአል፡-

> «እግዚአብሔርም ከምድር ዳር እስከ ዳርቻዋ ድረስ ወዳሉ አሕዛብ ሁሉ ይበትንሃል፤ በዚያም አንተና አባቶችህ ያላወቃችኋቸውን ሌሎችን አማልክት፥ እንጨትንና ድንጋይን፥ ታመልካለህ። በእነዚያም አሕዛብ መካከል ዕረፍት አታገኝም፥ ለእግርህም ጫማ ማረፊያ አይሆንም፤ በዚያም እግዚአብሔር ተንቀጥቃጭ ልብ፥ ፈዛዛ ዓይን፥ ደካማም ነፍስ ያመጣብሃል። ነፍስህም ታመነታለች፤ ሌሊትና ቀንም ትፈራለህ፥ በሕይወትህም አትታመንም» (ዘዳግም 28፡64-66)።



> «እነሆ፥ የሕዝቤን የእስራኤልንና የይሁዳን ምርኮ የምመልስበት ዘመን ይመጣልና፥ ይላል እግዚአብሔር ለአባቶቻቸውም ወደ ሰጠኋት ምድር እመልሳቸዋለሁ፥ እነርሱም ይገዙአታል» (ኤርምያስ 30፡3)።

> «አሕዛብ ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፥ በሩቅም ላሉ ደሴቶች አውሩና፡- እስራኤልን የበተነ እርሱ ይሰበስበዋል፥ እረኛም መንጋውን እንደሚጠብቅ ይጠብቀዋል በሉ። እግዚአብሔር ያዕቆብን ተቤዥቶታል፥ ከበረቱበትም እጅ አድኖታል» (ኤርምያስ 31፡10-11)።

> «እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤ ዘርህንም ከምሥራቅ አመጣዋለሁ፥ ከምዕራብም እሰበስብሃለሁ። ሰሜንን፡- መልሰህ አምጣ፥ ደቡብንም፡- አትከልክል፤ ወንዶች ልጆቼን ከሩቅ ሴቶች ልጆቼንም ከምድር ዳርቻ፥ በስሜ የተጠራውን ለክብሬም የፈጠርሁትን፥ የሠራሁትንና ያደረግሁትን ሁሉ አምጣ እለዋለሁ።
>
> «ዓይኖች ያሉአቸውን ዕውሮችን ሕዝብ፥ ጆሮችም ያሉአቸውን ደንቆሮቹን አውጣ» (ኢሳይያስ 43፡5-8)።

ለእኔ ከሁሉም በላይ የሚያስደንቀኝ የአይሁዶች ወደ እስራኤል ምድር መመለስ ነው። ይህም ባለፈው ክፍለ ዘመን ፍጻሜ ላይ ተጀምሮ፥ ከመጨረሻው የዓለም ጦርነት በኋላ ታላቅ እንቅስቃሴ በማድረግ፥ በ1948 ዓ.ም. የእስራኤልን መንግሥት ለመመሥረት በቅቷል። ይህ የማይገመት ቢመስልም እንኳ፥ ተተንብዮ ነበር፤ ትንቢቱም ከዳር ደርሷል፤ እየደረሰም ነው።

## አሁን በመፈጸም ላይ ያሉ ትንቢቶች

የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮት መቋጫው በኢየሱስ መመለስ ነው።

ምንም እንኳ አሁን አብዛኞዎቹ አይሁዶች የኢየሱስን መሢሕነት ቢክዱም፥ መሢሕ እንደሚመጣ ይጠባበቃሉ። መሢሑም ድል አድራጊ፥ ነፃ አውጪ፥ ታላቅ ጀግና እንደሚሆን ያስባሉ። እንዲሁም ለሁለተኛ ጊዜ የሚመጣው በዚህ አኳኋን ነው።

«በዳዊትም ቤት ላይ፥ በኢየሩሳሌምም በሚኖሩት ላይ፥ የሞገስንና የልመናን መንፈስ አፈስሳለሁ ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ ሰውም ለአንድያ ልጁ እንደሚያለቅስ ያለቅሱለታል፥ ሰውም ለበኵር ልጁ እንደሚያዝን በመራራ ኅዘን ያዝኑለታል» (ዘካርያስ 12፡10)።

ይህ የሚሆነው በ«ታላቁ መከራ» ጊዜ ነው። ክርስቶስና ነቢያት ይህንን ተንብየዋል፡-

«የእግዚአብሔር ቀን መጥቶአልና፥ እርሱም ቀርቦአልና በጽዮን መለከትን ንፉ፥ በቅዱሱም ተራራዬ እሪ በሉ፤ በምድርም የሚኖሩ ሁሉ ይንቀጥቀጡ የእግዚአብሔር ቀን መጥቶአልና፤ የጨለማና የጭጋግ ቀን፥ የደመናና የድቅድቅ ጨለማ ቀን ነው፤ ታላቅና ብርቱ ሕዝብ በተራሮች ላይ እንደ ወገግታ ተዘርግቶአል፤ ከዘላለምም ጀምሮ እንደ እነርሱ ያለ አልነበረም፥ ከእነርሱም በኋላ እስከ ብዙ ትውልድ ድረስ እንደ እነርሱ ያለ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም። እሳት በፊታቸው ትባላለች፥ በኋላቸውም ነበልባል ታቃጥላለች፤ ምድሪቱ በፊታቸው እንደ ዔድን ገነት፥ በኋላቸውም የምድረ በዳ በረሃ ናት፤ ከእነርሱም የሚያመልጥ የለም።

«መልካቸው እንደ ፈረስ መልክ ነው፥ እንደ ፈረሶችም ይሮጣሉ። በተራራ ላይ እንዳሉ ሰረገሎች ድምፅ፥ ገለባውንም እንደሚበላ እንደ እሳት ነበልባል ድምፅ፥ ለሰልፍም እንደ ተዘጋጀ እንደ ብርቱ ሕዝብ ያኰበኵባሉ። ከፊታቸው አሕዛብ ይንቀጠቀጣሉ፤ የሰውም ፊት ሁሉ ይጠቍራል። እንደ ኃያላን ይሮጣሉ፥ እንደ ሰልፈኞችም በቅጥሩ ላይ ይወጣሉ፤ እያንዳንዱም በመንገዱ ላይ ይራመዳል፥ ከእርምጃቸውም አያፈገፍጉም። አንዱ ካንዱ ጋር አይጋፉም፥ እያንዳንዱም መንገዱን ይጠብቃል፤ በሰልፉ መካከል ያልፋሉ። እነርሱም አይቈስሉም። በከተማም ያኰበኵባሉ፥ በቅጥሩም ላይ ይሮጣሉ፤ ወደ ቤቶችም ይወጣሉ፥ እንደ ሌባም በመስኮቶች ይገባሉ። ምድሪቱም ከፊታቸው ትናወጣለች፥ ሰማያትም ይንቀጠቀጣሉ፤ ፀሐይና ጨረቃም ይጨልማሉ፥ ከዋክብትም ብርሃናቸውን ይሰውራሉ። እግዚአብሔርም በሠራዊቱ ፊት ድምፁን ይሰጣል፤ ሰፈሩ እጅግ ብዙ ነውና፥ ቃሉንም የሚያደርግ እርሱ



ኃያል ነውና የእግዚአብሔር ቀን ታላቅና እጅግ የሚያስፈራ ነውና ማንስ ይችለዋል?» (ኢዩኤል 2፡1-11)።

ይህን ዘመናዊ የጦር ጓዝ የሚታይበትን ሁኔታ ለመግለጽ ቃላት ከማጣቱ በቀር፥ ኢዩኤል በራእዩ ምን እንደ ተመለከተ ለማስተዋል ብዙም የሚያስቸግር አይደለም። ከሚናገራቸው ነገሮች ውስጥ የጦር ታንኮችን፥ ከፍተኛ የውጊያ መሣሪያዎችንና ጭካኔ የተሞላባቸውን ፍልሚያዎች በአእምሮ ውስጥ መቅረጽ ይቻላል፤ ዳሩ እንዴት አወቃቸው?

ነቢዩ ሕዝቅኤል ስለ መጨረሻው ዘመን ብዙ ዝርዝር ጉዳዮችን ያቀርባል። በእስራኤል መመለስና አሁንም ሲመጣ ባለው መንፈሳዊ መነቃቃት ላይ ይዘግባል። ደግሞም በጎግ ሥር (በማጎግ የሮሽ፥ የሞሳሕና የቶቤል ዋና መስፍን) ቃል በተጋቡ በአካባቢው ሕዝቦች ስለ ተነሣው ጦርነት፥ ፍርሃትና ሞትም ይዘግባል። የዕብራይስጥና የግሪክ ባህሎች እነዚህ እስኪቴስ እንደ ሆኑ ይጠቅሳሉ። ይህ ባልተወሰነ ክልል በካውካሰስ ተራሮች እና በዶን ወንዝ መካከል በሩሲያ ሜዳማ አካባቢዎች የሚኖር ሕዝብ ነው። ጎመር በመጀመሪያ በሰሜን ምዕራብ እስያ ቀጥሎም የአውሮፓዋ ሩሲያ እምብርት በሆነችው በኡክሬይን የምትገኝ መስላቸው፤ የኬልቲክ ሕዝቦች (ዌልሽ) ከዚያ ያቆጠቆጡ ይመስላሉ። ቶጋርማ [ቶካ = ነገድ (ሳንስክሪት) አርማ=አርሚኒያ] ከደቡብ ሩሲያ ሊፈለግ ይገባል። ፋርስ (ፐርሺያ)፥ ኩሽ (ኢትዮጵያ) እና ፉጥ (ሊብያ) ደግሞ የተመሠረተችውን እስራኤልን ለመክበብና ለማጥፋት ከሚፈልገው ቡድን ጋር ይሰለፋሉ።

«የሰው ልጅ ሆይ፥ የእስራኤል ቤት በምድራቸው በተቀመጡ ጊዜ በመንገዳቸውና በሥራቸው አረከሱአት፥ መንገዳቸውም በፊቴ እንደ መርገም አደፍ ነበረ። በምድር ላይ ስላፈሰሱት ደም በጣዖቶቻቸውም ስላረከሱአት መዓቴን አፈሰስሁባቸው ወደ አሕዛብም በተንኋቸው ወደ አገሮችም ተዘሩ እንደ መንገዳቸውና እንደ ሥራቸው መጠን ፈረድሁባቸው። ወደ መጡባቸውም ወደ አሕዛብ በመጡ ጊዜ፥ ሰዎች እነርሱን፡- ከምድሩ የወጡ የእግዚአብሔር ሕዝብ እነዚህ ናቸው ሲሉአቸው ቅዱስ ስሜን አረከሱ። እኔ ግን የእስራኤል ቤት በመጡባቸው በአሕዛብ መካከል ስላረከሱት ስለ ቅዱስ ስሜ ሰል ራራሁላቸው።

«ስለዚህ ለእስራኤል ቤት እንዲህ በል፡- ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- የእስራኤል ቤት ሆይ፥ በመጣችሁባቸው በአሕዛብ መካከል ስላረከሳችሁት ስለ ቅዱስ ስሜ ነው እንጂ ስለ እናንተ የምሠራ አይደለሁም። በአሕዛብም ዘንድ የረከሰውን፥ በመካከላቸው ያረከሳችሁትን ስሜን እቀድሰዋለሁ በዓይናቸውም ዘንድ በተቀደስሁባችሁ ጊዜ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ አሕዛብ ያውቃሉ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። ከአሕዛብም መካከል እወጣችኋለሁ ከየአገሩም ሁሉ እሰበስባችኋለሁ ወደ ገዛ ምድራችሁም አመጣችኋለሁ ...»

«ባድማ የነበረች፥ በመንገደኛም ሁሉ ዓይን ዘንድ ባድማ የነበረች ምድር ትታረሳለች። ሰዎችም፡- ባድማ የነበረች ይህች ምድር እንደ ዔድን ገነት ሆናለች፤ የፈረሱት ባድማ የሆኑት የጠፉትም ከተሞች ተመሽገዋል ሰውም የሚኖርባቸው ሆነዋል ይላሉ። በዙሪያችሁም የቀሩት አሕዛብ እኔ እግዚአብሔር የፈረሱትን ስፍራዎች እንደ ሠራሁ ውድማ የሆነውንም እንደ ተከልሁ ያውቃሉ እኔ እግዚአብሔር ተናግሬአለሁ፥ እኔም አደርገዋለሁ።

«የሰው ልጅ ሆይ፥ ፊትህን በጎግ ላይና በማጎግ ምድር ላይ፥ በሞሳሕና በቶቤል ዋነኛ አለቃ ላይ አቅናበት፥ ትንቢትም ተናገርበት፥ እንዲህም በል፡- ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- የሞሳሕና የቶቤል ዋነኛ አለቃ ጎግ ሆይ፥ እነሆ፥ እኔ በአንተ ላይ ነኝ። እመልስህማለሁ በመንጋጋህም ልጓም አገባብሃለሁ፥ አንተንና ሠራዊትህንም ሁሉ፥ ፈረሶችንና ፈረሰኞችን የጦር ልብስ የለበሱትን ሁሉ፥ ጋሻና ራስ ቍርን ሰይፍንም የያዙትን ሁሉ፥ ታላቁን ወገን አወጣለሁ፥ ፋርስንና ኢትዮጵያን ፉጥንም ከእነርሱ ጋር ጋሻና የራስ ቍርን የለበሱትን ሁሉ፥ ጋሜርንና ጭፍሮቹን ሁሉ፥ በሰሜን ዳርቻም ያለውን የቴርጋማን ቤትና ጭፍሮቹን ሁሉ፥ ብዙዎችንም ሕዝቦች ከአንተ ጋር አወጣለሁ።

«አንተና ወደ አንተ የተሰበሰቡ ወገኖችህ ሁሉ ተዘጋጁ፥ አንተም ራስህን አዘጋጅተህ አለቃ ሁናቸው። ከብዙ ዘመንም በኋላ ትፈለጋለህ በኋለኛውም ዘመን፥ የዘላለም ባድማ በነበሩ በእስራኤል ተራሮች ላይ ከብዙ ሕዝብ ውስጥ ወደ ተሰበሰበች፥ ከሰይፍ ወደ ተመለሰች ምድር



ትገባለህ እርስዋም ከሕዝብ ውስጥ ወጥታለች ሁሉም ሳይፈሩ ይቀመጡባታል። አንተም ትወጣለህ፥ እንደ ዐውሎ ነፋስም ትመጣለህ አንተና ጭፍሮችህ ሁሉ ከአንተም ጋር ብዙ ሕዝብ ምድርን እንደ ደመና ትሸፍናላችሁ።

«በዚያ ቀን ነገር ወደ ልብህ ይገባል፥ ክፉ አሳብንም ታስባለህ፥ እንዲህም ትላለህ፡- ቅጥር ወደሌላቸው መንደሮች እወጣለሁ፤ ተዘልለው ወደሚኖሩ፥ ሁላቸው ሳይፈሩ ያለ ቅጥርና ያለ መወርወሪያ ያለ መዝጊያም ወደሚቀመጡ እገባለሁ ምርኮን ትማርክ ዘንድ ብዝበዛንም ትበዘብዝ ዘንድ፥ ባድማም በነበሩ አሁንም ሰዎች በሚኖሩባቸው ስፍራዎች ላይ፥ ከአሕዛብም በተሰበሰበ፥ ከብትና ዕቃንም ባገኘ፥ በምድርም መካከል በተቀመጠ ሕዝብ ላይ እጅህን ትዘረጋ ዘንድ።

«አንተም፥ ከአንተም ጋር ብዙ ሕዝብ ሁላቸው በፈረሶች ላይ የተቀመጡ፥ ታላቅ ወገንና ብርቱ ሠራዊት፥ ከሰሜን ዳርቻ ከስፍራችሁ ትመጣላችሁ። ምድርንም ትሸፍን ዘንድ እንደ ደመና በሕዝቤ በእስራኤል ላይ ትወጣለህ። በኋለኛው ዘመን ይሆናል፥ ጎግ ሆይ፥ በዓይናቸው ፊት በተቀደስሁብህ ጊዜ አሕዛብ ያውቁኝ ዘንድ በምድሬ ላይ አመጣሃለሁ።

«በዚያም ቀን ጎግ በእስራኤል ምድር ላይ በመጣ ጊዜ መቅሠፍቴ በመዓቴ ይመጣል ...»

«አንተ በምድር ፊት ላይ ትወድቃለህ» (ሕዝቅኤል 36፡17-24፤ 34-36፤ 38፡2-12፤ 15-23፥ 18፤ 39፡5)።

ከዚህ ውስጥ ግማሽ ያህሉ በፊታችን እየተፈጸመ እንዳለ እንመለከታለን። የሶቭየት ኅብረት ኃያል መሆን የርዕዮተ-ዓለሟ ወደ እስያና አፍሪካ አገሮች መዝለቅ፥ የእስራኤል መንግሥት በሉዓላዊነት መመሥረትና በመንግሥታቱ ማኀበር ተቀባይነት ማጣት ያን ከሚያህል ረዥም ጊዜ (600-500 ዓ.ዓ.) በፊት ሊነገሩ የማይችሉ ገሃድ የሆኑ ክስተቶች ናቸው። በሕዝቅኤል 36፡25-31፤ 37፡1-14፤ ሮሜ 11፡25-26 የተተነበየው የሕዝቦች መነቃቃትም ሆነ፥ የመጨረሻው ግጭት ገና የሚመጡ ናቸው።

እዲስ ኪዳንም ደግሞ በዚህ ርዕስ - ነገር ላይ አክሏል። ክርስቶስ ከመሞቱ ትንሽ ቀደም ብሎ በአትኩሮት ባቀረበው ትምህርቱ (በማቴዎስ 24፥ ማርቆስ 13 እና ሉቃስ 21 ተመዝግቧል) ወደዚህ ምድር ተመልሶ ከመምጣቱ በፊት የተወሰኑ ነገሮች መፈጸም እንዳለባቸው ተናግሯል። የጀመረውም በዚያን ጊዜ ገና በቅርቡ ዳግም የታነጸውን የቤተ መቅደስ ሕንፃ መፈራረስ በመተንበይ ነበር (ማቴ. 24፡2፤ ማር. 13፡1፤ ሉቃስ 21፡6)። ከዚያም በመቀጠል ጦርና የጦር ወሬ እንደሚሰማ በመግለጽ፥ ይህ ሊያስጨንቀን እንደማይገባ ይናገራል። እነዚህ ነገሮች መሆን ያለባቸውና ተከትለዋቸውም የዓለም ግጭቶች፥ ከከፍተኛ የመሬት መንቀጥቀጦችና ረሀቦች ጋር የሚመጡ ናቸው። በተጻፈው ታሪክ ውስጥ እንደ ዛሬው የበረከተ የመሬት መንቀጥቀጥ የተፈጸመበት ጊዜ የለም። ከሰሐራ በስተ ደቡብ ባለው የአፍሪካ ክልል ያለው እጅግ አስፈሪ ረሀብ፥ በእስያ የሚገኘው አስጨናቂው የመከር መዛባት፥ በባንግላዴሽ ያለው ረሀብ የሚነገር አይደለም። በመቀጠልም ክርስቶስ በክርስቲያኖች ላይ የሚነሣውን ተቃውሞና ስደት ይተነብያል (በታሪክ ሁሉ እንደዚህ ክፍለ ዘመን ሰማዕታት የበዙበት ጊዜ የለም)።

እንዲሁም ስለ ብዙ የሐሰት ነቢያት መምጣት ይናገራል። ዛሬ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች አሉን? ሞርሞንስ (የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለኋለኛ ዘመን ቅዱሳን) የተባለውን ሃይማኖት የመሠረተውን ጆሴፍ እስሚዝ፥ ቲዎሶፊ የተባለውን ያመነጩችውን ማደም ብላቬትስኪ፥ ክርስቲያን ሳይንቲስቶች የተሰኘውን የፈለሰፈችውን ሚስዝ ቤከር ኤዲ፥ የይሖዋ ምስክሮች የተባለውን ያቋቋመውን ፓስተር ሩሴል፥ ኤሌን ዋይት እና ጥቁር «መሢሖች»ን ለመጥቀስ ደግሞ አይዛያ ሽምቤ፥ ሌክጋንያኔ የተባሉትን ማቅረብ ይቻላል። መንፈሳዊ ተመስጦንና ሌሎችንም እንቅስቃሴዎች የሚለማመዱትን የሕንድ ጉሩዎችን በመመልከት ለመቀጠል እንችላለን። በተጨማሪም አሮጌና አዲስ የሐዋርያት አብያተ ክርስቲያናት የፈጠሩትን ሐዋርያትን፥ የመጨረሻው ነቢይ ነኝ ባዩን ዊሊያም ብራንሃምንም እናገኛለን። ብዙ ሰዎች ክርስትና ይህ ነው ብለው ወደዚህ እንግዳ የማታለያ ትምህርት ማተኮራቸው በጣም የሚያሳዝን ነው። ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች። ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን (ይህን ከ100፥ 500፥ 1000 ወይም ከ1900 ዓመታት በፊት ማወቃቸው አያስገርምም?) ይህ የመንግሥት ወንጌል «በዓለም ሁሉ



ይሰበካል (የሬድዮ ስርጭት አገልግሎትንም ከግምት አስገባ)፤ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል።» የሕዝቅኤል 38 እና የኢዩኤል 2 «ታላቁ መከራ» ተገልጿል። የምንኖረው ታላቅ ግጭት ባለበት ዓለም ውስጥ ነው። ስለ ሆነም ተጠበቁ የሚል መልእክት ከክርስቶስ ተሰጥቶናል። ለምን? «የጊዜውን ምልክቶች» ከ«ጸናው የትንቢት ቃል» ጋር ማስተያየት እንችል ዘንድ ነው (2ኛ ጴጥሮስ 1፡19)። በዚህም ትክክለኛ ወደ ሆነ ውሳኔ እንድንደርስ ነው። መረጃው ሁሉ በእምነትና በተግባር ጉዳዮች ሙሉ ለሙሉ ተእማኒነት ስላለው፥ ወደ እግዚአብሔር ቃል እውነትነት አብልጦ ያመዝናል።